# የክብር ዘበኛ ጦር ግዳጅ መደናቀፍ
## (ሐሙስ ታኅሣሥ ፯ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም.)

የመድፍ ተኩስ ወደ ፩ኛ ክፍለ ጦር ተጀምሮ ፲፭ ደቂቃዎች እንዳለፉ በየስፍራው ተኩስ ተከፈተ:: ለማጥቃት ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር ተጠግቶ የነበረው የክብር ዘበኛ ጦር "ኤች አወር" ሰ-ሰዓት ነበረው:: ይህ "ኤች አወር" ወይም ሰ-ሰዓት፣ በ፱ ሰዓት ጨበጣ ውጊያ ግባ የሚል ከሆነ፣ ከዚህ ሩብ ሰዓት ቀደም ብሎ የከባድ መሣሪያ ተኩስ መቆም አለበት:: በቀር ግን፣ ባልሆነ ሰዓት የክብር ዘበኛ ጦር ከተንቀሳቀሰ በራሱ ላይ ድብደባ ሊደርስበት ይችላል:: "ኤች አወር" ደርሶ የክብር ዘበኛ አጥቂ ጦር ለጨበጣ ውጊያ ሊገባ ሲጠባበቅ የመድፍ ተኩስ በድንገት በመቆሙ፣ አጥቂው ጦር ምክንያቱን ባለማወቁ ተደናግሮ፣ የነበረው አማራጭ አድፍጦ መጠበቅ ሆነ::

በሻለቃ ተፈራ ወልደ ትንሣኤ ዋና አዛዥነትና በሻለቃ መላኩ በቀለ ምክትል አዛዥነት ይመራ የነበረው አንደኛ ብርጌድ ደግሞ፣ ከጃንሜዳ ለቆ ጠቅላይ ሠፈሩን አራዳ ጊዮርጊስ በማምጣት አንደኛ ክፍለ ጦርን ለማጥቃት እንቅስቃሴውን በሱማሌ ተራ፣ በተክለ ሃይማኖት በኩል አድርጐ ቀድሞ አንበጣ መከላከያ (ኋላ የአየር መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤት) ከሆነው ቦታ ሲደርስ በዚያ መሽጐ የነበረ አንድ የጦር ሠራዊት ክፍል ተኩስ ከፍቶ እንቅስቃሴውን ገታው:: በጉዞ ላይ የነበረው የክብር ዘበኛ ጦር ከመኪና ወርዶ የመከላከልና የማጥቃት ተኩስ ከፍቶ፤ የጦር ሠራዊት አባሎችን ከምሽጋቸው በአጭር ጊዜ አስለቅቆ፤ አካባቢውን ነፃ አደረገ:: ይሁን እንጂ ግዳጁን ወደሚወጣበት ቦታ ቶሎ ለመድረስ፣ ከየመኪናው ወርዶ የነበረው የክብር ዘበኛ ሠራዊት ቀደም ብሎ ወደ ነበረበት መኪና እንዲሣፈር ሲፈለግ፤ አብዛኛው ጦር ከድቶ ስለነበረ ሊገኝ አልቻለም:: የሚገርመው ሾፌሮቹ ሳይቀር መኪናቸውን ትተው በመሔዳቸው፤ የወታደር ማጓጓዣ መኪና ታጣ:: አዛገፉ በአካባቢው አልፈው የሚሔዱ ከባድ የግል የጭነት መኪናዎችን አስገድዶ በማስቆም፤ የተረፉ ወታደሮቹን አሣፍሮ ገነት ሆቴል አካባቢ እንዲያደርሱ አደረገ::

ከዚያም ውጊያውን ለመቀጠል ወደ ቁርቆስ ቤተ ክርስቲያን ሲያቀና ያን አካባቢ እንዲጠብቁ ከተመደቡት ከጦር ሠራዊት አባሎች ጋር በድንገት ሲገናኙ፤ የጦር ሠራዊቱ አባሎች "እኛ ከእናንተ ጋር ነን:: መዋጋት አንፈልግም" ብለው በሰላም አለፉ:: የክብር ዘበኛ ሠራዊትም ዐላማው ወደነበረው አንደኛ ክፍለ ጦር ግቢ በምዕራብ በኩል ዘልቆ ተኩስ ከፈተ:: ከውስጥ የረባ የመልስ ተኩስ አልገጠመውም:: ምክንያቱን ሲጠይቅ የጦር ሠራዊት ጠቅላይ መምሪያውን ከአንደኛ ክፍለ ጦር ወደ በቅሎ ቤት አዛውሯል ተባለ:: ጠቅላይ መምሪያቸውን የለወጡበት አንዱ ምክንያት የክብር ዘበኛ መድፈኛ ከተኮሳቸው ሁለት የመድፍ ጥይቶች አንዱ የዐፄ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት ከውድቀት ለማዳን መኳንንቱ ተሰብስበው ይመካከሩበት ከነበረው አዳራሽ ጐን ከነበረ ቤት አንዱ ማዕዘን ላይ ስላረፈ፣ በዚያ ተደናግጠው ነው ተባለ:: በኮሎኔል ጃገማ ኬሎ ሪፖርት ለመዛወሩ ምክንያት ተብሎ የተገለጸው ግን ጠቅላይ

መምሪያው በክብር ዘበኛ መድፈኛ ጦር ለምት ይመዘገባል በሚል ግምት አስቀድሞ ነበር።

ይህ በዚህ እንዳለ፣ የአጥቂው ጦር አዛዥ የሻለቃ ተፈራ ወልደ ትንሣኤ ከአንደኛ ክፍለ ጦር ግቢ በአንድ ሺህ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘውን አዲሱን ጠቅላይ መምሪያ ለማጥቃት ኃይሉን ለማሰባሰብ ሲሞክር፣ የተገኘው ሠራዊት ብዛት ሁለት ሻምበል የማይሞላ ሆነ። የጦሩን አቅም አጠናክሮ ግዳጁን ለመወጣት ተባባሪ የነበረውን የፈጥኖ ደራሽን ጦር ለማምጣት ከመረጃ መኮንኑ ከመቶ አለቃ አምዴ ደበበ ጋር አንድ ጓድ ጦር ይዞ በጂፕ ከቂርቆስ ወደ ትንባሆ ሞኖፖል በመዝለቅ የፈጥኖ ደራሽ ጦር ካለበት ጉልፍ ክለብ ከነበረው ግቢ ሲደርስ፤ በዚያ የነበረው የፈጥኖ ደራሽ ጦር አዛዥ ሻለቃ (በኋላ ሌፍተናንት ኰሎኔል) ረታ፣ ‹‹ ተፈራ! ተፈራ!›› ብሎ ጠርቶ አቁሞ አቅፎ የሚስም መስሎ በመያዝ እሱንና አብረውት የነበሩትን ሳያስቡት አስከብቦ ምርኮኛ አደረጋቸው። ከክብር ዘበኛ አንደኛ ብርጌድ ሻለቆች ውስጥ የ፫ኛ ሻለቃ ጥብቅ አዛዥ የነበረው ሻለቃ ገብረ የሱስም ከብርጌዱ አዛዥ ጋር ግንኙነት ስለተቋረጠ ከብርጌዱ ዘመቻና ማሠልጠኛ መኮንን ከሻምበል አሰፋ አርአያ ጋር ግንኙነት ፈጥሮ የብርጌድ ጥብቅ አዛዥ ፈጥኖ ደራሽን አስተባብራለሁ ብለው ሔደው ስለመቅረታቸው አስታውቆ ከሻምበሉ ጋር እንቅስቃሴውን ወደ ዋናው ግባቸው ለማድረስ ወሰኑ።

ይህ በእንዲህ እያለ የውጊያው ትእዛዝ በተሰጠበት ጊዜ፣ ሻለቃ መላኩ በቀለ በሌለበት በምክትል አዛዥነት ሻለቃ ተፈራ ወልደ ትንሣኤን እንዲረዳ ተብሎ፣ በጄኔራል መንግሥቱ ሲታዘዝ በአቅራቢያው አልነበረምና ከቆየበት ቆይቶ ጠቅላይ መምሪያ ሲደርስ ይህንኑ ስለገለጹለት፤ ከሻለቃ ወርቁ ወልደ ጊዮርጊስ ጋር በመሆን ከጠቅላይ መምሪያው ወደ ፩ኛ ብርጌድ ጠቅላይ መምሪያ ወደሆነው አራዳ (መናገሻ) ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሲሔዱ፤ ጦሩ ተነቃንቆ ያገኙታል። ከዚህ ቀጥሎ ስለሆነው ሁኔታ የሻለቃ መላኩ ሲገልጽ፣

> ጦሩ ካለበት ለመድረስ ተከታትለን ሔደን ማይጨው አደባባይ (በቃሉ ሜክሲኮ) ሲደርስ የአንደኛ ብርጌድ ጦር ከሁለት ተከፍሎ አንደኛው ከማይጨው አደባባይ ወደ ጥይት ፋብሪካ በሚወስደው መንገድ ሲሔድ፣ ሁለተኛው ክፍል በገነት ሆቴል ወደ አዲሱ ቄራ ወደ ቂርቆስ ቤተክርስትያን የሚወስደውን መንገድ ይዞ ተጓዘ። እኔና የሻለቃ ወርቁ ወልደ ጊዮርጊስ አሁን የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሕንፃ ከተሠራበት ተነስተን ቁልቁል ወደ ገነት ሆቴል ልንወርድ ስንል፤ በዚያ አካባቢ ከነበሩት የጦር ሠራዊት መኮንኖች መኖሪያ ፎቆች ተተኮሰብን። እኛም ተመልሰን አሁን የዕድገት ሕንፃ (ፕሮግሬስ ቢልዲንግ) በተሠራበት በኩል ወደ ትምባሆ ሞኖፖል በሚወስደው መንገድ ዘልቀን ወደ ጥይት ፋብሪካ ልናቀና ስንል፤ በፋብሪካው ግቢ ውስጥ የነበሩ ወታደሮች እየተኮሱ አላሳልፍ አሉን። ስለዚህ በዚያው በመጣንበት መንገድ ተመልሰን ገነት ሆቴል አጠገብ ስንደርስ፤ ለግዳጅ ተሰማርቶ የነበረው የክብር ዘበኛ ጦር

> ግዳጁን ትቶ ወታደራዊ ሥርዓት በሌለው ሁኔታ በብዛት ተበታትኖ ሲመለስ አገኘነው። ምን ከባድ ችግር አጋጠመ ብለን ብንጠይቅ መልስ ሳይሰጥ ዝም ብሎ ጥሶን ሔደ። ስለሻለቃ ተፈራ ወልደ ትንሣኤ ሁኔታ ብንጠይቅም ይሔ ነው ብሎ የሚነግረን አጣን። በዚህ ምክንያት ወደ ጠቅላይ መምሪያ ተመልሰን ለጄኔራል መንግሥቱ ሁኔታውን ሪፖርት አደረግን።[18]

በማለት የክብር ዘበኛ አንደኛ ብርጌድ የዘመቻ ዕጣ የተጠቃለለበትን ሁኔታ ይዘረዝራል።[19] ስማቸው ከላይ የተጠቀሰው መኮንኖች ከኩብለላ የተረፈውን ሠራዊት እያስተባበሩ በተለይም ሻምበል አሰፋ አርአያ እስከ ቂርቆስ ቤተክርስቲያን አካባቢ መዝለቅ ቢችልም፣ በመጨረሻ በሠራዊቱ መመናመን ምክንያትና ሌሎችም ተዳምረው ውጤት ለማግኘት ሳይቻል ቀረ።

በፓትርያርኩ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ስም በአውሮፕላን የተበተነው የውግዘት ቃል ወረቀት ለክብር ዘበኛ ጦር የውጊያ የሥነ ልቦና ውድቀት ምክንያት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረጉ ግልጽ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የመድፍ ተኩስ መቆሙ በዘውድ ጠባቂው ወገን ላይ ለመፍጠር ታስቦ የነበረውን ተፅዕኖና የውጊያ ዕዝ ቅደም ተከተል አደናገረው። ለማንኛውም በያቅጣጫው የተላከው የክብር ዘበኛ ጦር እስከደረሰበት ድረስ ግዳጁን መወጣት ቀጥሏል። በሻለቃ ተፈራ በላይ ዋና አዛዥነትና በሻለቃ ኃይለ ማርያም ሌንጮ ምክትል አዛዥነት የተመራው ፪ኛው ብርጌድ ክብር ዘበኛ ጦር፣ ከጃንሜዳ በመነሣት በግቢ ገብርኤል በኩል አድርጎ በዑራኤልና በእስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን መካከል አልፎ አንደኛው ክፍል፣ የራስ ብሩን ቤት ወደቀኝ ትቶ ፊት ለፊት በመዝለቅ አንደኛ ክፍለ ጦርን በምሥራቅ ሲያጠቃ፤ ሁለተኛው ክፍል፣ የራስ ብሩን ቤት በጋሻው አድርጎ በመውጣት የመድፈኛን ግቢ እንዲይዝ ግዳጅ ተሰጥቶት ነበር። በመሆኑም በሻለቃ ኃይለ ማርያም ሌንጮና በሻምበል ለገሠ ደምሴ የሚመራው ጦር የራስ ብሩን ሠፈር አልፎ ሁለት ጊዜ ያህል የሐዲዱን መስመር በመያዝ ወደ ፩ኛ ክፍለ ጦር ለመግባት ሞከረ። ሆኖም እየኮበለለ ከሔደው የተረፈው ኃይል በጣም አነስተኛ ስለነበር እንዳሰበው ፩ኛ ክፍለ ጦርን መያዝ ሳይችል ቀረ።

በአጠቃላይ ውጊያው ዘጠኝ ሰዓት ተጀምሮ ጥቂት እንደተካሔደ በክብር ዘበኛው ዘማች ክፍል የሚሰማው ወሬ ጥሩ አልነበረም። ቀስ እያለም በግራ ቀኙ በኩል የሚሰማው ተኩስ ቀዝቀዝ እያለ መጣ። አሥራ አንድ ሰዓት ተኩል አካባቢ ቁጥራቸው ከሁለት መቶ እስከ ሦስት መቶ የሚደርሱ (የቤተ መንግሥት ሰዎች ናቸው ይባላል) ኃይለ ሥላሴ! ኃይለ ሥላሴ! ድረስ በነፍሴ እያሉ እየጨፈሩ ከቅድስተ ማርያም አካባቢ የመፈንቅለ መንግሥቱ እንቅስቃሴ መምሪያ ወደ ሆነው ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ (አሁን የፌደራል ሰበር ሰሚ ፍርድ ቤት) ፊት ለፊት ወደ ገነተ

[18] ሻለቃ መሳኩ በቀለ
[19] ዝኒ ከማሁ

ልዑል ቤተመንግሥት ዘልቀው ሽብር ፈጠሩ:: የጭፈራው መልእክት ግልጽ ነበር:: መፈንቅለ መንግሥቱ ከሽፏል እንደማለት ነበር:: በዚህ ጊዜ ጄኔራል መንግሥቱ ከጠቅላይ መምሪያው ቢሮ ወደ ደጅ ወጥተው ሽጉጣቸውን አውጥተው በመያዝ "ምንድነው?" "ምንድነው?" ብለው ሲጠይቁ የጥበቃ ኃላፊው ሃምሣ አለቃ ከላይ የተገለጸውን የጭፈራ ቃል ነገራቸው:: እሳቸውም "እምምም" ብለው አሽሚጠው ወደ ውስጥ ተመለሱ::

ይህ ሲሆን እኔ የክብር ዘበኛ ጦር ዘመቻን መደናቀፍ ተረድቼ ስለበር ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ቢወጣልኝ ከዚያ ይገፔ ለማሸሽ ከሰንደቅ ዐላማ መስቀያው አጠገብ የመኪናዬን ሁለት በር ከፍቼ ሞተሩ እንደተነሣ ከመኪናዬ ወጥቼ ሜዳው ላይ ቆሜ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ዓይቶኝ ወደ በር ብቅ ቢልልኝ በማለት ስጠባበቅ፣ ሃያ ደቂቃ ያህል ሆኖኝ ነበር:: በዚህ መኻል ወርቅነህ ዓይቶኝና ፍላጐቴን ተረድቶ ቀስ እያለ ወደ እኔ ሲመጣ፣ ጄኔራል መንግሥቱ ዓዩትና "ወርቁ! ወርቁ! የትነው የምትሔደው? ተመለስ! ተመለስ!" ሲሉት ተመልሶ ገባ:: እኔም እንዳያስይዙኝ ሠግቼ መኪናዬን ከነበረችበት አንስቼ ወደጓሮ ወስጄ አቁሜ ትንሽ ዘግየት ብዬ ስመለስ፣ በር ላይ የነበረው ዘብ «አሥራ ሁለት ሰዓት አንባቢ የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች ከነበሩበት ከመፈንቅለ መንግሥቱ ጠቅላይ መምሪያ በችኮላ በሁለት ላንድሮቨር መኪኖች ተሣፍረው ወጡ» ብሎ ነገረኝ:: እኔም ቶሎ ወደ መኪናዬ ተመልሼ እነሱ በወጡበት በር ወጥቼ ወደ ስድስት ኪሎ ስከተል ሁለት ላንድሮቨር መኪኖች ወደ አሜሪካን ኤምባሲ አቅጣጫ በፍጥነት ሲሔዱ ስላየሁ በፍጥነት እየነዳሁ ተከትያቸው ዛሬ ሽሮሜዳ አካባቢ ያለው አምሐ ደስታ ትምህርት ቤት አጠገብ ደረስኩባቸውና ጣያቸው እነሱ ሣይሆኑ የቤተ መንግሥት ላንድሮቨሮች ሆነው አገኘኋቸው:: ከዚያ ወደነበርኩበት ተመልሼ እንደኔው የደነዘዛቸው ጥቂት ወታደሮች አግኝቼ መሪዎቹ የት ሔዱ? ስላቸው «እንጃ! ወደላይ ነው የሔዱት» አሉኝ:: እንደገና ተመልሼ ወደ አምሐ ደስታ ትምህርት ቤት ሔድኩና ሌሎች ላንድሮቨሮች በዚህ አልፈዋል ወይ? ብዬ ከዚያ አካባቢ ያገኘኋቸውን ሰዎች ሁሉ ብጠይቅ ሁሉም አላየንም ስላሉኝ፣ መምሪያ ወደ ነበረው ተመልሼ የተገኘ ፍንጭ እንዳለ ወታደሮችን ጠየኩ:: እነሱም ምንም እንደማያውቁና ግራ እንደተጋቡ ገለጹልኝ:: እኔም እማደርገውን አጥቼ ወደቤተሰቤ ስሔድ ከወርቅነህ ጋር እስከ መጨረሻው ላንገናኝ ተለያየን:: በኋላ እንደተረዳሁት ላንድሮቨሮቹን ዓይቼ እኔ ወደሽሮ ሜዳ ስሔድ እነመንግሥቱን የያዟቸው ላንድሮቨሮች ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ነው የገቡት::

በሌላው ግንባር ደግሞ ከታንከኛና ከፈረሰኛ ክፍል የተውጣጣውና የመከላከያ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤትን አጥቅቶ እንዲይዝ የታዘዘው በሻለቃ ጌታቸው አፈወርቅ የሚመራው ጦር ከጠቅላይ ሠፈሩ ከጃንሜዳ ተነሥቶ በታላቁ ቤተ መንግሥት በኩል በፊት በር አድርጐ፣ በዘውዲቱ ሆስፒታል ተጠግቶ ወንዙ ውስጥ ገብቶ እንዲያጠቃ ነበር የታሰበው:: ሆኖም፣ በኋላ የፓፓሲኖስ ሕንፃ በተሠራበት፣ ከመከላከያ ሚኒስቴር አጠገብ (ቀደም ብሎ የእንጨት መሰንጠቂያ በነበረበት ቦታ)፣ ብዙ የጦር ሠራዊት

ባልደረቦች ከመመሸጋቸውም ሌላ፣ አሁን ተስፋዬ ቀጀላ ሕንፃ (ሐራምቤ ሆቴል) ከተሠራበት አጠገብ ካለው መስቀለኛ መንገድ ላይ፣ አንድ የጦር ሠራዊት ብረት ለበስ ተሽከርካሪ ቆሞ የክብር ዘበኛውን ጦር አላላውስ አለው። የመከላከያ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤትን እንዲይዝ ከታዘዙት፣ ከሻለቃ ጌታቸው አፈወርቅ ምድብ፣ የአንዱ ክፍል አዝማች የነበረው የሻምበል ታደሰ ከበደ ስለወቅቱ የውጊያ እንቅስቃሴ የገለጸው ጥሩ የዓይን ምስክር ስለሆነ እንደሚከተለው ተቀምጧል።

> *የመከላከያን ሕንፃ ለመያዝ ስናመራ፣ ከአርጌው ቁራ ጀምሮ (አሁን ንግድ ማተሚያ ቤት) ከተሠራበት አካባቢ እስከ ሐራምቤ ሆቴል አጠገብ እስካለው ድልድይ ድረስ ወንዝ ወንዙን በመሔድ ዘለቅን። መከላከያ ግቢ ውስጥ የነበረች ባለ ጐማ ታንክ በመትረየስ አላስጠጋ ብላን በማስቸገሯ የወገን ታንክ መጥቶ የመትረየሷን አፍ ዘጋልን። ከእንጨት መሰንጠቂያው አሁን ፓፓሲኖስ ሕንፃ ከተሠራበት አካባቢ ከነበሩት የጦር ሠራዊት አባላት ውስጥ ሰባ ሦስቱ ተማረኩ። መከላከያ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤትንም አሥር ሰዓት ሲሆን ያዝነው። ከምሽቱ አንድ ሰዓት አካባቢ ምርኮኞቹን ወደ ሦስተኛ ሻለቃ በመላክ እኔ እዚያው አደርኩ።*[20]

በዘውድ ጠባቂው ወገን ግን ስለተኩሱ አጀማመር እርስ በእርሱ የተጣረሰ መረጃ ተሰራጭቷል። የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አዘጋጅ ታኅሣሥ ፲፩ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. "ሰላማዊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥንትም ዛሬም ወደፊትም ለንጉሠ ነገሥቱ ታማኝ ነው" በሚል ርእስ ስር በመጀመሪያ ተኩሱን የጀመረው ማን እንደነበር ለጄኔራል መርዕድ ላቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ተኩሱን የከፈተው የክብር ዘበኛ ነው ማለታቸው ተመዝግቧል። ተኩስ የከፈተውም በመከላከያ ሚኒሲቴር ግንባርና በስተኋላ እንዲሁም በራስ ብሩ ቤት በኩል እስጢፋኖስ ላይ ከዚያም በአዲሱ ቁራ መንገድ ዞሮ ቁልፍ ሥፍራዎችን ከያዘና ከከበበ በኋላ እንደሆነ ቀርቧል። ይህ ግን ለታሪክ ሽሚያ ካልሆነ በቀር ትክክለኛ ምስክርነት ሆኖ አይገኝም። ለምሳሌ የጦሩ አዝማች የነበሩት ኮሎኔል ጃገማ ለበላይ ባቀረቡት የዘመቻ ዘገባ ክብር ዘበኛ ተኩስ ጀመረ ያሉት ለ፱ ሩብ ጉዳይ ማለትም ጄኔራል መንግሥቱ ውጊያውን በመጀመር ቀዳሚ ሆኖ ላለመገኘት በማሰብ ትዕዛዙን በሰጡበት ሰዓት እንደነበር ያመለክታል። ስለዚህ በጄኔራል ጽጌ ዲቡ ጎትጓችነት በጄኔራል መንግሥቱ አዛዥነት ለዘጠኝ ሩብ ጉዳይ የማጥቃት ተኩስ ተሰማ። ወዲያው የጠላት መድፎችና ሞርታሮች የወገንን ሠፈር መደብደብ ጀመሩ ብለው ኮሎኔል ጃገማ በሪፖርቱ ያሠፈሩት[21] ከጄኔራል መርዕድ ቃል ጋር የሚጣረስ መሆኑን እንገነዘባለን።

ክብር ዘበኛ የውጊያው ጀማሪ ስለመሆኑ የኮሎኔል ጃገማ ሪፖርትም ይቀበላል። እንደኮሎኔል ጃገማ፣ የክብር ዘበኛ ዘማች ጦር የማዘዣ ቦታውን አራዳ ጊዮርጊስ፣ ክብር ዘበኛ መኮንኖች ሠፈርና ጃንሜዳ ክብር ዘበኛ ፈረሰኛ ክፍል፣ ጠቅላይ መምሪያውን ደግሞ በጠቅላይ ሚኒስቴር ግቢ በማድረግ የማጥቃት ውጊያ የጀመረው

---

[20] *ሻምበል ታደሰ ከበደ፣ የአንድ ሻምበል ጦር አዝማች የነበረ።*
[21] *የኮሎኔል ጃገማ ኬሎ ሪፖርት፣*

የክብር ዘበኛ መድፈኛ ክፍል ነበር። ይህንንም ልክ ለዘጠኝ ሰዓት ሩብ ጉዳይ (በወታደራዊ ሰዓት አቆጣጠር በ፲፬:፵፭ ላይ) በክፍለ ጦሩ ጠቅላይ ሠፈር በስተሰሜን ምሥራቅ በራስ ብሩ ቤት እንዲሁም በኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት በጦርሠራዊቱ ላይ የማጥቃት ተኩስና ንቅናቄ በማድረግ ፈፅሟል። ከዚያ በኋላ በየሥፍራው ተኩሱ ተስፋፋ ማለት ነው።[22]

የኮሎኔል ጃገማ ኬሎ ሪፖርት ስለጦር ሠራዊት ሥምሪት የሚያመለክተው ደግሞ

> የወገን ከባድ መሣሪያ የክብር ዘበኛ ሦስተኛ ሻለቃ ሠፈርን፣ የክብር ዘበኛ መድፈኛ ሠፈርን፣ በተክለ ሃይማኖት በኩል የሚወርደውን ጦር፣ የታችኛውን ግቢ፣ በሰሜን ቀኝ ደረት የጠላት መድፍ ቦታን፣ የፀጥታን መሥሪያ ቤትን፣ የድሮ ቁራን፣ የቀበናን ወንዝ ከሰሜን እስከ ምሥራቅ፣ የአባሬን ሰርጥ፣ ከጦር ሠራዊት መሐንዲስ ሠፈር በስተጀርባ ሆኖ እንዲመታ፣ ቢያስፈልግ በጥሪ እንዲደበድብ...

መታዘዙን ነው። ስለዚህ የክብር ዘበኛ የመድፍ ተኩስ በ፩ኛ ክፍለ ጦር ላይ ተጀምሮ ፲፭ ደቂቃዎች እንዳለፈ በየሥፍራው ተኩስ ስለመከፈቱ ነው የኮሎኔል ጃገማ ኬሎ ሪፖርት የሚገልጸው።

---

[22] ዝኒ ከማሁ፤

## ምስቅልቅል (ዓርብ ታኅሣሥ ፯ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም.)

ውጥረቱ ሰፍኖ ከተማዋ ያነጋችው በጭንቀት ተውጣ ነበር:: ዛሬም እንደ ትናንቱ፣ የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች የሚያሳስቧቸው፣ ሌሊቱን ሲያወጡ ሲያወርዱ ያደሩባቸው ሁለት አማራጭ ዕቅዶች ነበሩ:: እነሱም፣ አንደኛ የክብር ዘበኛውን ሠራዊት ከያለበት አሰባስቦና አጠናክሮ የጦር ሠራዊት የሚጀምረውን የማጥቃት እርምጃ በመመከት በቁጥጥር ሥር ለማድረግ ተገቢውን ዝግጅት ማከናወን፤ ሁለተኛ በተጀመረው የሽምግልና ጥረት ለውጡ ያለ ተጨማሪ ደም መፋሰስ እንዲጠናቀቅ፣ በተቻለ መጠን ማበረታታት ነበሩ:: ስለዚህ፣ የመጀመሪያውን ዕቅዳቸውን ለመፈፀም በክብር ዘበኛ መኮንኖች አማካኝነት ሐሙስ በዘጠኝ ሰዓት ከጦር ሠራዊት ጋር ፍልሚያ ጀምሮ፣ ወዲያው ውጊያ አቁሞ በየቦታው ከተበተነው የወገን ጦር ጋር ለመገናኘት ሐሙስ ለዐርብ አጥቢያ ከንጋቱ ፲፩ ሰዓት ቃኚዎችን አሠማሩ:: ሆኖም፤ በየቦታው አንድም የክብር ዘበኛ ሠራዊት አባል አልተገኘም::

ስለዚህ ሁኔታ ከተዋጊ መኮንኖቹ አንዱ የነበረው የሻምበል ታደሰ ክበደ ሲያስታውስ እንዲህ ይላል::

> ዐርብ ጠዋት ከንጋቱ በአሥራ አንድ ሰዓት ወደ ፍል ውሀ ቃኚ ቡድን ላኩ:: ያገኘሁት መልስ አንድም ወታደር በቦታው አለመኖሩን ነው:: እራሴ ወደ ፈረሰኛና ታንከኛ ግቢ ሄድኩ:: እዚያም እንኳን ሰው ወፍ አልነበረም:: ግቢው ጭር ብሏል:: በጣም አዘንኩ:: ሌላው ቀርቶ፣ አዛዥ የተባለው እንኳን በሥሩ ለሚገኙት የመቶ አለቆች ትእዛዝ ሰጥቶ ሸሽቷል:: ቆይቼ ያገኘሁት ቢኖር ምክትል አዛዡን የሻምበል ንጋቱ ተሊላን ነበር:: ከእርሱም ጋር ተለያየን:: እሱ ወደ መሣሪያ መጋዘን ሲገባ እኔ ከግቢው ውጭ መኪናዬን ተደግፌ የምሔድበትን ማሰላሰል ጀመርኩ:: በዚህ ጊዜ፣ አንድ ወታደር "ስሪ ኳርተር" መኪና ይዞ መጣና "ጄኔራል መንግሥቱ ይፈልጉዎታል" አለኝ:: እኔም፣ "ስሜን ጠርተው ነው ወይ ያዘዙህ?" ብዬ ጠየቅኩት:: ወታደሩም "ያገኘኸውን መኮንን ነው የተባልኩት" ብሎ እንደመለሰልኝ በመኪናው ተሣፍሬ ሔድኩ::
>
> ሐሙስ ወደ ማታ ጦር ሠራዊቱ የከፈተውን የማጥቃት ውጊያ መክቶ በቁጥጥር ሥር ለማዋል፣ በየአቅጣጫው ተሰማርቶ የነበረው የክብር ዘበኛ ሠራዊት "ከወገን ጋር አንዋጋም" በማለት ከተሰለፈበት ግንባር እየተመለሰና እያመለጠ በመበታተን የገባበት ጠፋ::[23]

ዐርብ ዕለት ጠዋት ሲፈለግ ሊገኝ አለመቻሉን የሻምበል ታደሰ ክበደ ቁርጥ ባለ ሁኔታ ያስቀመጠው ሲሆን፤ ከታኅሣሥ አምስት እስከ አስራ ሁለት ከመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች ጋር የነበረው የመቶ አለቃ ተክለ ማርያም ዘረፉም እንዲህ ሲል ያጠናክረዋል::

> ዐርብ ጧት በቤተ መንግሥቱ አካባቢ የነበርን መኮንኖች፣ "ላስቸኳይ ስብሰባ አረንጓዴ ሳሎን" እንድንገባ ተደርጐ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ለመኮንኖቹ ንግግር አደረጉ:: የንግግራቸው ፍሬ ሐሳብም፣ «ይህ ሠራዊት

[23] የሻምበል ታደሰ ክበደ፤

(ክብር ዘበኛ) ግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱን አልከዳም፤ አይከዳምም:: ነገር ግን፣ መኳንንቱ የንጉሡን አመራር አበላሽተዋል:: ሕዝቡን አደንቁረው ገዝተው አደህይተዋል:: የክብር ዘበኛ እንደመሆናችን መጠን ይህን ዓይነት የተበላሸ አመራር በአጭር መቅጨት አለብን:: አንድ ወታደር በወር የሚያገኘው ደሞዝ ለአንድ ባለሥልጣን ውሻ እራት የማይበቃ አሥራ ሰባት ብር ነው፤ አስቡ» በማለት አንዳንድ የማጠናከሪያ ሐሳቦችን ከሰጡ በኋላ፣ "አሁን ሔዳችሁ ይህን መልእክት ለሠራዊቱ አስረዱ" አሉ:: መኮንኖቹም ይህን መግለጫ ካዳመጡ በኋላ ጥያቄዎች አቀረቡ:: ከጥያቄዎቹ መካከል፣ "ይህንን ለምን ቀደም አድርጋችሁ አልነገራችሁንም? አሁን ነገሮቹ ተበላሽተዋል:: ከዚህ በኋላ ቅስቀሳ ብንጀምር ምን ውጤት ሊገኝ ይችላል" የሚሉ የተቃውሞ መንፈስ የነበራቸው ይገኙበታል:: ገለጻው ሲሰጥ ጄኔራል መንግሥቱም አብረው ስለነበሩ፣ ተጨማሪ ሐሳብ በመስጠት መኮንኖቹ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ባቀረቡት ሐሣብ መሠረት ሔደው ወታደሮችን በያገኙበት አሰባስበው እንዲያነቃቁ አበረታቱ:: በዚህ ጊዜ አንዳንዶቹ ሐሳቡን በመቀበል ሠራዊቱን ለማነቃቃት ከቤተ መንግሥቱ እየወጡ ሔዱ:: ሌሎች ግን፣ ገለጻው ከተሰጠበት ቦታ ከቤተ መንግሥቱ አልወጡም::[24]

የክብር ዘበኛ ሠራዊት የውጊያ መንፈስ ይህን በመሰለ በተበታተነ መልክ እንዳለ፤ በሌላ በኩል ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህና ጄኔራል መንግሥቱ እነ ሜጀር ጄኔራል መርዕድ መንገሻ የሚከፍቱትን የማጥቃት ተኩስ አቁመው፣ በሁለቱ ወገኖች መካከል ሽማግሌ ገብቶ ተቀራርበው ያለ ተጨማሪ ደም መፋሰስ ለውጡ እንዲካሔድ ለማድረግ እንዲተባበሩ የአሜሪካ ኤምባሲ የፖለቲካ ኃላፊውን ጠርተው ለማነጋገር ወሰኑ::

በመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች በኩል፣ እነዚህ እንቅስቃሴዎች ከጠዋት አንሥቶ እየተደረጉ ሳለ፤ በተቃራኒው በጦር ሠራዊት በኩል ደግሞ ቀጥሎ የተጠቀሱት እንቅስቃሴዎች ይካሔዱ ነበር:: ከሐረር በባቡር እንዲመጣ የታዘዘው የጦር ሠራዊት ጠዋት በአንድ ሰዓት አዲስ አበባ እንደገባ፣ የተመደበለትን ቦታ እንዲይዝ፣ የአየር ኃይል ግንኙነት ክፍልም፣ አዲስ አበባ ከዋናው ጦር መምሪያ አጠገብ እንዲቋቋም ሲደረግ፣ የጦር ሠራዊቱ በሚገኝበት ግንባር ሁሉ በመሬት ላይ የነጭ መስቀል ምልክት እንዲለጠፍ ሆነ:: ነጩ መስቀል አውሮፕላን ጦር ሠራዊቱን በስሕተት እንዳይደበድበው ለማመልከት የተደረገ ነበር::

እንግዲህ በክብር ዘበኛ ላይ የማጥቃት እርምጃውን ዛሬም ለመቀጠል አስፈላጊውን መሰናዶ በማድረግ ላይ እንዳለ፤ የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች በጠዋት የተመካከሩበትን ሰላም የማምጣቱን ጉዳይ ለማስፈጸም፣ ከልዑል ራስ እምሩ

[24] የመቶ አለቃ ተክለ ማርያም ዘረፉ፤ ከመቶ አለቃ ተክለ ማርያም ዘረፉ ስላገኘሁት መረጃ ዋና ምክንያቱ ሻለቃ ነጋሽ ድንበሩ ናቸው:: ሻለቃ ነጋሽ የመፈንቅለ መንግሥቱ ታሪክ መጻፍን አጥብቀው ይደግፉ ስለነበረ፤ ስለሁኔታው ጥሩ መረጃ ያለው የመቶ አለቃ ተክለማርያም ዘርፉ ስለሆነ፤ እንደምንም አግባብተህ ብትጠይቀው ይጠቅምሃል ባሉኝ መሠረት መቶ አለቃ ዘረፉን በማነጋገሬ ብዙ ጠቃሚ መረጃዎችን አግኝቻለሁ::

ጋር በመሆን ለአሜሪካ ኤምባሲ የፖለቲካ ኃላፊ ሐሳባቸውን በመግለጽ፣ ከሌሎች ሁለት የሥራ ባልደረቦቹ ጋር ወደ እነ ሜጀር ጄኔራል መርዕድ ለሽምግልና ተላኩ። የፖለቲካ ኃላፊውም የልዑል ራስ እምሩንና የመፈንቅለ መንግሥቱን መሪዎች ሐሣብ በመቀበል፣ ከእነ ሜጀር ጄኔራል መርዕድ ጋር በአንደኛ ክፍለ ጦር ውስጥ ተገናኝቶ ከተነጋገሩ በኋላ ጊዜ ሳይወስድ ተመልሶ በመምጣት፣ "ከእነሜጀር ጄኔራል መርዕድ በኩል ተወክሎ ከእናንተ ጋር የሚነጋገር አንድ ሰው ተሰጥቶን፣ ኤምባሲያችን ድረስ ወስደን እንዲቆየን አድርገናል። ከእናንተ በኩል እንደዚሁ አንድ ሰው ስጡንና በኤምባሲው ሁለቱ ይነጋገሩ" ብለው ገለጹ። በዚህ ጊዜ ልዑል ራስ እምሩ፣ "ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ቢሔድና ቢነጋገር ይሻላል" የሚል ሐሳብ ካቀረቡ በኋላ እንደገና እንደማቅማማት ብለው ሐሳባቸውን ለወጡና "ግዴለም! ወርቅነህ ይቆይ! ገርማሜ ቢሔድ ይሻላል" አሉ። ሌሎቹም በገርማሜ መሔድ ተስማምተው፣ ከፖለቲካ ኃላፊውና ከባልደረቦቻቸው ጋር ወደ አሜሪካ ኤምባሲ ሔዱ። ብዙ አልቆዩም ወዲያው መልሰው ይዘውት መጡ።

ገርማሜ ደርሶ እንደተመለሰ የውይይቱን ውጤት በጉጉት ይጠብቁ የነበሩት ልዑል ራስ እምሩ ሁለቱ ወገኖች ተገናኝተው ተነጋግረው የደረሱበትን ፍሬ ነገር ለማወቅ ጠየቁት። እሱም "ከእኔ ጋር ለመነጋገር የመጣው ሻለቃ አሰፋ ለማ ነው። በኔ በኩል በተቻለ መጠን ለሱ ሊገባው በሚችል መንገድ አስረድቸዋለሁ። እርሱ ከተናገረው ውስጥ ግን መያዣ ያለው የተጨበጠ ቃል አላገኘሁም» የሚል ቅሬታ የተሞላበት መልስ ሰጣቸው። እርሳቸውም ሁኔታው እጅግ ስላሳሰባቸው በውጤቱ አዘኑ። ከጄኔራል መንግሥቱና ከሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ጋርም ቆመው ጥቂት ከተነጋገሩ በኋላ፣ ለአቡነ ባስልዮስና ለሜጀር ጄኔራል መርዕድ በሕዝብ ላይ እልቂት እንዳይፈጠር የሁሉም ኃላፊነት መሆኑን በማስገንዘብ ማስታወሻ ጽፈው፣ የአሜሪካ ኤምባሲ የፖለቲካ ኃላፊው ለሁለቱም ሰዎች እንዲያደርሱላቸው ይቅርታ በመጠየቅ ሰጡዋቸው። ኃላፊውም በትሕትና አደርሳለሁ፤ ችግር የለም ብለው ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር እንዳመሩ፤ የአየር ኃይል አውሮፕላኖች እየተመላለሱ በከተማዋ ላይ ማንዣበብ ጀመሩ። መትረየስም በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ላይ መተኮስ እንደያዙ በሕንፃው ጥግ ከነበሩ የክብር ዘበኛ ወታደሮች መሐል ጥቂት ሞቱ።

የአየር ኃይል አውሮፕላኖች በከተማው ላይ ሲያንዣብቡና ተኩስ በከፈቱበት ሰዓት ከነገሌ ቦረና እንዲመጣ የተጠራው የጦር ሠራዊት አዲስ አበባ ገብቶ ከ፲፪ኛ ሻለቃ ብረት ለበስ ጦር ጋር አብሮ በመሰለፍ፣ በኮሎኔል ጃገማ ኬሎ ግንባር ቀዳሚነት ባቡር ጣቢያን ይዞ በመጠባበቅ ላይ ይገኝ ነበር። በኋላም ፲፩ኛ ሻለቃ ተጨማሪ ሆኖ ተመደበለት። ፳፯ኛ ሻለቃ ጦር ከመድፈኛ ግቢ ተነሥቶ ወደ ከተማው የሚሔደውን ጐዳና ይዞ ለማጥቃት ሲሰናዳ፣ የ፲፪ኛ ሻለቃ ከበቅሎ ቤት በስተጀርባ ተነሥቶ፣ በታንክ እየታበጀ፣ ፀራስ ብሩ ሠፈር አልፎ በእስጢፋኖስ በኩል በኢዮቤልዩና በታላቁ ቤተመንግሥት በማድረግ፣ የክብር ዘበኛን መድፈኛ ሠፈር ለመያዝ ዝግጅቱን አጠናቀቀ።

ከነገሌ የመጣው ጦርም እንዲሁ ከደብረ ዘይት ወደ አዲስ አበባ የሚወስደውን መንገድ፣ የሜክሲኮ አደባባይን፣ አምስተኛ ፖሊስ ጣቢያን፣ ወደ ተክለ ሃይማኖት የሚወስደውን ቀናታ መንገድ እና ቸርቸል ጐዳናን በመያዝ በታንክ እየተረዳ ወደ መናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ በመውጣት፣ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥትን እንዲይዝ ሥምሪት ተሰጠው:: የጦር ሠራዊት የማጥቃት ሥምሪት እየተቀላጠፈ እንዳለ፤ የአሜሪካ ኤምባሲ የፖለቲካ ኃላፊ ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን ከልዑል ራስ እምሩ የተሰጣቸውን ማስታወሻ ይዘው ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር በመሔድ ሜጀር ጄኔራል መርዕድን አግኝተው ሰጧቸው:: ሜጀር ጄኔራል መርዕድም፣ የራስ እምሩን ማስታወሻ ዓይተው መልስ በመጻፍ እነዚህን መልእክተኞች ሸኙዋቸው:: እነሱም ወዲያው ወደ ገነተ ልዑል ቤተመንግሥት በመምጣት አሁንም በጉጉት ይጠብቁ ለነበሩት ለልዑል ራስ እምሩ ማስታወሻውን ሰጡ:: ራስ እምሩም የማስታወሻውን ፍሬ ሐሳብ ከተረዱ በኋላ እንደገና በጣም አዘኑ:: መልእክቱን አድርሰው ለተመለሱት ለአሜሪካ ኤምባሲ ኃላፊዎች "የጠየኩትን ትቶ ያልጠየኩትን መለሰልኝ:: የባሰውን እናንተን ብዙ አደከምኳችሁ:: ይቅርታ አድርጉልኝ" በማለት አሰናበቷቸው:: ወዲያው ጠዋት ሦስት ሰዓት ገደማ በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት የመትረየስ ተኩስ ከፍተው የነበሩት የአየር ኃይል አውሮፕላኖች ተመልሰው መጥተው መደብደብ ጀመሩ:: ከዚያም በጦር ሠራዊት የአዲስ አበባ ብርጌድ ዋና አዛዥ በቀዳሚነት የማጥቃት እርምጃውን ለመውሰድ የተቋቋሙት መሪ መቶዎች ከ፲፩ኛ ሻለቃ አንድ የመቶ ጦር፣ ፲፮ኛ ሻለቃ በሙሉ፣ ከማረፊያ ሠፈር ለተጠባባቂነት የተመደቡ ወታደሮችን ጨምረው በማሰለፍ ከየአቅጣጫው ውጊያ ከፈቱ::

ውጊያው እንደተከፈተም ጄኔራል መንግሥቱ ግርማዊት እቴጌ መነንና ቤተሰቦቻቸው ካሉበት ቪላ እንዲወጡ ተደርጐ ልዑል አልጋ ወራሽ ወደ ሚገኙበት ቤተመንግሥት በመምጣት ተገናኝተው፣ ጠንካራ ጥበቃ እንዲደረግላቸዉ ስላዘዙ፣ አንድ የመኮንኖች ቡድን በላንድሮቨር መኪና ወደዚያው ሔደ:: የቡድኑ ኃላፊ ሻምበል ባዬ ጥላሁን ነበር:: ሆኖም፣ ግርማዊት እቴጌ መነን በነበሩበት ቪላ ተመድበው የነበሩት የዘቦች ኃላፊ፣ ግርማዊት እቴጌ መነንና ቤተሰቦቻቸውን ለማስረከብ ፍቃደኛ አልሆኑም:: የቪላውን ቅጥር ግቢ በርም በቋጥኝ ድንጋይ አዘጉት:: ወታደሮቹም በተጠንቀቅ እንዲጠብቁ አዘዙ:: በዚህ ጊዜ ሻምበል ባዬ ኃላፊውን ሻለቃ አንጋጋው ኃይሌን (በኋላ ኮሎኔል) እቴጌ መነንን ከነቤተሰቦቻቸው እንዲያስረክቡት ሲያነጋግር፤ "ከጄኔራል መንግሥቱ የማዘዣ ደብዳቤ እስካልመጣልኝ ድረስ አምኜ ማስረከብ አልችልም" የሚል መልስ ሰጡ:: በሻምበል ባዬ ጥላሁን የሚመራው የመኮንኖች ቡድን ተመልሶ ወደ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት አመራ:: ወዲያው፣ በአንድ ጐን፣ "የክብር ዘበኛ ሠራዊት ከጦር ሠራዊት ጋር ደም አንፋሰስም" በማለት መሣሪያውን እያስቀመጠ ግርማዊት እቴጌ መነን ወደሚገኙበት እቴጌ ቪላ መኮልኮል ጀመረ:: የጥበቃ ኃላፊ የነበሩት፣ ሻለቃ አንጋጋው ስለተፈጠረው ምስቅልቅል ሲገልጹ

የክብር ዘበኛ ሠራዊት ውጊያ ተስኖት ሳይሆን ተበሳጭቶ ‹ውርደት ላይ ወደቅን› እያለ፤ የተሰጠውን የውጊያ መስመር በራሱ ሐሳብ

እየለቀቀ፣ ወደ ሰሜን እንጦጦ ተራራ በሚያፈገፍግበት ጊዜ፣ በተለይም የቀጨኔ አካባቢ ሕዝብ ለዘረፋና ለግድያ እየተዘጋጀ በመምጣቱ መከለያ ለማግኘት ወደ ግርማዊት እቴጌ ቪላ እየገባ መጠለልን መረጠ። እኛም በግርማዊት እቴጌ ቪላ ጥግ ለመጠለል የሚመጡ ጓደኞቻችንን ለመቀበል ወደኋላ አላልንም።[25]

በማለት ያወሱት፤ የክብር ዘበኛን መዝረክረክ ሲያመለክተን፤ በሌላ በኩል ደግሞ፣ የጦር ሠራዊቱ ኃይል እየተጠናከረ መምጣቱን የሚያሳይ ነበር።

የክብር ዘበኛ ውጊያውን ባለመፈለግ በየሥፍራው መበታተኑ ግልጽ መሆኑ ሲታወቅ፤ የሻለቃ አንጋጋው ኃይሌ በግርማዊት እቴጌ ቪላ አካባቢ ጦር ሠራዊት ተኩስ እንዳይከፍት፤ ዋስትና ስለሚገኝበት ሁኔታ አመቻችተዋል። ይህንን ሁኔታም ራሳቸው እንዲህ ሲሉ ይተርኩታል።

ታኅሣሥ ሰባት ቀን ረፋድ ላይ፣ የመፈንቅለ መንግሥቱ ተቃዋሚ የሆነው የጦር ሠራዊት ወደ ሰሜኑ ክፍል እየገፋ ስለመጣ፤ ግርማዊት እቴጌን ሲጠብቅ ለነበረው እንዲሁም ከአደጋ ለማምለጥ በቤተ መንግሥቱ ከተሰበሰቡት መኮንኖችና ወታደሮች አንድ ዐይነት ሐሳብ ቀረበልኝ። ሐሳቡም፣ "እኛ በግርማዊት ዙሪያ የተሰበሰብን ሲሆን፣ እያጠቃ የመጣው ኃይል የሚያውቀው የክብር ዘበኛ ባልደረባ መሆናችንን ስለሆነ፤ አደጋ ይጥልብናልና ከግርማዊት የዋስትና ቃል እናግኝ" የሚል ነበር። ይህንን ወዲያው ለልዕልት ተናኘወርቅ ነገርኩ። እሳቸውም ፈጥነው ገብተው ለእቴጌ ከነገሩ በኋላ "በእምነት እንደጠበቃችሁን ሁሉ እኛም እንጠብቃችኋለን" የሚል መልስ ሰጥተዋል ስለተባልኩ ለወታደሮቹና ለመኮንኖቹ ይህንኑ አበሰርኳቸው። ከአምስት ሰዓት በኋላ የጦር ሠራዊት ኃይሉን የሚቋቋመው አጣ። በነፃ መንገድ ወደ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት እየተጠጋ መጣ። ስለዚህ ግርማዊት እቴጌ ቪላ ከሚገኘው የክብር ዘበኛ ሠራዊት ጋር ግጭት እንዳይፈጥር ለልዕልት ተናኘወርቅ ከጀኔራል መርዕድ ጋር በጦር ሜዳ ሬዲዮ እንዲገናኙ አደረኩ። በሬዲዮ ግንኙነታቸውም ቤተ መንግሥታችንን በእምነት ሲጠብቁ በቆዩትና፣ በኋላም እኛን ሲሉ በአጠገባችን በተሰበሰቡት የክብር ዘበኞች ላይ አደጋ እንዳይደርስ ማስጠንቀቂያ ይሰጥ የሚለውን የግርማዊት እቴጌን መልእክት አስተላለፉላቸው።[26]

ይህ በእንዲህ እንዳለ የጦር ሠራዊት በቅድሚያ የተቆጣጠረው የክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያን ነበር።

[25] ሻለቃ አንጋጋው
[26] ዝኒ ከማሁ

# ንጉሡ ስለ መፈንቅለ መንግሥቱ እንዴት ሰሙ?

በብራዚል ይፋዊ ጉብኝት በማድረግ ላይ የነበሩት ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በዙፋናቸው ላይ መፈንቅለ መንግሥት መደረጉን የሰሙት፣ ቀደም ሲል የጠቀስናቸው ሁኔታዎች በአዲስ አበባ ውስጥ ይካሔዱ በነበረበት ጊዜ ነበር። የሰሙትም ከተለያዩ አቅጣጫዎች በተሰራጩ ዜናዎችና ከአገር ውስጥም ከተላኩ መልእክቶች እና ልዩ ምንጮች ነበር። ረቡዕ ታኅሣሥ ፭ ቀን የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ለተለያዩ አገሮች መንግሥታት በኢትዮጵያ የመንግሥት ለውጥ መደረጉን፣ በቴሌግራም አስታውቆ ነበር። በመሆኑም፣ የእንግሊዝ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በእንግሊዝ አገር ለሚገኙ የውጭ ዲፕሎማቶች፣ በብራዚል ለሚገኙ ጋዜጠኞችና ለብራዚል መንግሥት በዚያ በሚገኘው አምባሳደሩ አማካይነት፣ በጉብኝት ላይ ባሉት በዐፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ላይ መፈንቅለ መንግሥት የተካሔደ መሆኑን እንዲያውቁ አድርጓል።

በጉብኝቱ ጊዜ፣ ከንጉሡ ጋር አብሮ ተጉዞ የነበረው የሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ መምሪያ ባልደረባና የጉዞው የሬዲዮ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ወርቁ ተስፋ ስለሁኔታው ሲገልጽ፤ "ብራዚል በዓለም ውስጥ የተከናወኑትን የየዕለቱን ዐበይት ድርጊቶች በርእሰ ዜና መልክ በጣም በአጫጭር ዓረፍተ ነገሮች በማዘጋጀትና፣ ከከፍተኛ ፎቆች ላይ በኒዮን[27] መብራት በማሳየት ሕዝብ እንዲያውቀው ያደርግ ስለነበረ፤ በዚያ አማካይነት ዜናውን ሳያውቁ አልቀሩም የሚል ግምት አለኝ" ብሏል። ይህ አንዱ ማወቂያ መንገድ ነው። ከንጉሡ ጋር በአጃቢነት ወደ ብራዚል ለጉብኝት ከሔዱት መካከል፣ ልዕልት አይዳ ደስታ አንዷ ነበሩ። የልዕልት አይዳ እህት ልዕልት ሶፊያ ደስታ እንደሚሉት ደግሞ ከእህታቸው ባገኙት መረጃ መሠረት ከዚሁ ከአዲስ አበባ ልዑል ሣኅለ ሥላሴ በላኩት መልእክት ሳያውቁ አልቀረም። ልዑል ሣኅለ ሥላሴ የአማተር ሬዲዮ ተነጋጋሪና የተነጋጋሪዎች ማህበር አባል ስለነበሩ፤ በሬዲዮው አማካይነት በኢትዮጵያ መፈንቅለ መንግሥት እየተካሔደ መሆኑንና፣ የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎችንም ስም ዝርዝር አስተላልፈው ነበር፣ የሬዲዮ መልእክት ተቀባዩ የተቀበለውን መልእክት በትክክል ለግርማዊ ጃንሆይ ስላደረሰ፤ ጃንሆይ መልእክቱን እንዳገኙ ጉብኝቱን አቋርጠው ወደ አገራቸው የሚመለሱ መሆኑን ለተከታዮቻቸው አሳወቁ።[28] ልዑል ሣኅለ ሥላሴ ባስተላለፉት መልእክት ከዐመፀኞች ስም ዝርዝር ውስጥ፣ የሌፍተናንት ኮሎኔል ወርቅነህን ስም ዓዩ። ይሔን ጊዜ፣ በጣም ደንግጠውና ተደንቀው ልዕልት አይዳን "አየሽ! አየሽ! ወርቅነህም አለበት! ይላል፣ ይህን ታምኛለሽ?" ብለው ሲጠይቋቸው፤ "ጃንሆይ ከተጻፈ እንዴት አይሆንም ይባላል?"[29] ብለው መለሱላቸው።

27 በመብራት እየተንፀባረቀ ጽሑፍ የሚያሳይ ሰሌዳ

28 ይህን የሬዲዮ መልእክት፣ ታኅሣሥ ፳፮ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. እ.ኤ.አ. ኒውስ ዊክ ጋዜጣ ‹‹አንበሳው በችግር ላይ›› በሚል ርዕስ በዓምዱ ላይ አውጥቶታል።

29 ልዕልት ሶፊያ መስከረም ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም. ቃለመጠይቅ አድርጌላቸው እንደነገሩኝ

ከላይ የተጠቀሰውን የልዑል ሣኅለ ሥላሴን የቴሌግራም መልእክት የጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ የኢንተርናሽናል የሬዲዮ መልእክቶች መቆጣጠሪያ ኃላፊ፣ የመቶ አለቃ ታምሬ የማነ ብርሃን ጠልፈውት ስለነበር፤ ረቡዕ ታኅሣሥ ስድስት ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. አምሥት ሰዓት ተኩል ገደማ አምጥተው ለሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ሲሰጡት፤ እኔም እዚያው ነበርኩ። ይህ ለጄኔራል መንግሥቱ ቢገለጽም የተወሰደ እርምጃ አልነበረም።

ከዚህ ሌላ፣ የንጉሡ የፕሬስ ኃላፊ የነበረው አቶ መብዓ ሥላሴ ዓለሙ ግምት ደግሞ ንጉሡና አጃቢ ቤተሰቦቻቸው ልዑል ሣኅለ ሥላሴ ባሥተላለፉት መልዕክት አማካኝነት ሰሙት የሚለውን አስተያየት የሚደግፍ ነው።

> ታኅሣሥ አምስት ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. በብራዚል ሳኦፖሎ ከተማ፣ ከሰዓት በኋላ በአሥር ሰዓት አካባቢ፣ ትምህርት ቤት ወይም ፋብሪካ ይመስለኛል በመጐብኘት ላይ እንገኝ ነበር። ከዚያ ጋዜጠኞች ፕሬስ ኦፊሰሩ የታል? የታል? እያሉ ሲጠይቁ፣ ሰዎች ወደ እኔ ጠቆሙዋቸውና መጥተው፣ «በአገራችሁ መፈንቅለ መንግሥት ተካሒዷል ይባላል፤ እርግጥ ነው ወይ?» ብለው ጠየቁኝ። እኔም ደንግጬ ፊቴ ልውጥ ሲል፣ ልዕልት አይዳ አይተው፣ «መብዓ! መብዓ! የጠየቀህን ዐውቀናል። ከጥቂት ጊዜ በፊት ሰምተነዋል፤ ዐውቀነዋል፤ ዝም በለው» አሉኝ።[30]

የኤርትራ ራስ ገዝ ዋና አስተዳዳሪ (ቺፍ ኤክስኩቲቭ) የነበሩት ቢትወደድ አስፍሐ ወልደ ሚካኤል የንጉሡ ነገሥቱ የክብር አጃቢ ከነበሩት አንዱ ነበሩ። እርሳቸው ንጉሠ ነገሥቱ ስለመፈንቅለ መንግሥቱ ሰሙ ያሉበት ሁኔታ ደግሞ ሌላ ነው።

> ከምዕራብ አፍሪካ ወደ ብራዚል ለመሔድ አትላንቲክ ውቅያኖስን ማቋረጥ አለና፣ የያዝነው አውሮፕላን ዲ.ሲ. ስድስት ስለነበረ ችሎ አይዘልቅ ይሆናል ብሎ በመጠርጠር፣ በጄት አውሮፕላን መሔድ ተመረጠ። እንደምርጫው ለመፈጸም ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ አክሊሉ ሀብተ ወልድ በዚያን ጊዜ በፓሪስ አምባሳደር ወደነበሩት ወንድማቸው ወደ አቶ አካለ ወርቅ ሀብተ ወልድ ስልክ ደውለው ብራዚል አድርሶ ለመመለስ የጄት አውሮፕላን ኪራይ ምን ያህል እንደሚሆን ከባለአውሮፕላኖች ጠይቀው ያገኙትን ዋጋ እንዲገልጹላቸው አዘዙ። የቀረበው ዋጋ ከመግዣ ዋጋ የማያንስ መሆኑን መልስ ሰጡ። ምን ይሻላል ተባለና፣ ካፒቴን ዓለማየሁ በተባባሪ ፓይለትነት ከእኛ ጋር ስለነበረ፣ (ዋናው ፓይለት አሜሪካዊ ነበር) ጃንሆይ ዓለማየሁን ይኸ አውሮፕላናችሁ አትላንቲክን መሻገር ይችላል? ብለው ሲጠይቁት በፈገግታ፣ 'እንዴት? እንዴት አይችልም?' ብሎ መለሰና፣ በዚያው ለመሔድ ተወስኖ ከሰባት እስከ ስምንት ሰዓት የሚፈጅ መያዣ መጨበጫ የሌለው፣ ላዩ ሰማይ ጥቁር ታቹ ውቅያኖስ ጥቁር በሆነ አስጨናቂ ጉዞ

[30] አቶ መብዓ የንጉሡ የፕሬስ ኃላፊ ሲሆኑ፤ በጉብኝቱ ወቅት አብረው የነበሩ በመሆናቸው ቃለመጠይቅ አድርጌላቸው የነገሩኝ ነው።

ተጉዘን ውቅያኖሱን አቋርጠን "ሬሲፌ" ከተባለችው የብራዚል የወደብ ከተማ በደህና አረፍን።

ሬሲፌ ያለውን የጉብኝት ፕሮግራም አጠናቀቅን። በማግሥቱ ታኅሣሥ አራት ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ወደ አዲስዋ ዋና ከተማ ወደ ብራዚሊያ ጉዞ ሆነ። እዚያ ግሩም የሆነ ኦፊሴላዊ አቀባበል ተደረገልን። ታኅሣሥ አምስት ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ወደ ቀድሞ የብራዚል ዋና ከተማ ሪዮዲጂነዬሮ ተጉዘን ሳኦፓሎ እስከደረስን ድረስ ስለ መፈንቅለ መንግሥቱ የተሰማ ምንም ነገር አልነበረም። ሳኦፖሎ እንደደረስንም ከፍ ያለ የክብር አቀባበል ተደርጉልን በከፍተኛ አጀብና ጭብጨባ ታጅበን ተጉዘን ጃንሆይን ወደ ማረፊያቸው ካደረስን በኋላ፣ ሻንጣችንን ይዘን ወደየማረፊያ ክፍላችን ስንገባ፣ እኔ ከገባሁበት ክፍል ሬድዮ አገኘሁና ከፈትኩ። የሬዲዮ ጣቢያው በፖርቱጊዝ ቋንቋ፣ 'አዲስ አበባ ላይ መፈንቅለ መንግሥት ተደረገ' ብሎ ተናገረ። እኔ ጣልያንኛ ስለምችልና ሁለቱ ቋንቋዎች ደግሞ ብዙ የሚመሳሰሉ ስለሆነ መልእክቱን ለመረዳት አላዳገተኝም። ነገሩ አስደንግጦኝ፣ ጆሮዬ ነው ወይስ ሬዲዮኑ ተናግሯል እያልኩ ደንዝዤ ቆየሁና ከሩብ ሰዓት በኋላ እንደገና ስከፍተው ያንኑ ደግሞ አረዳኝ። 'የበቅሎ ዕቃ ሁሉም ለየራሱ አለቃ' እንዲሉ በብራዚል ማዕከላዊው መንግሥት ጥሪ ንጉሡ የአገሪቱ እንግዳ ሆነው አገር በመጐብኘት ላይ እያሉ፣ ይህ የራስ ገዝ ክፍል እሱ ደግሞ ለራሱ መንግሥት ሆነና ቁጥጥር ያልተደረገበትና እንግዳውን የሚያስከፋ ዜና በማሰራጨቱ አሳዘነኝ። ማዘን መከፋትና መጨነቅ ካመሰቃቀለኝ በኋላ፣ ነገሩን ለንጉሡ ለመግለጽ እሳቸው ወደ አረፉበት መሔድ ግድ ሆነብኝ። አንገቴን ደፍቼ መሬት መሬት እያየሁ ስሔድ፤ የጉዞው የፀጥታ ጉዳይ ኃላፊ የሆነው ኮሎኔል ይርጉ እንዳይላሉ መንገድ ላይ አገኘኝና ሬስቶራንቱ ጠፍቶኝ የምፈልግ መስሎት ወደዚያ መርቶ ወሰደኝ። እኔ ግን ሐሳቤ ሌላ ስለነበር 'ልንገረው? አልንገረው?' እያልኩ በማመንታት ካወጣሁ ካወረድኩ በኋላ ሳልነግረው ቀረሁ።

ንጉሡ ካረፉበት አካባቢ ስደርስ ምንም ነገር የለ። ጭር ብሏል። እማደርገው ጨንቆኝ ወደ ማረፊያዬ ተመልሼ ቆየሁና ከእኩል ሰዓት በኋላ ንጉሡ ወዳረፉበት ተመልሼ ስሔድ ትርምስ ሆኗል። ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ከጃንሆይ ማረፊያ ክፍል ገብተው ወሬውን ነግረው ወጥተዋል። ንጉሡም ተከታትለው ወጥተው ይንቆራጠጣሉ። "ምንድን ነው?" ብዬ ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉን ስጠይቅ፣ ከሎንዶን አንድ ጋዜጠኛ ደውሎ፣ "ቤታችሁ መቃጠሉን ሰምታችኋል ወይ?" ብሎ ጠየቀኝ። "ምንድን ነው የምታወራው?" ስለው "በአገራችሁ እኮ መፈንቅለ መንግሥት እየተካሔደ ነው። እዚህ (ለንደን) ያለውን አምባሳደራችሁን ብጠይቀው መልስ አልሰጥ አለ" አለኝ። በዚያን ጊዜ በለንደን የኢትዮጵያ አምባሳደር ልጅ እንዳልካቸው መኰንን ነበሩ። እኔን «ስለጉዳዩ ምን ታውቃለህ» ቢለኝም ‹‹ምንም አላውቅም›› አልኩት። እሱ ተናግሮ እንደጨረሰ፣ በዚህ አገር የሚገኘው የእንግሊዝ አምባሳደር ደወለልኝና «በአገራችሁ መፈንቅለ መንግሥት ተካሒዷልና ፍቀድልኝና መጥቼ ላስረዳ» አለኝ አሉ። እንዳሉትም አምባሳደሩ ልዑል አልጋ ወራሽ በሬዲዮ ያሰሙትን ዐዋጅ

የያዘ ቴፕ ይዞ መጣ። ከንጉሡ ጋርም ተነጋግሮ ቴፑን አሰምቶ ተነሥቶ ሔደ።

የእንግሊዙ አምባሳደር ከጃንሆይ ጋር ለመነጋገር እርሳቸው ወደ አሉበት ክፍል ሲገባ፣ እውጪ ያለነው ነገሩን በትክክል ለማወቅ ተጨንቀን ተጠበን እንዳለን፣ የእልፍኝ አስከልካዩ ኮሎኔል ደበበ ኃይለ ማርያም (ኋላ ሜጀር ጄኔራል) ወደ ብራዚል ከመሔዳችን በፊት ላይቤሪያ ሳለን ከእኔ ጋር አንድ ጨዋታ ተጫውተን ስለነበር በዚህ የውዥንብር ጊዜ ከብዙ ሰዎች መካከል እኔን ነጥለው አጠገባችን ወደ ነበረው ክፍል አስገብተው፣ 'ይኸውልዎ የተነጋገርነው እኮ ደረሰ' አሉ። የተነጋገርነውም እንዲህ የሚል ነበር። ንጉሡ ለምንድን ነው እንዲህ የሚያደርጉት? አልጋ ወራሽ! አልጋ ወራሽ ናቸው። ግን እንደዚህ ራቅ ወደ አለ አገር ሲወጡ ሕዝቡን 'በጸሎትህ ተከተለኝ፣ አልጋ ወራሻችንን ጠባቂ ሰጥተንሃል' ማለት ሲገባ ያለተወካይ እንዲያው አገር ጥሎ መሔድ አይገባም። በዐፄ ምኒሊክ ጊዜ እኮ ንጉሡ ቅርብም ቢሔዱ ሩቅ ራስ ዳርጌን ይወክሉ ነበር። ንጉሡ ልክ እንደዚያው አልጋ ወራሽን ለምን አይወክሉም? ደግሞ እንደ ራስ አበበ ዐይነቱን ትልቅ ሰው ከአልጋ ወራሽ በኋላ በምንትስ ደረጃ ጠባቂ አበበ ነው ለምን አይሉም? ተባብለን አምተን ስለነበር "ይኸው የተነጋገርነው ደረሰ" አሉኝ። ወዲያው ጃንሆይ ወደ አረፉበት ክፍል ተጠርተን ገባን። ጃንሆይም፣ "አገራችን፣ በተለይም ዋናው ከተማችን፣ ጤና የለውም ስለተባለ ነው የጠራናችሁ። ወታደር በመንግሥታችን ላይ ተነሥቷል።" እንግዲህ የክብር ዘበኛ ማለትም ትንሽ ከበዳቸው መሰለኝ "ወታደር ተነሥቷል፣ የሆነው ሆኖ፣ እኛንም ደግፎ የተነሣው አብዛኛው ክፍል ነው" አሉና "የአስፋው ወሰንንም የዐዋጅ ንግግር ሰማነው። በፈቃዱ የገባበት ነው" የማለት አዝማሚያ አሣይተው ሊያልፉ ሲሉ፣ ልዕልት አይዳ ደስታ "እንዴ? ተገደው ያደረጉት ነው። ሰዎች ባሉበት ይሰማ? የተገደዱ መሆናቸው ያስታውቃል" ብለው ሲከራከሯቸው፣ መልሰው ግርም በማለት "አዎ! የገዛ ልጃችንን አንጠረጥርም" አሉና ነገሩ በዚህ ቆመ።

ከዚያም በፕሮግራሙ መሠረት በአሥር ሰዓት "ስቴት ሀውስ" ወደሚሉት ሔደን እንግዶቹ ከአገሪቱ ባለሥልጣኖች ጋር ይተዋወቁና የሻምፓኝ ግብዣ ይደረጋል ስለሚል ጃንሆይ ምንም ዓይነት የለውጥ ምልክት ሳያሳዩ ቀጥ ብለው ሔደው ፕሮግራሙ ተጀምሮ አበቃ። ከዚያም በፕሮግራሙ መሠረት ሁለተኛው ጉብኝት ቀጠለ። ሶሪያውያን ናቸው የተባሉ ሀብታም ቤተሰቦች ንብረትና በጣም ዘመናዊ የሆነ እህሉ እንደታጨደ ቀርበለት ወቅቶ፣ አንፍሶ፣ አበጥሮ፣ ፈትጉ፣ አድርቆና ፈጭቶ፣ አቡክቶ ዳቦ ጋግሮ የሚያወጣ በጣም አስገራሚ የሆነ ፋብሪካ ነው ያየነው። ታዲያ በዚህ ጊዜ በእኛ አገር የሆነውን ሕዝብ በመገናኛ ብዙኃን ተሠራጭቶ ሰምቶት ስለነበር፣ ከሕዝብ መካከል "እንዴ እኒህ ሰውዬ አገራቸው የሆነውን ሰምተው ዝም ብለው ነው ወይስ ያልሰሙ ሆነው ነው?" እያለ ይንሾካሾክ ነበር። ሌላው ደግሞ አታየውም እንዴ?

ሰውነቱ ከስቶ" ሲል ሌላው "አይ በአንድ ቀን ከሱ ብለህ ነው?" እያለ እርስ በርሱ ይወያይ ነበር። የሆነው ሆኖ ጉብኝቱ በደህና ተፈጸመ።[31]

ጃንሆይ በአገራቸው የተካሔደውን መፈንቅለ መንግሥት ከላይ በተገለጸው አኳኋን ከተረዱ በኋላ ጉዟቸውን ከሳኦፖሎ ወደ ብራዚል፣ ከዚያ ወደ ሞኖሮቪያ ላይቤሪያ አምርተው ወደ አገራቸው የሚገቡበትን በር በህሊናቸው እያመራመሩና እያጣሩ ነበር።

## የመልስ ጉዞ መወሰንና የጭንቅ ጉዞ

ስለመልሱ ጉዞ አወሳሰን ቢትወደድ አስፍሐ እንዲህ በማለት ቀጥለዋል።

> ከዚያ ወደማረፊያችን እንደተመለስን ‹ጉበዝ!› አሉ ጃንሆይ፣ ‹እንግዲህ እኛ መነሣት አለብን። እነዚህ መቼም ጥሩ ሰዎች ናቸው፤ ገራገር ናቸው። ማታ የስቴት ግብዣ ይደረጋል። በዚያ ላይ ፕሬዚዳንቱ ምን ብሎ እንደሚናገር አያውቅም ይሆናል። ይኸም ማለት በኢትዮጵያ ብጥብጥ እያለ በንግግሩ ላይ ዕድሜ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እንበል ወይስ እንበል። ይኸን እየሰማን ምን እንበል፣ በማለት ይቸገራሉና፣ እኛ መሔዳችን ነው ብለህ ለፕሬዚዳንቱ ንገራቸው› ተብለው ጸሐፊ ትእዛዝ ተፈራ ወርቅ ኪዳነ ወልድ ታዘዙና ሔዱ። ከዚያ አውሮፕላኑ እንዲዘጋጅ ትእዛዝ ይሰጥና አብራሪዎቹ ሲፈለጉ፣ አገር አማን ነው ብለው ራቅ ብለው ሔደው ኑረው ጥቂት ጊዜ ወሰደ። እነሱ ተፈልገው መጥተው እኩለ ቀን ላይ ገብተን ልክ እኩለ ሌሊት አገሩን ለቀቅን።[32]

በወቅቱ ረዳት አብራሪ የነበሩት ካፒቴን ዓለማየሁ አበበም ሁኔታውን የሚያጠናክሩት፣

> ጃንሆይና የአገሪቱ መሪ በታላቅና ደማቅ በሆነ ሰልፍ መሐል ወደ ቤተ መንግሥቱ ሲያመሩ፣ እኛም እንደተለመደው ወደ ማረፊያችን ከመሔዳችን በፊት አውሮፕላኑን ለሚቀጥለው ጉዞ ማዘጋጀት ስለሚገባን ቴክኒካዊ ይዞታውን መፈተሽ፣ በቂ ቤንዚን መሙላት፣ ውስጡን ማጽዳት ጀመርን። ሳኦፖሎ ለአንድ ቀን ጉብኝት ሔደን አረፍን። የሚቀጥለው ፕሮግራም በማግሥቱ ወደ ሪዮዲጀኔሮ እንደሚሆን ተነገረንና ለአራት ሰዓት ያህል አውሮፕላናችንን አዘጋጅተን በቀረበልን አውቶሞቢል ወደ ሆቴላችን ጉዞ ጀመርን። ከሆቴሉ ደርሰን በእንግዳ መቀበያው ክፍል ተሰልፈን በመመዝገብ ላይ እንዳለን፣ በድምፅ ማጉያው ካፒቴን ዓለማየሁ በስልክ ይፈለጋሉ ተብዬ ተጠራሁ። በዚያ ቦታና ሰዓት በስልክ የሚፈልጉኝ የፕሮቶኮል ኃላፊዎች እንደሚሆኑ በመገመት "እኔ ነኝ" ብዬ ወደ ስልኩ ኦፕሬተር ቀረብኩ። እዚያ ክፍል ውስጥ ይግቡና ያነጋግሩ ተባልኩና ገብቼ "ሃሎ! ዓለማየሁ ነኝ ቀርቤያለሁ" ስል፣ ‹ስማ ዓለማየሁ ወደ አገራችን እንድንመለስ አስቸኳይ መልእክት ስለደረሰን ለመዘጋጀት ስንት ሰዓት ዕረፍት ያስፈልጋችኋል?› ብለው ደጃዝማች ካሣ ወልደ ማርያም ጠየቁኝ። ጆሮዬ የሰማውን ማመን አቃተኝና፣ ‹ምነው ምን

[31] ቢትወደድ አስፈሐ ወልደሚካኤል አጅበው ከሔዱት ባለሥልጣናት አንዱ ናቸው። እኔ ቃለመጠይቅ ያደረኩላቸው በ፲፱፻፺፩ ዓ.ም. ነው።

[32] ዝኒ ከማሁ

ተፈጠረ?› ብዬ ጠየኳቸው:: ‹ባጠገቤ ብዙ ጋዜጠኞች ስላሉ በስልክ ልነግርህ አልችልም:: ስምንት ሰዓት ያህል ዕረፍት አድርጋችሁ መነሣት ትችላላችሁ ወይ?› ሲሉኝ፤ መቻላችንን ስገልጥ፣ ‹ደግነው ተዘጋጁ› አሉኝ:: በዚህ መሠረት ካፒቴን ግሪን ዘንድ ሔጄ ሁኔታውን አስረዳሁት:: ካፒቴን ግሪን ምንም እንኳን በድንገተኛው ሁኔታ ቢደናገርም፣ ትዕዛዙ መፈጸም እንዳለበት ተስማማና የአውሮፕላኑን ሠራተኞች ሰብስቦ ወደ ኢትዮጵያ እንድንመለስ ታዘናል:: የነገው ፕሮግራም ቀርቷል፣ ከአሁኑዋ ሰዓት ጀምሮ ስምንት ሰዓት አርፈን በአውሮፕላን ማረፊያ መገኘት ስላለብን ተዘጋጁ ብሎ ትዕዛዝ ሰጠ::

ምንም እንኳን በደረሰው ሁኔታ ግራ ብንጋባም፣ ለአጭር ጊዜም ቢሆን የነበረንበትን ከተማ በመጠኑ ለመጐብኘትና አንዳንድ የመታሰቢያ ዕቃዎችም ለመግዛት ሔድን:: የድንገተኛው ጥሪ ምክንያት ግርማዊት እቴጌ በጠና ታመው ወይም አርፈው ይሆናል ብለን ገምተን ነበር:: ወደ ማታ ግን የመንግሥት ግልበጣ በመካሔድ ላይ መሆኑን ጭምጭምታ ሰማን:: ከዕረፍት በኋላ ማታውኑ ወደ አውሮፕላን ማረፊያው ተመልሰን ማንኛውንም ለጉዞ አስፈላጊ የሆነውን መረጃ አሟልተንና ዝግጁዎች ሆነን ንጉሠ ነገሥቱን መጠባበቅ ጀመርን:: ወዲያው ግርማዊ ጃንሆይ መጡና ጉዟችንን ወደ ሪሲፌ ቀጠልን::[33]


ቢትወድድ አስፋሐ ወልደ ሚካኤል
የኤርትራ የውስጥ አስተዳደር ኃላፊ/ቺፍ ኤክስፐርት

በማለት ነው:: በመንገድ ላይም ስለሁኔታው በቅጡ ባይወያዩበትም አጋጣሚዎችን ሁሉ እየተጠቀሙ ማንሳታቸው አልቀረም::

ስለዚህ ሁኔታ ቢትወደድ አስፍሐ ወልደ ሚካኤል በማስታወስ ያከሉት ደግሞ እንደሚከተለው ነው::

በዚህ ጉዞ ላይ ሳለን ራስ መስፍን ስለሺ አንድ ሕልም ዓየሁ፤ የአንድ ሰው ስም ጠርተው በሕልማቸው ያ ሰውዬ አማጬን በጭራ ሲጠራርገው ዓየሁ::” ብለው ነገሩንና ‹ያርገው! ያርገው!› ብለን እንደሣቅን ሬሲፌ አረፍን:: አገረ ገዥው መጥቶ ተቀበለን:: ነገሩን ሰምቶ ኖሮ አዘነ:: ወዲያው ቁርስ መጣ:: ጃንሆይ እምቢ አሉ:: ልዕልት አይዳን ብቻ ብይ

[33] ካፒቴን ዓለማየሁ ሕይወቱ በምድርና በአየር ፣ ገጽ171-181



ቢትወድድ አስፋሐ ወልደ ሚካኤል
የኤርትራ የውስጥ አስተዳደር ኃላፊ/ችፍ ኤክስፐርት

አንቺ ይላሉ:: የቀረነው ደግሞ እንኳን እህሉ ውሀው አልወርድልን ብሎ ስለተናነቀን የጃንሆይን ዐይንና ፊት እያየን በግድ ለመቅመስ ሞከርን::[34]

በዚሁ ጉዞ ከንጉሡ ጋር ወደ ብራዚል አብረው ለጉብኝት ሔደው የነበሩት ልዕልት አይዳ፣ በመልሱ ጉዞ ላይ ስለነበረው የንጉሡ ስሜትና ሁኔታ ሲገልጹ "ግርማዊ ጃንሆይ ምንም እህልና ውሀ አልቀመሱም:: እንዲቀምሱ ሲጠየቁ "አገሬ ስገባ እቀምሳለሁ እህህ!!!" እያሉ በረጅሙ ይተነፍሱና "ወይ አገሬ! ወይ አገሬ! እያሉ" ይቆጩ ነበር ብለዋል::

እንደ ካፒቴን ዓለማየሁ አባባል በዚህ ዓይነት ወደሪሲፌ በረው ቤንዚን ሞልተውና አውሮፕላኑ ተፈታትሾ አትላንቲክ ውቅያኖስን አቋርጠው ወደ ሞንሮቪያ ለመብረር ተነሡ:: በረራው ሌሊት ስለነበረ ባለሥልጣኖቹ አገር ቤት በተከሰተው ችግር ሳቢያ ስለተረበሹ እንዲሁ ሲንቆራጠጡ አደሩ:: ግርማዊነታቸው ግን የተለየ የመኝታ ክፍል ስለነበራቸው ሳይጠራ ማንም ወደ እሳቸው ክፍል ስለማይገባ በምን ሁኔታ ላይ እንደነበሩ ለማወቅ አልተቻለም:: ይሁን እንጂ ጃንሆይ የመሔዱን ነገር አላወላወሉበትም:: ስለ ስጃንሆይ ውሳኔ ቢትወድድ አስፍሐ ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ::

> ከዚያ ተነሥተን ሌሊት ላይቤሪያ ገባን:: ፕሬዝዳንቱ በደንብ ተቀበሉን:: ሁኔታው እስቲበርድ ይቆዩ:: ቤተ መንግሥቴ የርስዎ ነውና ለቅቄልዎታለሁ አሉዋቸው:: ጃንሆይም፣ በአገራችን ሁለት አውራ ዶሮዎች ሲጣሉ፣ ዋናው መጥቶ ካልገላገላቸው ይተላለቃሉና መሔድ አለብን አሉዋቸው:: አይሆንም ይተዉ ቢሏቸው፣ የለም እንሔዳለን አሉ:: በዚህ ጊዜ ሮበርት ኬኔዲ በአውሮፕላን መጣ:: "አሥመራ ያለው ቃኘው እስቴሽን የሚያገለግለን ለመቼ ነው? ያን ያህል መስኮብ እየፎከረብን እያለ የመገናኛውን መቋቋም የፈቀድነው ለመቼ ሊያገለግለን ነው? እንዲህ ያለ ችግር ሲመጣ ባይሆን አያገናኘንም ወይ?" አልኳቸው:: ጃንሆይም ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉን "ሒድና በሥርዓት ጠይቀው፣ ከዐቢይ ጋር አሥመራ አገናኘን በለው" አሏቸው:: ከዚያ የጆን ኤፍ ኬኔዲ ታናሽ ወንድም ሮበርት ኬኔዲ አካባቢው ባይገኝም፣ የላይቤሪያው ኃላፊ ተፈልጎ ተጠይቆ በሊቢያ በኩል ወደ አሥመራ ተደውሎ ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ከጄኔራል ዐቢይ ጋር ግንኙነት አደረጉ:: "አንተ ለመሆንህ ምልክት ስጠኝ" ብለው ጄኔራል ዐቢይ ጠየቁ:: ጸሐፊ ትዕዛዝ ሳውዲ ሔደው ሳለ የተባባሉትን ንግግር ከተለዋወጡ በኋላ፣ ለመፈንቅለ መንግሥት የተነሣው ክብር ዘበኛ መሆኑን፣ የጃንሆይ ደጋፊ ደግሞ ጦር ሠራዊት መሆኑን ሰማን:: ከዚያ ወደ አሥመራ ኑ አሉን::[35]

ስለሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ተሳትፎ ንጉሡ ያወቁበትን ሁኔታ ደግሞ በተጠቀሰው መጽሐፋቸው ካፒቴን ዓለማየሁ አበበ እንዲህ ብለዋል::

---

[34] ቢትወደድ አስፍሐ

[28] ዝኒ ከማሁ

ሞኖሮቪያ አውሮፕላን ጣቢያ ጧት ላይ እንዳረፍን የአገሪቱ ፕሬዚዳንት ዊሊያም ተብማን ለጃንሆይ የክብር አቀባበል አድርገውላቸው "ግርማዊ ሆይ በሚያስፈልግዎ ሁሉ ለመርዳት ዝግጁ ነኝ" ብለው ወዳጅነታቸውን ገለጹ። የፕሬዚዳንት ኬኔዲ ታናሽ ወንድም ሴናተር ኤድዋርድ ኬኔዲ አፍሪካን ጎብኝተው ወደ አገራቸው በመመለስ ላይ ስለነበሩ እዚያው ሞኖሮቪያ ከፕሬዚዳንት ተብማን ጋር አብረዋቸው ስለነበሩ ወደ ጃንሆይ ቀረብ ብለው በኔስ በኩል የምረዳው ምንድነው? ብለው ጠየቁ። ጃንሆይም አሥመራ በነበረው ቃኘው ጣቢያ በኩል እንደራሴው ጀኔራል ዐቢይ አበበን በሬዲዮ እንዲያቀርቡላቸው ጠየቋቸው። ሴናተሩም ጥያቄያቸውን ተቀብለው ዘመኑ ባስገኘው መገናኛ አማካኝነት ጀኔራል ዐቢይን አቀረቡላቸው። እርሳቸውም አሥመራ ሰላም መሆኑንና በሱዳን በኩል እንድንበር ሐሳብ አቅርበው በዚሁ ስምምነት ተደረሰ። እኛ ም በየት በኩል አድርገን እንደምንበር ዐወቅን።

ከብራዚል ስንነሣ ወደ አዲስ አበባ እንድንመለስ ብቻ ነበር የተነገረን። እኔ እንደመሰለኝ ግን ወደ ኢትዮጵያ ተጠግተን በጐረቤት አገር ሆነው ሁኔታውን ለመከታተል ነበር። ሴናተር ኤድዋርድ ኬኔዲ ባደረጉት ዕርዳታ ከባዱ ጉዳይ ተቃለለ። ስለዚህም ከሞኖሮቪያ ተነሥተን ወደ ቻድ ዋና ከተማ ፎርት ላሚ /እንጃሜና/ አመራን።

በዚህ ጉዞ በእኔ ላይ በግል የደረሰና ለየት ያለ ነገር ነበር። ይኸውም ከብራዚል ሪሲፌ ምዕራብ አፍሪካ በመመለስ ላይ ፎርት ላሚ /እንጃሜና/ ስንቃረብ፣ የአውሮፕላኑ የሦስተኛ ሞተር ካንዴላ በትክክል እንደማያቃጥል፣ *ኢግኒሽን አናላይዘር* በሚባል መለኪያ አማካኝነት ተረዳን። ይኸንንም ሁኔታ አሜሪካዊው ሜካኒክ /ፎርት ላሚ/ እንጃሜና እንዳረፍን ቤንዚን እስኪሞላና ሌሎችም አገልግሎቶች እስኪመረመሩ ድረስ የአንድ ሰዓት ጊዜ ስለሚኖረን በዚያኑ ጊዜ አጠብቀዋለሁ ብሎ አማክሮኝ ተስማምተን ነበር።

እኔም መሬት እንዳረፍን ከሠላሳ አምስት ሰዓት በላይ ስላልተኛሁ እንቅልፍ ጥሎኝ አውሮፕላኑ ውስጥ ወንበሩ ላይ ጋደም አልኩ። ተረኞቹ አብራሪዎች ካፒቴን ግሪንና ረዳቶቹ ሁሉ ቦታቸውን ይዘው ይጠባበቃሉ። መካኒኩም አውሮፕላኑ ክንፍ ላይ ወጥቶ ሥራውን ጀምሮ ጃንሆይ በመስኮት ያዩትና "ወደ አገራችን ለመመለስ ቸኩለን አሜሪካዊው ምንድነው የሚጎረጉረው? ለዓለማየሁ ንገረው" ብለው የግቢ ሚኒስትር የነበሩት አቶ ተፈራ ወርቅን ይልካሉ። እሳቸውም ይቀሰቅሱኝና "ፈረንጁ ምንድነው የሚሠራው? ሊያዘገየን ነው ወይ? ተነስና የሚሠራውን ተመልከት" ይሉኛል። በእንቅልፍ ላይ ነበርኩና "ቀላል ነው የሚዘገይ አይደለም ሥራውን ዐውቀዋለሁ" ብዬ ተመልሼ ተኛሁ፣ ለሁለተኛ ጊዜ መጡና "ተነሥና የሚሠራውን ተመልከት ተብለሃል" ይሉኛል። "እሺ ቀላል ነው" ብዬ እንቅልፌን ቀጠልሁ። በሦስተኛ ጊዜ ግን ከራስ መስፍን ጋር መጥተው አምርረው ተቆጡና "ተነሥ እኮ ነው የምንልህ!" ብለው ያወዛውዙኛል። ነገሩ እንደከረረ ገባኝና ተነሥቼ ከአውሮፕላኑ ወርጄ ጉዳዩን እንደማያውቅ ሆኜ፣ "ምን እየሠራህ ነው?" ብዬ ሜካኒኩን ጠየቅሁት። "የተነጋገርነውን እያስተካከልኩ ነበር ጨርሻለሁ" ብሎ ሞተሩን ዘጋና ወረደ። ለካስ ጉዳዩ ሆን ተብሎ ጃንሆይን ለማዘግየት

የታሰበ መስሏቸው አብረዋቸው የነበሩትም ሁሉ የሥጋታቸው ተካፋዮች ሆነው ኖሯል።

አሥመራ ደርሰን ሆቴል እንዳረፍን ከካዴትነት ጊዜ ጀምሮ የምንተዋወቅና በዚሁ ጉዞ ላይ አብረን የነበርን የጃንሆይ ዘመድ የነበረው፣ የክቡር ዘበኛው ኮሎኔል መርዕድ ግዛው (በኋላ ብርጋዴር ጄኔራል) ከአረፍኩበት ሆቴል ይመጣና፣ ‹እንጃሜና ላይ የደረሰው ሁኔታ ሆን ተብሎ ጉዞውን ለማዘግየትና አንተም በዐድማው ውስጥ እንዳለህበት ስለአስጠረጠረህ በዐድማው የሌለህበት መሆንህን ጉዳዩን አብራርተህ ጽፈሕ ጃንሆይን ይቅርታ ጠይቅ። እኔ ግን እንደሌለህበት አምናለሁ። ይህንንም የምነግርህ በወንድምነቴ ነው› ብሎ ያጫውተኛል። ‹ታዲያ ካመንክኝ አንተ ለምን አታስረዳልኝም?› አልኩት። ቀጥዬም እንደዚህ የመሰለውን ጉዳይ መጻፍ ከባድ ነው። በዐድማው እንዳለሁበት ያስመስላልና ስጠየቅ በቃል እመልሳለሁ ብዬ ቁርጡን ነገርኩት። አሥመራ ስንገባ ደግሞ የኮሎኔል ወርቅነህ ሲገርመኝ እኔም የመጠርጠሩ ጽዋ ደረሰብኝ። ከእርሱ ጋር ስለሽጉጥ የተነጋገርነውን ቢያውቁማ ኖሮ ብዙ ፈተና ይደርስብኝ ነበር።

በማግሥቱም ወደ አዲስ አበባ ስንበር የምንጓዝበትን ከፍታ፣ በየት አቅጣጫ እንደምናርፍና የአዲስ አበባ አውሮፕላን ጣቢያው በሚገባ እንደሚጠበቅ በሬዲዮ ይተላለፍልን የነበረውን መረጃ ሁሉ ጃንሆይ ወደነበሩበት ልዩ ክፍል ገብቼ አስረዳኋቸው። ዘመዳቸው ነኝ የሚለው ኮሎኔል የነገረኝን ግን አላነሣሁም፤ እሳቸውም አልጠየቁኝም። ከዚያ በኋላ ጉዳዩ ተነሥቶ አያውቅም። ከዚያም ቤንዚን ሞልተው ወደ ካርቱም መብረር ጀመርን። ከዚያም ከአዲስ አበባ ጋር በኢትዮጵያ አየር መንገድ ሬዲዮ አማካኝነት ግንኙነት ተመሥርቶ ለጃንሆይ ሁኔታውን ለማስረዳት ጄኔራል መርዕድ መንገሻ ቀረቡ። ጃንሆይም ከክፒት ድረስ በመምጣት የሬዲዮኑን ማዳመጫ ከመቶ አለቃ ኃይሌ (የአውሮኘላኑ የሬድዩ መገናኛ ኃላፊ) ተቀብለው፣ ከጄኔራል መርዕድ ጋር ተነጋገሩ። ሁኔታውን ጃንሆይ እየጠየቁ እነማን እንደሆኑ የስም ዝርዝር ሲነገራቸው፤ በመጀመሪያ መንግሥቱ ከወንድሙ ገርማሜ ጋር ሲባሉ፣ ብዙም አልተደነቁም። ቀጥሎም ጄኔራል ጽጌ ዲቡ ሲባሉ፣ አሁንም አልተገረሙም። አስከትሎም ወርቅነህ ሲሏቸው የቱ ወርቅነህ? ብለው በመገረም ሲጠይቁ ወርቅነህ ገበየሁ ሲባሉ "የእኛ ወርቅነህ!" አሉ፣ "አዎን" ብለው ሲመልሱላቸው የሬዲዮ ማዳመጫውን አውልቀው ጥለው ሌላ ነገር ሳይናገሩ ወደ ማረፊያቸው ተመለሱ። እኔም የመቶ አለቃ ኃይሉን ‹ምንድነው ጃንሆይን ቅር ያሰኛቸው› ብዬ ስጠይቀው፣ ‹ወርቅነህ ገበየሁ በጉዳዩ ላይ እንዳለበት ስለሰሙ ነው› አለኝ።

ያን ጊዜ ከአዲስ አበባ ከመነሣታችን በፊት ከሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ ጋር መንገድ ላይ ተገናኝተን አንድ የተናገረኝ ነገር ትዝ አለኝ። ጃንሆይ ወደ ውጪ አገር በሚያደርጉት ጉብኝት አብዛኛውን ጊዜ የደህንነት ኃላፊ ሆኖ አብሯቸው የሚጓዝ እሱ እንደመሆኑ መጠን፤ በሔድንበት አገር ሁሉ ሌሊትም ይሁን ቀን ከእርሳቸው እርቆ አያውቅም። እንዲያውም ባረፉበት ሥፍራ ሁሉ መኝታ ክፍሉ ከጃንሆይ ቀጥሎ ነው። ብራዚል ረጅም ጉዞ እንደመሆኑ ከእርሳቸው አይለይም ብዬ በማሰብ፣

ወርቅዬ አብረን ነዋ የምንሔደው ብዬ ስጠይቀው፣ አይ እኔ አልሔድም፣ ሌላ ሥራ አለኝ ብሎ ሲመልስልኝ ቀደም ብዬ የጠየኩትን አስታወስኩት:: ይኸውም ጃንሆይ ለጥቂት ሰዎች ሽጉጥ ሸለሙ ሲባል ስሰማ እኔም እንዲያስጠኝ ደጋግሜ እጠይቀው ነበር:: እርሱ ቆይ እያለ ብዙ ቃል ስለገባልኝ በዚህ አጋጣሚ አሁንም ስጠይቀው፣ "እናንተ እንኳን ሽጉጥ ጠመንጃም ቢሰጣችሁ ምን ታደርጉበታላችሁ!" ሲል በጣም ደነገጥኩ:: እኔ ሽጉጥ የፈለኩት የልጅነት ትዝታ ስለነበረኝ ነው:: ይህ የሌ/ኮሎኔል የዐመፅ ተባባሪነት ሲከሰት ከጉዞው የቀረው ለዚህ ይሆን ብዬ ብጠራጠርም ለግርማዊነታቸው የነበረው አክብሮትና ፍቅር ለዚህ ዓይነቱ ድርጊት ፈጽሞ የሚያበቃው አልመሰለኝም ነበር:: ግን "የሰው ሆዱን የወፍ ወንዱን የሚያውቀው የለም" ይባላል አይደል! ወደ ካርቱም በመብረር ላይ እያለን፣ ጃንሆይ በኤርትራ የፀጥታው ኃላፊ የነበሩትን ደጃዝማች አስጋኸኝ አርአያን ካርቱም መጥቶ ሁኔታውን ያስረዳን ብለው አዝዘው ስለነበረ ካርቱም ላይ መጥተው ጠበቁን:: የደጃዝማቹ ካርቱም ላይ መጠበቅ እጅግ አሳሳቢ የአገር ጉዳይ በመሆኑ፣ በዚያን ጊዜ አሥመራ በሚገኘው አውሮፕላን ማረፊያ የነበረው ዲሲ ሦስት አውሮፕላን ምንም በቂ ጠቋሚ መሣሪያ ባይኖረውም፣ ካፒቴን አዳሙ መድኅኔ ጠንቃቃ በመሆኑ ደጃዝማችን አሳፍሮ በሌሊት ካርቱም ገብቶ ጠበቀን:: በትዕዛዙም መሠረት ደጃዝማች አስጋኸኝ አርአያ ለጃንሆይ ቀርበው አስረዱ::

ሱዳን ስንደርስ ጄኔራል አቡድ ተቀበሉን:: "ጦሩ የርስዎ ነው ይዘዙን እንዘምታለን» አሏቸው:: እሳቸውም "እግዚአብሔር ይስጥልን እናመሰግናለን::" ብለው በአየር ማረፊያው ግሩም ግብዣ ተደርጎልን ሳለ አንድ እንግሊዛዊ የቀድሞ አማካሪያቸው የነበረ መጥቶ ይህ ሙከራ እኮ መንግሥቱ ከፍፃሜ አደረሱት እንጂ ጥንስሱ የጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ ነው አሏቸው:: እሳቸውም ቆጣ ብለው ሙሉጌታን አንተ አታውቀውም፣ ከባድ ሰው ነው፣ በማያዛልቅ ነገር ውስጥ አይገባም" አሉት::[36]

ካፒቴን ዓለማየሁ ንጉሡ በመጨረሻ ወደ አሥመራ የሔዱበትን አኳኋን የገለጹት ደግሞ

ግርማዊነታቸው ጠቅላላውን ሁኔታ ከፀጥታው ኃላፊ ከደጃዝማች አስጋኸኝ ከተረዱ በኋላ፣ በደህንነት ኃላፊነት አብሮን የተጓዘው ኮሎኔል ሰለሞን ከድር የኮሎኔል ወርቅነህ ወዳጅ መሆኑ ይታወቅ ነበርና፣ በግልበጣው እሱም ስለተጠረጠረ ካርቱም ቀርቶ ደጃዝማቹ በመጡበት በዲሲ ሦስት አውሮፕላን ወደ አሥመራ እንዲሔድ ተደርጐ፣ እኛም በኮሎኔሉ ምትክ ደጃዝማቹን ይዘን ወደ አሥመራ አመራን::

በማለት ነው:: በመንገድ ላይ ስለነበረው ሁኔታ ቢትወደድ አስፍሐ እንዲህ ይላሉ

በዚህ ጉዞ አቅጣጫ ላይ ከአገር ቤት ለጃንሆይ ይደርሱ ከነበሩት የቴሌግራም መልእክት፣ የበጌምድርና ሰሜን ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ የነበሩት የደጃዝማች ክፍሌ ዳዲ ቴሌግራም ይገኝበታል:: የመልእክቱ ፍሬ ሐሳብም፣ "ጃንሆይ በሌላ በኩል እንዳይሔዱ፣ በቀጥታ ወደ ጎንደር እንዲመጡ፣ ወደ ሌላ ቢሔዱ እጅዎን ይዘው ይሰጡዎታል" የሚል

[36] ቢትወደድ አስፍሐ

ነበር፡፡ በሌላም በኩል ጄኔራል ዐቢይ አበበ፣ በኤርትራ ፌደራል ግዛት የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት እንደራሴ የነበሩት፣ ግርማዊነታቸው በአሥመራ በኩል እንዲገቡ ቴሌግራም አስተላለፉ፡፡ አሥመራ አውሮፕላን ማረፊያ እንዳረፍን ጄኔራል ዐቢይ አበበ ወደ አውሮፕላኑ ውስጥ ገብተው እጅ ነሥተው ከተነጋገሩ በኋላ፣ ግርማዊነታቸው ከአውሮፕላኑ ብቅ ሲሉ እንኳን ደህና ገቡ በማለት አውሮፕላን ማረፊያ ተገኝቶ የነበረው የአሥመራ ከተማ ነዋሪ ሕዝብ ታላቅ የደስታ አቀባበል አደረገላቸው፡፡ ዕልልታውንም አቀለጠው፡፡ እኛም አውሮፕላናችንን እንደተለመደው ፈታተሽንና አዘጋጅተን እንዳበቃን ለአዳር ወደ ከተማ ገባን፡፡[37]

ንጉሡ አሥመራ በገቡ ዕለት ማታም በኢትዮጵያ ሬድዮ ጣቢያ ከዚህ ቀጥሎ ያለው የንጉሡ ቃል ለአሥመራ ሕዝብ ተነገረ፡፡

---

[37] ቢትወደድ አስፍሐ

## ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አሥመራ በደረሱ ጊዜ

## ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሬድዮ ያሰሙት ቃል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አገሩን ታላቅ ያሰኘው ፣ የሕዝቡ ታማኝነትና ቀራጥነት ነው ። ይልቁንም ሕዝቡ አገሩን መልከም ስም ሰጥቶት በዓለም እንዲታወቅ ያደረገው በቆራጥነት የአምስት ዓመት አርበኝነትና በደተኝነት የተፈጸሙት ቀራጥ ሥራዎች ቢሆን ይህንኑ ጀብዱ በመላው ዓለም የማያደንቅ የለም ።

አሁን አገራችን ወደ ሥልጣኔ እርምጃ እያደረገች በምትገሰግስበት ጊዜ በአዲስ አበባ ብቻ የተነሣው ሁከት አገራችንን ወደ ኋላ ለመመለስ ከሚያስቡ ጋር የተጋጠመ ይመስላል ፤ አንድ ጠብታ ደም ማፍሰስ ወይም ሁከት ማንሣት መላውን ኢትዮጵያ ከታላቅ ፈተና ላይ መጣል እንደሆነ ምን ? በየጊዜው የሚደርሰው የሬድዮ ወሬ ፣ የክብር ዘበኛና ፖሊሶች ናቸው ይባላል ። ይህንንም ማንኛውም ቀጥር የሆነ ሰው ሊያምነው አስቸጋሪ ነው ። ከሕዝባችንም ውስጥ የተመረጡበት ሥራ እጅግ ከባድ የሆነ ኃላፊነት ያለው ነው ። መላው ኢትዮጵያ በጸጥታ ላይ ሆና በአዲስ አበባ ሁከት ስለፈጠሩ በጣም አሳዝኖናል ። በአሁኑ ጊዜ አብዛኛው የአፍሪቃ ክፍል ነፃ አገሮች ነፃ በሰጠበት ፣ ከነዚሁ የአፍሪቃ አገሮች የደቡብ አሜሪካ ሕዝብና መሪዎች ጋር መተዋወቅና መዘመድ ፣ እንደዚሁም ቃል በቃል መነጋገር ለሀገራችን ታላቅነትና እድገት ይረዳል ብለን በማሰብ ጀምረን የነበረውን ጉዞና ቀጠሮ ሰርዘን ፣ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰን በመምጣት አሁን አሥመራ ደረስን ።

ከክብር ዘበኛ ከፖሊስም ወይንም ከሁከት አንሺዎቹም ቢሆን ወደ እኛ መጥቶ ሊያስረዳን የሚፈልግ ሰው ቢኖር ፣ ተቀብለን እናነጋግረዋለን ።

ሁከት አንሺዎቹን በመቃወም መንግሥታችንና ሕዝባችንም እንደዚሁም የሀገሩን ፀጥታ ለማስከበርና ለመጠበቅ የጦር ሠራዊቶቻችንና የአየር ኃይላችን ሕዝባችንም የሚያደርገውን ትግል ስምተናልና መልካም እየሆነ ነው ። እስከዛሬ ድረስ ሁከቱን ለመደምሰስ ትግላቸውን ቀጥሉ ።

መላውስ ኢትዮጵያ በሰላም ረግቶ አዲስ አበባ ለምን የሁከት ምንጭ ይሆናል ? ሁከት አንሺዎቹም ወገናቸው በማስመሰል የተወደዱ ልጆችን የአሊጋ ወራሻችንንና እንደዚሁም ከመኳንንቶቹ በጣም የምናምናቸውን ሰዎች ስም እያነሱ ፣ የሚያወሩትና የሚያስወሩት ወሬ በፍጹም ሐሰት መሆኑንና ይኸውም ሁከቱን ለማጋጋን የተደረገ ሥራ መሆኑን ተገንዝበናል ።

በጠቅላላው በአጭሩ ለሁከት አንሺዎቹ የምንነግራችሁ ለታላቋ ኢትዮጵያና ሕዝቧ እንደዚሁም ለታሪኳ እኛና መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የደከምንበትን በማስታወስ ፣ በዚሁ ሁከት ምክንያት የውጭ እጅ ገብቶ ኢትዮጵያን እንደገና ከአደጋ ላይ እንዳያደርሳት በማሰብ አሁኑኑ ደም መፍሰሱ እንዲቀር ይሁን ። እንደምታውቁትም ያሁኑ ነገር ርኅራኄና ፍርድ ልማዳችን ነው ፤ በተረፈ ዝርዝሩን ሁሉ እዚያው አዲስ አበባ በደረስን ጊዜ እናስረዳችኋለን ።

## የቅዳሜው ትግልና ዕልቂት

የክብር ዘበኛ መምሪያውን የተቆጣጠረው የጦር ሠራዊት ክፍል ከ፴፪ኛ ሻለቃ አንድ የመቶ ጦር ተጨማሪ በማድረግ በታንክ ታጅቦ ወደ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት አመራ:: ይህ እንደሆነም፣ በዚያው አካባቢ ይጠባበቅ የነበረው የክብር ዘበኛ ሠራዊት በኃይል ተከላክሎ በጦር ሠራዊቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አደረሰ:: ከምከታውም በኋላ ጦር ሠራዊቱ ለድጋፍ ያሰለፈው ሰላማዊ ሕዝብ በማርቆስና በዋናው በር በኩል እየጨፈረና "ኃይለ ሥላሴ ድረስ በነፍሴ" እያለ እየዘመረ መጣ:: በእርግጥ ሁኔታው አሳዛኝ ገጽታ ነበረው:: ሕዝቡ ከበስተጀርባው የነበረውን ምስጢር አላወቀውም ማለት እችላለሁ:: ምክንያቱም፣ ከሕዝቡ በስተጀርባ ጦር ሠራዊት ይከተላል:: ከፊት ለፊት የክብር ዘበኛ ለመከላከል ተሰልፏል:: ከቤተ መንግሥቱ በስተምዕራብ በኩልም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጦር ትምህርት ቤት ሠራዊት ተጠግቷል:: በጥበብ መውጣት ባይቻል ኑሮ ይህ በድጋፍ ሰልፍ ስም እየተነዳ የመጣው ሰላማዊ ሕዝብ ከፊትም፣ ከኋላም፣ ከጐንም እንዲንቀሳቀስ የተደረገው በእሳት መሐል ነበር:: በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥትን ለመያዝ ሲባል በዚህ አኳኋን በጦር ሠራዊቱ አለቆች በኩል የተወሰደው እርምጃ ከታሪክ ወቀሳ የሚያድን አልነበረም:: ስለዚህ እልቂቱ የተፈራውን ያህል ሳይደርስ በጥንቃቄ ለመውጣት በክብር ዘበኛ በኩል ትዕግሥት መደረጉ በዚህ አጋጣሚ መጠቀስ ያለበት አስተውሎት ነው ብዬ አምናለሁ::

እንዲህ ከበስተጀርባ ጦር እየተከተለው የመጣው ሕዝብ አጣብቂኝ ውስጥ ገብቶ እንዳይጨፈጨፍ ትዕግሥት እየተደረገ ሳለ፤ ከጦር ሠራዊቱ በኩል፣ የሻምበል ደረጀ ኃይለ ማርያም ክብር ዘበኛን የሚደግፍ መስሎ፣ የገነተ ልዑል ቤተ መንግሥትን በር በታንክ በኋላ ማርሽ በመጣስ፣ ታንኩን እስከ ቤተ መንግሥቱ ሰንደቅ ዐላማ መስቀያ ይዞት ገባ:: ከገባ በኋላም፣ በታንኩ አናት አንገቱን ብቅ በማድረግ፣ በጄኔራል መንግሥቱ ላይ የስድብና የዘለፋ ውርጅብኝ አወረደ:: ስድቡንና ዘለፋውን ያወረደው የድምፅ ማጉያ በመጠቀም ነው:: የሻምበል ደረጀ በመጀመሪያ፣ «ክብር ዘበኛ እጅህን ስጥ፣ ጄኔራል መንግሥቱ የጃንሆይን መንግሥት ከድቷል፣ አታሎዋችኋል::» ካለ በኋላ ጄኔራል መንግሥቱን፣ «ከአልጋ ቢሉህ አመድ ይሻለኛል አልክ? አንተ የድሃ ልጅ! ያ ድህነት ይሻልሃል!» በማለት ዘለፋ አወረደ:: በዚህ ጊዜ፣ ሁኔታውን በቦታው ሆኖ አይቻለሁ ያለኝ የክብር ዘበኛ የሁለተኛ ኮርስ ተካፋይ የነበረውና በኋላ (በእጩ መኮንኖች ተካሒዶ በነበረው ዐድማ ምክንያት ከካዴቱ ተሰናብቶ) በሲቪል ሥራ ተሰማርቶ እንዳለ በታኅሣሡ ግርግር ተሳታፊ ነበር በሚል ታስሮ የነበረው አቶ ነጋሽ ድንበሩ እንደገለጸልኝ ጄኔራል መንግሥቱ "ይህ ውሻ" ብለው በመናደድ ከአንድ አጠገባቸው ከነበረ ወታደር ኤም ዋን ጠመንጃ ነጥቀው የሻምበል ደረጀን ገደሉ::[38] ልዕልት ሶፊያ እንዳጫወቱኝ ግን፣ ገዳዩ ጄኔራል መንግሥቱ ሳይሆኑ ሌላ ሰው ነው::

---

[38] አቶ ነጋሽ በጥበቃ ሥር የነሩት መኳንንት ሲረሸኑ፤ በርሸናው የተሳተፈና ከመፈንቅለ መንግሥቱ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ስለታሠረ ሁለታችንም በዓለም በቃኝ በነበረበት ጊዜ የነገረኝ ነው::

አቶ ነጋሽ የሚያክልልን ሌላው ጉዳይ የሻምበል ደረጀ ከላይ በተጠቀሰው ሁኔታ የገነተ ልዑል ቤተ መንግሥትን በር በታንክ ጥሶ በገባ ጊዜ፣ አንድ ሌላ ታንክ ተከትሎ ይመጣና መትረየሱን ወደ ቤተ መንግሥቱ በመደገን ስለመተኮሱ ነው። ጀኔራል ጽጌ ዲቡም «እንዝርቱን ምታው! እንዝርቱን ምታው!» እያሉ ቢጮሁ ወታደሩ አልገባው ስላለ፤ ጀኔራል መንግሥቱ እንዳደረጉት ከአጠገባቸው ከነበረ አንድ ወታደር ኤም ዋን ጠመንጃ ነጥቀው ከታንኩ ላይ ተጠምዶ የነበረውን መትረየስ የጥይት መጉረሻውን በመምታት ከጥቅም ውጭ አድርገውታል።

በዚህ መልክ የገነተ ልዑል ቤተ መንግሥትን ለመያዝ ጦር ሠራዊት ጥረት ሲያደርግና፣ የሻምበል ደረጀ ኃይለ ማርያም ታንኩን ይዞ በሩን ጥሶ ሲገባ፤ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህና ራስ እምሩ ከአሜሪካው አምባሳደር ጋር ይነጋገሩ ነበር። አምባሳደሩ ለራስ እምሩ ያመጡት አንድ ደብዳቤ ነበር። ምንም እንኳን አድራሻው ለእሳቸው ቢሆንም፤ የተጻፈው ለጀኔራል መንግሥቱ ነው። የፈረሙበትም ሜጀር ጀኔራል መርዕድ ናቸው። ራሰ እምሩ ሜጀር ጀኔራል መርዕድ በፊርማቸው የላኩትን ደብዳቤ ከአምባሳደሩ ተቀብለው ሲያነቡ፤ መልዕክቱ "ለመገናኘት ፈቃዳችን ነበር። ነገር ግን፣ ገርማሜና የሻለቃ አሰፋ ለማ በአሜሪካን ኤምባሲ ተገናኝተው በርስዎ በኩል የተላከልን ቃል ተስፋ የሚሰጥ ሆኖ አላገኘነውም። ስለዚህ ተገናኝተን ለመነጋገር አንፈቅድም።" የሚል የመጨረሻ ስንብት የያዘ ጽሑፍ ነበር። አምባሳደሩ መልእክቱን ባደረሱበት በዚህ ሰዓት በአካባቢው ተኩስ ተፋፍሞ ነበር። ስለዚህ ድንጋጤ ስለያዛቸው ጉዳት እንዳይደርስባቸው ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ሊጠለሉበት ወደሚችሉበት ሥፍራ ወስዶ፤ በአቶ ከተማ ይፍሩ ቢሮ በመስኮት አዘልሎ በማውጣት ሸኝቶ ሰደዳቸው። በዚህ መካከል የጦር ሠራዊቱ ግፊት እያየለ መጣ። ስለዚህ በጥበቃ ሥር የነበሩትን የዐፄ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ከየነበሩባቸው የተለያዩ ክፍሎች አውጥተው፤ ሁሉንም አንድ ላይ ወደሚይዝ ወደ አረንጓዴ ሳሎን እንዲዛወሩ አደረጉ።

ይህ እርምጃ ስለፈጠረው ስሜትና ያስከተለው ውጤት አቶ ነጋሽ ድንበሩ የሚለው አትኩሮት የሚሻ ነው። ‹‹መኳንንቱ ‹ወደ አረንጓዴ ሳሎን ተዛወሩ የተባልነው ለርሸና ነው› በሚል ግምት፣ ጀኔራል መንግሥቱ ወደ ሳሎኑ ሲመጡ፤ አቶ አምደ ሚካኤል ደሳለኝ (የፕሮፓጋንዳ መሥሪያ ቤት ምክትል ሚኒስቴር) ወንበር አንሥተው ጀኔራል መንግሥቱን ሊመቱ ቃጡ፤ ጀኔራል መንግሥቱም "አትለውም?" አሉ። በዚህ ጊዜ በሁሉም ላይ ያልታሰበ ተኩስ ተከፈተባቸው። ከዚያም መሞታቸውን ለማረጋገጥ የማጣሪያ ተኩስ ተደጋግሞ ተካሔደ። በዕለቱ የተረሸኑት የዐፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ባለሥልጣናት የሚከተሉት ነበሩ።

፩ኛ/ ልዑል ራስ ሥዩም የትግሬ ጠቅላይ ገዥ

፪ኛ/ ክቡር ራስ አበበ አረጋይ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢና የመከላከያ ሚኒስትር

፫ኛ/ ክቡር አቶ መኮንን ሀብተ ወልድ የንግድና የፕላኒንግ ሚኒስትር

፬ኛ/ ክቡር ብላታ አየለ ገብሬ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል

፭ኛ/ ክቡር ሜ/ጄ ሙሉጌታ ቡሊ የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስትር

፮ኛ/ ክቡር ሊቀ መኳስ ታደሰ ነጋሽ የፍርድ ሚኒስቴር ሚኒስትር ደኤታታ

፯ኛ/ ክቡር አፈንጉሥ እሸቴ ገዳ የጸጥታ ምክትል ሚኒስትር

፰ኛ/ ክቡር ብላታ ዳዊት እቁበ እግዚ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ደኤታታ

፱ኛ/ ክቡር አቶ አምደ ሚካኤል ደሳለኝ የፕሮፓጋንዳ (የማስታወቂያ) ምክትል ሚኒስትር

፲ኛ/ ክቡር አቶ ገብረ ወልድ እንግዳ ወርቅ የጽሕፈት ሚኒስቴር ሚኒስትር ደኤታ

፲፩ኛ/ ክቡር አባ ሃና ጅማ የጃንሆይ ግምጃ ቤት ሹም

፲፪ኛ/ ክቡር ደጀዝማች ለጥይበሉ ገብሬ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል

፲፫ኛ/ ክቡር አቶ ለማ ወልደ ገብርኤል የመንግሥት ንብረትና የማዕድን ም/ሚኒስትር

፲፬ኛ/ ክቡር አቶ አብዱላሂ ሙሜ የገንዘብ ምክትል ሚኒስትር

፲፭ኛ/ ክቡር አቶ ክብረት አስታጥቄ ባገር ግዛት ሚኒስቴር ረዳት ሚኒስትር ናቸው። በተኩሱ ፲፭ቱ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ሕይወታቸው ሲያልፍ፣

፩. ሐጂ ፋራህ በአገር ግዛት ሚኒስቴር ረዳት ሚኒስትር

፪. ጄኔራል መኮንን ደነቀ የግቢ ምክትል ሚኒስትር በ፲፪ ጥይት ተመትተውና

፫. አቶ አድመው ተሰማ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ልዩ ጸሐፊ ቆስለው ሲተርፉ፤

፬. ራስ አንዳርጋቸው መሳይ የአገር ግዛት ሚኒስትርና

፭. ደጃዝማች በዛብህ ስለሺ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል ምንም ሳያገኛቸው ተርፈዋል፡፡ "ከንፍሮ ጥሬ የሚያወጣው አምላክ" ይባል የለ?

አቶ ነጋሽ ድንበሩ በመኳንንቱ ርሸና እንዲካፈል የሆነበት የራሱ ምክንያት አለው፡፡ በክብር ዘበኛ ጦር መኮንኖች ትምህርት ቤት (ካዴት) የሁለተኛው ዙር ኮርስ እጩ ሠልጣኝ በነበረበት ወቅት በካዴቱ ውስጥ በተደረገው አድማ ግንባር ቀደም ተዋናይ ስለነበር፤ የሦስት ዓመት እሥራትና እሥራቱን ሲጨርስም በኢትዮጵያ መንግሥት መሥሪያ ቤት ሥራ እንዳይዝ ተፈርዶበት ነበር፡፡[39] እንደእሱ ዕምነት ይህ እንዲሆን ከፍተኛ ተፅዕኖ ያደረጉበት ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ (በጊዜው የክብር ዘበኛ ጦር አዛዥ) ነበሩ፡፡ በይግባኙ ላይ ደግሞ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያደረጉብኝ የሚላቸው ራስ አበበ አረጋይን (የመከላከያ ሚኒስትር) ነበሩ፡፡ ሥራ ለመያዝ አቤቱታ በጄኔራል መንግሥቱ አማካኝነት ለጃንሆይ ሲያቀርብም በአባ ሐና ጅማና በአቶ መኮንን ሀብተ ወልድ ሲዘጋበት ጄኔራል መንግሥቱ ድጋፋቸውን ስለሰጡት፤ ይቅርታ ተደርጐለት ይፋዊ የመንግሥት ሥራ መያዝ እስቲፈቀድለት ድረስ በክብር ዘበኛ መሥሪያ ቤት በሒሳብ ክፍል ሲሠራ እንዲቆይ በጊዜያዊነት ቀጥረውት ይሠራ ስለነበር፤ በግርግሩ ጊዜ ከጄኔራል መንግሥቱ ጎን ሆኖ የከረመ በመሆኑ በግድያው ተካፈለ፡፡

---

[39] *በዚህ ወቅት ነጋሽ ድንበሩ በክብር ዘበኛ ካዴት ሁለተኛው ኮርስ ውስጥ እያለ ወደኮርያ ዝመቱ ሲባል፤ እሱና ዕጩ መኮንን (ካዴት) ናደው ፈጠነ እንዴ ለምንድን ነው ለኢምፔሪያሊስት ድጋፍ ኮሚኒዝምን የምንወጋው በማለታቸው፤ ድርጊታቸው የኮሚኒዝም ስርፀት እንደተከሰተ አስቆጥሮባቸው ሦስት ሦስት ዓመት እንዲታሰሩ ተደረገ፡፡ ሲፈቱም በመንግሥት ሥራ እንዳይቀጠሩ ሆነ፡፡*

## ንጉሡ ከአሥመራ ወደአዲስ አበባ

ቅዳሜ ታኅሳስ ፰ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. በመፈንቅለ መንግሥቱ ሞካሪዎችና በዘውድ ጠባቂው ወገን ትግሉ እንዲህ ግሞ የመጨረሻው ደረጃ ደርሶ እያለ፣ ንጉሡ ከአሥመራ ወደአዲስ አበባ ጉዞ ጀምረው ነበር። ከአሥመራ ወደ አዲስ አበባ ስለተደረገው ጉዞና በአዲስ አበባ ለንጉሡ ስለተደረገው አቀባበል ሲያትቱ ካፒቴን ዓለማየሁ እንዲህ ይላሉ።

> ... በማግሥቱ ቅዳሜ ሁኔታው ከተረጋጋ ወደ አዲስ አበባ ለመብረር እንድንዘጋጅ ከቤተ መንግሥት ተነገረኝ። በዚያን ጊዜ ፖይለት ብቻ ሳይሆን እንደ አገናኝ መኮንን ሆኜ ነበርና፣ የፕሮቶኮል ክፍሉን ትእዛዝና ፕሮግራም ለአሜሪካዊያኑ ፖይለቶች አስተላልፍና አስተባብር ነበር። በዚህም መሠረት፣ ትእዛዙን ለአሜሪካኖቹ ፖይለቶች ስነግራቸው፣ እኛ ቤተሰቦችና ልጆች አሉን። በእናንተ ችግር ውስጥ መግባትና ከአደጋ ላይ መውደቅ አንፈልግም። ስለዚህ የአዲስ አበባ ሁኔታ በሚገባ የተረጋጋ መሆኑን ሳናረጋግጥ መብረር እንደማንችል ንገርልን አሉኝ። ሥጋታችሁ ትክክል ነው። ግን ንጉሡ ለሕይወታቸው ሳይሳሱ እኛ እንዴት እናመነታለን? ደግሞም ሁኔታው አስተማማኝ ሳይሆን እንሒድ እንደማይሉን እርግጠኛ እንሁን። ይልቅስ ከጥርጣሬና ፍርሀት አእምሮአችንን ነፃ እናድርገውና ትእዛዛቸውን ለመፈፀም እንዘጋጅ ብዬ አሳመንኳቸው። በኋላ እንደተረዳሁት ድንገት የአየር መንገድ አብራሪዎች ለራሳቸው ደህንነት ሲሉ አንበርም ቢሉ በሚል አስተሳሰብ ከአየር ኃይሉ አንድ አውሮፕላን በምሥጢር ተልኮ እንደ ነበር ሰማሁ።
>
> በማግሥቱም ቅዳሜ ከአሥመራ ስንነሣ ደማቅ አሸኛኘት ተደረገልን። ከአየር መንገዱም ጋር የሬዲዮ ግንኙነት ጀምረን በተላለፈልን መልእክት መሠረት አዲስ አበባ ገብተን ለደህንነት ሲባል በስተምዕራብ አቅጣጫ መጥተን አረፍን። ሞተሮቹን አጥፍተን መሰላሉ እንደቀረበ እኛም ደስታችንን ለመግለጽ ጃንሆይ ወደ ነበሩበት መቀመጫ ስናመራ ልዑል አልጋ ወራሽ ገብተው ከጃንሆይ ጫማ ወድቀው ሲማጸኑ ሰማን። ጃንሆይም ከፍ ባለ ጽምፅ፣ ወይድ ወዲያ! ሲሉ እልፍኝ አስከልካዩ እኛን ወደ ኋላ መለሱን። ከትንሽ ቆይታም በኋላ ተጠርተን ገባንና እጅ ነሥተንና ተመስግነን ተመለስን።

ስለመፈንቅለ መንግሥቱና በወቅቱ ስለነበረው ፖለቲካዊ ሁኔታ ጥናት ያካሔዱ ተመራማሪዎች በበኩላቸው የሰጡት አስተያየትም ከዚህ ብዙም የተለየ አይደለም። ጃንሆይ ስለ መፈንቅለ መንግሥቱ ሰምተው ወደ አገራቸው ሲመለሱ ላይቤሪያ እንደደረሱ፣ በአሜሪካን የአየር ኃይል ዓለም አቀፍ መገናኛ ባለው መርከብ በመጠቀም አሥመራ ካሉት እንደራሴ ከጄኔራል ዐቢይ አበበ ጋር ስለመገናኘታቸው ያትታሉ። ጄኔራል ዐቢይ አበበም በበኩላቸው የአሜሪካንን ቆንስላ በአሥመራ ሬዲዮ ጣቢያ ተጠቅመው ስለ መፈንቅለ መንግሥቱ ጉዳይ መልእክት ለማስተላለፍ ቢጠይቁት የአሥመራው ሬዲዮ አቅሙ ትንሽ በመሆኑ ከአሥመራ ውጭ ሊሰማ

አይችልም መባላቸውንና የቃኘው ጦር ሠፈርን የመገናኛ ዘዴ እንዲፈቀድላቸው ጠይቀው ከጃንሆይ ጋር ግንኙነት ማድረጋቸውን አንዳንድ ምንጮች ይገልጻሉ።

በአሥመራ ያለው የአሜሪካ ቆንሲል ከጀኔራል ዐቢይ ጋር በእንዲህ ዓይነት ትብብር ውስጥ ሲገኝ በአዲስ አበባ ያለው የአሜሪካ አምባሳደር ግን መጀመሪያ ገለልተኛ አቋም ይዞ ነበር። ይህን የገለልተኛነት አቋም እንዲይዝ ካደረጉት ምክንያቶች ሁለቱ የሚከተሉት ነበሩ። አንደኛ አልጋ ወራሽ መፈንቅለ መንግሥቱን ደግፈው ዐዋጅ መናገራቸው ድምጻቸውና የትንፋሽ አወራረዳቸው ምንም ተፅዕኖ ሳይኖርበት እንደሚያነብ ሰው ኮለል ብሎ የሚወርድ ስለነበረ፤ ሁለተኛ በአሜሪካኖቹ አስተሳሰብ አልጋ ወራሹ ጥሩ መሪ ይሆናሉ ተብሎ ባይገመትም፤ ለውጥ እንዲኖር የሚደግፉ በመሆናቸውና ወጣቱ ትውልድም ይህንኑ ስለሚያምን የአሜሪካ መንግሥት ገለልተኛ አቋም እንዲይዝ ሳይገፋፋው አልቀረም። በነዚህ ነጥቦች የተነሣ፣ የአሜሪካ የማግ /ኤም.ኤ.ኤ.ጂ/ ኃላፊና የጦር አማካሪ የነበሩት ጀኔራል ቸስተር ደጋብር፣ የሳቸው ወታደራዊ ክፍል ባልደረቦች በማንኛውም ወገን እንቅስቃሴ ውስጥ እንዳይገቡ አድርገው ቆይተው፤ በኋላ ግን ከዘውድ ጠባቂው ጋር በመሆን ብዙ ሥራ ሠርተዋል።

## የትግሉ ፍፃሜ

የግራ ቀኙ ሠራዊት ተኩስ ከከፈተና የሞት ሽረት ፍጥርቅ ከተካሔደ በኋላ፣ የክብር ዘበኛ ጦር ተፈታ። የመቶ አለቃ ተክለማርያም ዘረፉ የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች በነበሩበት በገነተ ልዑል በመጨረሻ ሰዓት ስለነበረው ሁኔታ እንደሚከተለው ይተርካል።



የሻምበል ባዬ ጥላሁን

> በገነተ ልዑል ቤተመንግሥት ውስጥ የነበርን መኮንኖች በየፊናችን ለማምለጥ ተገደድን። ማምለጫ ለመፈለግ ሁላችንም ወዲያ ወዲህ እያልን ከቤተመንግሥቱ በስተጀርባ ባለው ቤንዚን ማደያ በኩል ለመውጣት ስንሞክር፣ ሳናስበው ሁላችንም በአንድ አዳራሽ ውስጥ ተመልሰን ተገናኘን። በዚህ ጊዜ የሻምበል ባዬ ጥላሁን፦ "መኮንኖች! ከእንግዲህ ወዲያ ማዕረጋችን ለምንም አይጠቅመንም፣ ከከባችንን አውልቀን ሁላችንም በእኩልነትና በወንድማማችነት ነው የምንተያየው። እኔ ኮከቤን አወልቃለሁ እናንተም የራሳችሁን አውልቁ" ብሎ ከተናገረ በኋላ፣ ለጄኔራል መንግሥቱ ሰላምታ ሰጥቶ የሳቸውንም ማዕረግ አነሣ። የጄኔራል መንግሥቱን ማዕረግ ካነሣ በኋላ፣ "ወንድሞች ከዚች ሰዓትና ደቂቃ ጀምሮ አመራሩን የምይዘው እኔ ነኝ። ከግቢው እኔ እወጣለሁ፤ ችግር ካላጋጠመኝ ምልክት ስሰጥ እናንተም ተከትላችሁ ትወጡና፣ በምሰጣችሁ ምልክት ትመራላችሁ።" የምንሔደው ወደ እንጦጦ ነው፣ በማለት ሲናገር፤ የሻለቃ ዮሐንስ ምስክር ሕይወታቸውን በራሳቸው ሽጉጥ አጠፉ። ጄኔራል መንግሥቱ አዘኑ። የሻምበል ባዬ ወጥቶ በመሔድ ምልክት ሰጠን። እሱን ተከትለን በመሔድ፣ በቀጨኔ መድኃኔዓለም አድርገን ምንም ሳይደርስብን እንጦጦ ማርያም አጠገብ ደረስን።[40]

በሌላ በኩል ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህና የሻለቃ ተሰማ ዋቅጅራ ደግሞ፣ አንድ ኮርስና ያንድ መሥሪያ ቤት አባሎች ስለነበሩ፣ ከቤተ መንግሥቱ አብረው ወጥተው፣ ቀጨኔ መድኃኔዓለም አካባቢ ከመንደር መሐል ላንድ አልባሌ ቤት ባለቤት ሃምሳ ብር

---

[40] የመቶ አለቃ ተክለማርያም ዘረፉ ስለመፈንቅለ መንግሥቱ ብዙ እንደሚያውቅ መጀመሪያ የነገሩኝ የክብር ዘበኛ መኮንኖች ናቸው። በተለይ የሻለቃ ክፍሌ ድንበሩ ሳልሰለች አጥብቄ እንድይዘው ያሉኝ ትክክለኛ መረጃ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ለመቶ አለቃ ተክለማርያም ዘረፉ እና የሻለቃ ክፍሌ ድንበሩ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው።



የሻምበል ባዬ ጥላሁን

ክፍለው ገብተው ተደብቀው አደሩ::[41] የክብር ዘበኛ ወታደሩ ደግሞ ሁሉም ተጠልሎበት ከነበረው እየወጣ ወደ ፖሊስ ጣቢያዎችና ወደ መሳሰሉት የመቆጣጠሪያ ቦታዎች እየሔደ መሣሪያውን ማስረከብ ያዘ::

ኮሎኔል ጃገማ ኬሎ በጊዜው ለበላይ አለቆቻቸው ባቀረቡት የውጊያ ዘገባ፣ የዘውድ ጠባቂው ጦር ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ሲገባ የሚከተለው ሁኔታታ ነበር:: "በስተምዕራብ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጦር ትምህርት ቤት ወደ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት መግባት ጀመረ:: በዚህ ጊዜ ዐመፀኞች ጀኔራል ጽጌ ዲቡ፣ የሻለቃ ዮሐንስ ምስክር፣ የሻለቃ ሽፈራው አያኖና አቶ ገርማሜ ወንዳፍራሽ ሞተው ሲገኙ ሌሎቹ አምልጠው ወደ ቀጨኔ መሔዳቸውን ...›› ሰሙ:: በዚሁ እለት ተኩስ ተጋግሎ ሳለ፤ ልዑል አልጋ ወራሽ ካሉበት ደርሰው ልዑል አልጋ ወራሽን አግኝተው ወደ ግርማዊት ቪላ በመውሰድ ከግርማዊት ጋር እንዳገናኙም ይገልጻሉ:: በዚህ መልኩ የዘውድ ጠባቂው ድሉን በመጎናፀፉ ከአንደኛ ክፍለ ጦር የተንቀሳቀሰው ጦር የፕሮፓጋንዳ ጽሕፈት ቤትንና ባንክን በመያዝ የመፈንቅለ መንግሥቱን ኃይል ደምስሶ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት እንደፀና መሆኑን በኢትዮጵያ ሬዲዮ ጣቢያ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አበሰረ:: በመቀጠልም የሚከተለውን ማስታወቂያ አሠራጨ::

### ማስታወቂያ

ከዛሬ ከታኅሣሥ ስምንት ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ጀምሮ ላልተወሰነ ጊዜ ከምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት እስከ ጠዋት አንድ ሰዓት ድረስ ማናቸውም መኪና ከአዲስ አበባ ደብረ ዘይት በሚወስደው የባቡርና የመኪና መንገድ መተላለፍ በፍፁም ክልክል መሆኑን አስቀድመን እናስታውቃለን:: የኢትዮጵያ ሬዲዩ ጣቢያ ከአሁን ጀምሮ ወደ ፊት የሚሆነውን ማናቸውንም ሁሉ በዚሁ መሥመር የሚያሰማ መሆኑን እንገልጣለን::

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት
የጦር ሠራዊት ጠቅላይ ኤታማጆር ሹም፤
ሜጀር ጀኔራል መርዕድ መንገሻ::

[41] ሻለቃ ተሰማ ዋቅጅራ

# ምዕራፍ ፯

# የመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ ፍፃሜ

## ጦር ሠራዊቱ የድል ባለቤትነቱን አረጋገጠ (ታኅሣሥ ፰ - ፱)

ንጉሡ ከካርቱም አሥመራ እንደገቡ የሰጡት መግለጫ፣ የጦር ሠራዊቱን የድል ባለቤትነት አረጋገጠ። ጦር ሠራዊት «እኛ ወይም ክብር ዘበኛ ይለይልናል» ብሎ የጀመረው ማጥቃት፤ በክብር ዘበኛ መዋጋት አለመፈለግ ታግዞ መፈንቅለ መንግሥቱን በማክሸፍ፣ የዘውዱን ሕልውና አረጋገጠ። ለውጡን አክሽፎ የንጉሠ ነገሥቱ ተወዳጅ ለመሆን በቃ።

የጦር ሠራዊት የአዲስ አበባ ብርጌድ፣ የማዘዣ ጠቅላይ ሠፈሩን በተበተነው የክብር ዘበኛ ሠራዊት ሠፈር ሦስተኛ ሻለቃ ላይ አቋቋመ። ከዚያም በ፲፩ኛ ሻለቃ የክብር ዘበኛ መኮንኖች መኖሪያ ቤቶችን እና መድፈኛ ክፍልን፣ ሐኪም ቤቱንና ግምጃ ቤቱን፣ የክብር ዘበኛ ጋራዥን እና ሁለተኛ ሻለቃን እንዲጠበቅ አደረገ። ፲፪ኛ ሻለቃ ደግሞ፣ ኢዮቤልዩ ቤተመንግሥትን ያዘና በዚያው ለጥበቃ ቆመ። የክብር ዘበኛ የመጨረሻ ጠንካራ አምባ የነበረውን፣ ገነተ ልዑል ቤተመንግሥትን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጦር ትምህርት ቤት እጩ መኮንኖች ሠራዊት፣ ከስምንተኛ ብርጌድ አንድ የመቶ ጦር ተጨምሮለት፣ ሙሉ በሙሉ ተቆጣጠረ። የክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ደግሞ በአንድ ጓድ ጦር እንዲጠበቅ ተደረገ። እነዚህ ቁልፍ ቦታዎች በዚህ አኳኋን በጦር ሠራዊቱ እጅ ገብተው በጥበቃ ሥር እንዳዋሉ፤ አዲስ አበባ ከተማን ከምሥራቅ እስከ ሰሜን ምዕራብ፣ ማለትም ከየካ ሚካኤል አንሥቶ በራስ መኮንን ድልድይ አድርጎ፣ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጎዳናንና አርበኞች ጎዳናን ጨምሮ እስከ ገፈርሳ ድልድይ ያለውን የከተማዋን ክፍል በጥበቃው ሥር አደረገ። የጦር ሠራዊት ሁለተኛ ብርጌድ ደግሞ መሣሪያውን በየፊናው እያስረከበ እጁን የሚሰጠውን የክብር ዘበኛ ወታደር ሲቀበልና በጂፖች ወዲያ ወዲህ እየተዘዋወረ ሠፈሮችን ሲቃኝ፣ ሲፈትሽና ሲያረጋጋ ዋለ።[1]

የክብር ዘበኛ ጦር ከነመሪዎቹ ተበታትኖ፣ በአንጻሩ ጦር ሠራዊቱ የድል ባለቤት ሆኖ ከተማይቱን በእጁ እንዳደረገ፤ ንጉሠ ነገሥቱ ቅዳሜ ታኅሣሥ ስምንት ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ከቀኑ አሥር ሰዓት ገደማ ከአሥመራ አዲስ አበባ ገቡ። ንጉሡ አዲስ አበባ ሲገቡ፣ መፈንቅለ መንግሥቱን ለማክሸፍ ከመሩት ከፍተኛ መኮንኖች ጥቂቶቹ በአውሮፕላን ማረፊያው ተገኝተው ተቀበሏቸው። ከእነዚህ መኮንኖች መካከልም፣ ኮሎኔል አሰፋ አየነና የሻለቃ አሰፋ ለማ (በኋላ አምባሳደር) ይገኙበታል። የአየር ኃይል የዘውዱን ሕልውና ለማስጠበቅ በክብር ዘበኛ ላይ የመትረየስ፣ የሮኬትና፣ የቦምብ ድብደባ በማካሄድ የውግዘት፣ የማስጠንቀቂያና የምክር ወረቀት

---

[1] *የኮሎኔል ጃገማ ኬሎ ሪፖርት። (ስለመፈንቅለ መንግሥቱ ለመጻፍ ያሰብኩ መሆኔን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም. ለጀኔራል ጃገማ ስነግራቸው በወቅቱ ስለውጊያው ለበላይ ያቀረቡትን ዘገባ ኮፒ እንዳደርገው የሰጡኝ ነው።)*

በመበተን ከፍተኛ ሚና የመጫወቱን ዜና ንጉሡ ካርቱምና አሥመራ ሳሉ ተረድተው ስለ ነበር አውሮፕላን ማረፊያ እንደደረሱ፤ ኮሎኔል አሰፋ አየነ የንጉሡን ጫማ ሊስሙ ዝቅ ሲሉ (የቤተ መንግሥት ሥርዓት ነው)፤ ንጉሡ ራሳቸው ዝቅ ብለው አንሥተው መሳማቸውን በቦታው የነበሩት ሰዎች ይናገራሉ። ኮሎኔል አሰፋ አየነ ከዚህ አቀባበል በኋላ በአየር ኃይል ዕዝ በመገኘት ሠራዊቱን ሰብስበው "እናንተ በሠራችሁት ሥራ ንጉሡ እኔን ሳሙኝ" ሲሉ ንጉሡ ለአየር ኃይሉ የሰጡትን ከበሬታና ምሥጋና ገልጸውታል።

ንጉሡ አዲስ አበባ ከገቡ ከአንድ ሰዓት በኋላ፣ እጁን ሳይሰጥ ተቋርጦ ቆይቶ የነበረ አንድ የክብር ዘበኛ የጦር ክፍል፣ ከፈረንሳይ ለጋሲዮን በኩል የክብር ዘበኛውን ሠፈርና ከተማዋን ከምሥራቅ እስከ ሰሜን ምዕራብ መኻል ለመኻል ይዘው ይቆጣጠሩና ያረጋጉ የነበሩትን፤ የ፩፻፭ኛን ሻለቃ የ፪ኛን ብርጌድ ጠቅላይ መምሪያዎች፣ በ፶ ካሊበርና በመትረየስ መምታት ጀመረ፤ ድንጋጤም ፈጠረ። ሆኖም ከጐንደር በአውሮፕላን የመጣው ጦር አዲስ አበባ በመግባቱ፤ በኮሎኔል ይልማ ሺበሺ (በኋላ ሜጀር ጄኔራል የፖሊስ አዛዥ) ከሚመራ የተወሰነ ጦር ጋር ተቀላቅሎ ሁለት ታንኮችን በመያዝ ተኩስ ወደ ተከፈተበት ወደ ፈረንሳይ ለጋሲዮን ተላከ። ይህ ጦር ፈረንሳይ ለጋሲዮን ዝቅ ብሎ ከሚገኘው ድልድይ ላይ ሲደርስ፤ ከለጋሲዩኑ አጥር አካባቢ የክብር ዘበኛ ጦር የአውቶማቲክና የመትረየስ ተኩስ ስለከፈተበት የተጋጋለ ውጊያ ተካሄደ። በዚህ ጊዜ ሦስት የክብር ዘበኛ ወታደሮች በአንድ በኩል ሾልከው በመምጣት ለኮሎኔል ይልማ ሺበሺ እጃቸውን ሰጡ። ተኩስ ከፍቶ ድልድዩን አላሻግር ያለው የክብር ዘበኛ ጦር ቁጥር ሦስት መቶ እንደሚደርስ ወሬ ቢሰማም፤ ኋላ ትክክለኛው ቁጥር አሥራ አንድ ሰዎች ብቻ እንደነበሩ ታውቋል። ሆኖም ጊዜው እየመሸ በመሔዱ ተኩስ እየበረደ መጣ። በኋላም የጦር ሠራዊቱ የመከላከያ ወረዳውን አጠናክሮ በመያዝ በዚያው ለማደር ተገደደ። በፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ ይህ የተኩስ ልውውጥ ይደረግ በነበረበት ጊዜም፣ ሜጀር ጄኔራል መርዕድ መንገሻ በአየር ኃይል አውሮፕላን ወረቀት ያስበትኑ ነበር። የተበተኑት ወረቀቶችም የአዲስ አበባን ከተማ ሕዝብንና ክብር ዘበኛን የሚመለከቱ ሲሆኑ፤ የሚከተለውን ፍሬ ሐሳብ የያዙ ነበሩ።

የአዲስ አበባ ሕዝብ ስማ!

ትናንትም ዛሬም በከሃዲነት ያሉት የክብር ዘበኛ መኮንኖች እጃቸውን እንዲሰጡ ትእዛዝ ተሰጥቷቸው ነበር። ትዕዛዙን ተቀብለው እጃቸውን ባለመስጠታቸው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የአየር ኃይልና የጦር ሠራዊት፣ እንዲሁም የሰላማዊ ፖሊስ ኃይል በዐመፀኞች ላይ የደረሰውን ስቃይ አይተሃልና ከዐመፀኞቹ ሠፈር ርቀህ በየቤትህ ተከትተህ የራስህን ጸጥታ ጠብቅ።

የክብር ዘበኛ ወታደር ከፋሽስት ጠላት ጋር በማይጨው ጦር ሜዳ የተጋደልከውን አስታውስ። በዚያም የጦር ግንባር ለእያንዳንድህ የመኮንንነትን ምግባር ወስደህ ለአገርህ የሰጠኸውን ስም ስታስብ ትናንትና

በአንተው እጅ የነበሩት ልጆችህ ዛሬ በዐድማ ሲመሩህ ልብህ ዳኛ ሆኖ ይፈርድብሃል። ለዚህም መጥፎ ተግባር የምታፈሰው ደም የምትከሰክሰው አጥንት ታሪክህን በነውር ስትቀብረው በትውልድህ ላይ ነቀርሳ የሆነ እርግማን እንዳይጥልብህ ተጠንቀቅ። በሚሰጥህ ትእዛዝ መሠረት ዐመፀኞች የሆኑትን መኮንኖች እጅ እጃቸውን ይዘህ በመስጠት ታማኝነትህን ባጠገብህ ለሚያልፈው የጦር ሠራዊት ግለጥ። ይህንንም በሁለት ሰዓት ጊዜ ውስጥ ባትፈፅም ስቃዩ በራስህ ላይ ይፈላል። ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥትህም በመካከልህ ተገኝተዋል።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት
የጦር ሠራዊት ጠቅላይ ኤታማጆር ሹም፤
ሜጀር ጄኔራል መርዕድ መንገሻ።

### ማስታወቂያ

እስከ አሁን ተደጋግሞ በተሰጠው ማስታወቂያ መሠረት ለዐመፀኞች የሚተኮሰው ጥይት በሰላማዊው ሕዝብ ጉዳት እንዳይደርስብህ ከወንበዴዎቹ ሠፈር ርቀህ በየቤትህ ተከትተህ እንድትቀመጥ በጥብቅ እናስጠነቅቃለን።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት
የጦር ሠራዊት ጠቅላይ ኤታማጆር ሹም፤
ሜጀር ጄኔራል መርዕድ መንገሻ።

### ለክብር ዘበኞች

በዱር በገደል በመሰንበታችሁ ምክንያት በሰው ሕይወትና ንብረት ላይ ጉዳት ቢደርስ ኃላፊነታችሁ እየበረከተ ይሔዳል። እስክትጠሩ ድረስ መሣሪያችሁን አቅራቢያችሁ ከሚገኘው የሠፈር ዳኛ ወይም ፖሊስ ጣቢያ እያስረከባችሁ እንድትገቡ ይሁን።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት
የጦር ሠራዊቶች ጠቅላይ ኤታማጆር ሹም፤
ሜጀር ጄኔራል መርዕድ መንገሻ።

### ለክብር ዘበኞች

አለቆቻችሁ ከድተዋችሁ እንደጠፉ በነዋል። ለምሳሌ አቶ ኃይለ ማርያም ከበደ ደሴ ላይ ተይዞ ታስሮአል። የዐድማው ቋጣሪዎች ዕድል እንደዚህ ሆኖ ሲከተት እናንተ የቀሆቹ ለምን በየስንሰሉ ትጉላላላችሁ። የሚሻላችሁ በየቤታችሁ ገብታችሁ ትእዛዝ መጠበቅ ነው። ጊዜው እያምልጣችሁ ወደ ቤታችሁ ግቡ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት
የጦር ሠራዊቶች ጠቅላይ ኤታማጆር ሹም፤
ሜጀር ጄኔራል መርዕድ መንገሻ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የጦር ሠራዊቶች ጠቅላይ ኤታ ማዦር ሹም፤ ሜጀር ጄኔራል መርዕድ መንገሻ" በሚል መለያ ከሥር የተቀመጠባቸው ከላይ በቅደም ተከተል የሠፈሩት የመምከሪያና የማስጠንቀቂያ በራሪ ወረቀቶች በተለይም ክብር ዘበኛውንና ደጋፊዎቹን የሚያረጋጋ ትእዛዞችን ያዘሉ እንደነበሩ ይታያል:: መጀመሪያ የክብር ዘበኛ ወታደር የሆነ ሁሉ ዐመፀኛ አለቆቹን እጅ እየያዘ እንዲሰጥ ያም ቢቀር ወደ ቤቱ እንዲመለስ፤ ታማኝነቱንም ትእዛዙ ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ በሁለት ሰዓት ውስጥ አከናውኖ ባይገኝ ውርድ ከራሱ መባሉን ያሳስባል:: ሁለተኛው ማስታወቂያ ደግሞ በያቅራቢያው ለሚገኝ ዳኛ ወይም ፖሊስ እጃችሁን እየሰጣችሁ ግቡ የሚል ነው:: በዚህ መሠረትም የክብር ዘበኛ ሠራዊት አባል የሆነ ሁሉ እጁን በፈቃዱ እየሰጠ መግባት ቀጠለ::

ይህ በእንዲህ እያለ በመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች በኩል ደግሞ ሽሽቱ ቀጥሏል:: በጉዞ ላይ ሳሉ ስለነበረው ሁኔታ የመቶ አለቃ ተክለማርያም ዘረፉ[2] እንዲህ ይላል::

> ከመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች ጄኔራል መንግሥቱ፣ ገርማሜና አብረዋቸው የመጡ መኮንኖች እንጦጦ ማርያም እንዳረፍን፣ ጄኔራል መንግሥቱ ‹ኧረ ለመሆኑ ሚኒስትሮቹ እንዴት ሆኑ? ፈታችኋቸው? ልዑል ጌታዬስ? › ብለው ጠየቁ:: ‹እሳቸው እዛው ናቸው:: ለሚኒስትሮች ግን የሞት ቅጣት ሰጥተናል":: ብሎ ገርማሜ መለሰ:: ጄኔራል መንግሥቱም ‹ገደላችኋቸው? ፈጃችኋቸው?› ብለው በሐዘንና በፀፀት ጠየቁ?። ገርማሜም፣ ‹የነሱ ሞት ሲቆጭህ፣ የሚቀጥለው ያንተ ነው› አላቸው::
>
> ከዚያም ‹ጋሼ የክብር ዘበኛ የተነሣበት ዓላማ ያልተሳካ ቢሆንም፣ አንተ ታዘው የነበረው ሠራዊት በመፍረሱ ደስ ብሎኛል:: ሥልጣን እንደማንይዝ እኔም ገብቶኝ ነበር:: ያ ሠራዊት ጀግና ነው:: የታወቀ ነው:: በኢትዮጵያ ላይ የፈለገውን ነገር ማድረግ ይችል ነበር:: ነገር ግን፣ ለንጉሠ ነገሥቱ ያለው ታማኝነት ከፍ ያለ ስለሆነ ሳይዋጋ ቀረ። ለኔ ትልቁ ነገር፣ ይህንን ሠራዊት መጣል ነበር:: ሠራዊቱ አንድ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ተነሣ ሲባል ሔዶ ያፍናል (ይደዛል):: ስለዚህ በኢትዮጵያ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችም ሆኑ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት በተቃውሞ መንቀሳቀስ ወይም የልቡን ተናግሮ ሐሳቡን መግለጽ ስላልቻለ፤ ይህ ሠራዊት ከተበተነ በኋላ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ይነሣሣል:: ዓላማው ውጤት እንዲያገኝ ይረዳል ብዬ ያሰብኩት ተሳክቷል:: ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደልቡ መናገር ይችላል:: ከዚህ በኋላ ሕዝቡ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመተዳደር በትግሉ ለመግፋት እንዲችል ያደርገዋል፤ ቀጥሎም እንደልቡ መሆን ይችላል:: ይኸው ነው ሐሳባችን ይህ ቢሳካለት የተሻለ ኑሮ ይኖራል:: በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ፣ ምንም ይህ እንቅስቃሴ ቢደረግም እንኳን ንጉሠ ነገሥቱ የመመለስ ዕድል ይኖራቸዋል:: ይህንንም ቋሚ ነው የሚያውቀው፣ ምናልባት ከአሥር

---

[2] የመቶ አለቃ ተክለ ማርያም ዘረፉ

እስከ አሥራ ሁለት ዓመት ድረስ ሊገዙ ይችላሉ:: የረጋና የተደላደለ አይሆንም:: ፈተና እየተፈታተናቸው ይቀጥላል:: ከዛ በኋላ ደግሞ ከፍተኛ ለውጥ በኢትዮጵያ ላይ ይመጣል:: ይኸንንም ለቋሚዎች እተዋለሁ::› ‹እኛ ግን አበቃን! በዚህ ጨረስን:: ከእንግዲህ ወዲያ ትግላችን አከተመ! ይኸው ነው ጋሼ› ብሎ እንደገለጸ ነገሩን አቋርጠን፣ ስለጉዞአችን አነሳን::

በዚህ ጊዜ ጀኔራል መንግሥቱ፣ ‹አሁን ሁላችሁም ወደየቤታችሁ ተመለሱ፤ መሣሪያችሁን እየፈታችሁ ወደሚስቶቻችሁና ልጆቻችሁ ሒዱ:: እስካሁን ላደረጋችሁት ሁሉ እግዚአብሔር ይስጣችሁ:: ቀጥሉ...› አሉ:: እኛም ‹እርስዎን ጥለን አንሔድም፣ ይልቅስ ጉዞውን ይምሩ› ብለናቸው ውይይት ውስጥ ስንገባ፤ ከነበርነው መኮንኖች ከፊሉ ወደ ጐጃም፣ ከፊሉ ወደ ቡልጋ እንሒድ የሚል ሐሳብ ሲንዘር፣ አይ! ወደ ጐጃም መሔድ አያዋጣንም፤ እስከ ዐባይ ድረስ ያለውን ያንን ሁሉ ሜዳ እንዴት እናልፈዋለን? የሚለው ሐሳብ አሳማኝ ሆኖ ስለተገኘ ጉዞው ወደ ቡልጋ እንዲሆን ተቆረጠ::

የሻምበል ክፍሌ ወልደ ማርያም፣ (ከጀኔራል መንግሥቱ ጋር ሁለተኛው ተከሳሽ) ‹አገሩንና መንገዱን እኔ አውቀዋለሁ› ስላሉ፣ እሳቸው መንገዱን እንዲመሩ ተስማሙ:: ከዚያ አቅጣጫችንን ከእንጦጦ ማርያም ወደ ቡልጋ በማድረግ ማታ ማታ ትንሽ ትንሽ እየሔድን ቀን ቀን ውሏችንን ቋጥኝ መሐል አድርገን ጉዞውን ቀጠልን:: በመንገዱ መኮንኖች እየከዱ ቁጥራችን እየቀነሰ ሄደ:: የቀረነው እህል ውሃ ሳናገኝ ውለን አደርን:: የጨለማው ጉዞ ሳናውቅ ወደ ለገዳዲ ወስዶን ኑሮ በአጋጣሚ ከሻምበል አበበ ቢቂላ ዘመዶች ቤት ገብተን ስለነበር የሻምበል ባዬ በድፍረት በመጠኑ በሚያውቀው በኦሮምኛ ‹እናንተ የአበበ ቢቂላ ዘመዶች አይደላችሁም?› ሲላቸው ‹አዎ! ነን› ብለው ተደስተው ተቀብለው ጥሩ መስተንግዶ አስተናግደው ለስንቅ የሚሆን ቆሎ በየኪሳችን አሲይዘው መንገድ መርተው ሸኙን:: ጉዞው የጨለማ መንገድ ስለሆነ ሳናውቀው ወደ የካ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ተቃርበን ኖሮ ሊነጋጋ ሲል የካህናት የዜማ ድምፅ ስንሰማና ስንተያይ፤ ከእንጦጦ ማርያም ስንነሳ ቡልጋ ከሰም በርሐ ለመግባት በመንገድ መሪነት እስከ ታኅሣሥ ፲፪ ቀን ድረስ አብረውን የቆዩት የሻምበል ክፍሌ ጭምር ተለይተውን ስድስት መኮንኖች ብቻ እንደቀረን አረጋገጥን:: ይኸውም ጀኔራል መንግሥቱ፣ ገርማሜ ንዋይ፣ ሻምበል ባዬ ጥላሁን፣ ሻምበል አሰፋ ጌታሁን፣ መቶ አለቃ ፈለቀ አንጋሶና መቶ አለቃ ተክለ ማርያም ዘረፉ ብቻ ነበርን:: ጀኔራል መንግሥቱ ይህንን ሲያዩ፣ ‹እንግዲህ እግዚአብሔር ይርዳችሁ፣ ጥሩ እንጀራ ይስጣችሁ፣ ከአሁን በኋላ ጀኔራል መንግሥቱን እዚህ አደረስናቸው፣ ብላችሁ አትናገሩ:: ለእናንተም ሕይወት ያሠጋል:: ምን በወጣችሁ!› ብለው ግንባራችንን ስመው ተለያየን።


በወቅቱ እንደተወራው ከዚህ በኋላ እነ ጄኔራል መንግሥቱ መንገዳቸውን ወደ ዝቋላ አድርገው ድሬ ጨለባ ከተባለው መንደር ደረሱ። ነገር ግን አስቀድሞም ወደ ዝቋላ ሊሔዱ ይችላሉ ተብሎ ይጠረጠር ስለነበር፤ ደብረ ዘይት ያለው የፖሊስ ኃይል አካባቢውን እንዲያስስና እንዲጠብቅ ትእዛዝ ደርሶት እያሰሰ ነበር። ግምቱ ትክክል ሆኖ በዚያ አካባቢ ስለታዩ ከበባና የተኩስ ልውውጥ ተደረገ። ጄኔራል መንግሥቱ እጃቸውን ሊይዟቸው ያሉትን ፖሊሶች አንዱን ተኩሰው ገድለው ሁለተኛ ውን ስላቆሰሉት ወደቀ። ጄኔራል መንግሥቱ መሣሪያውን ለመግፈፍ ወደ ወደቀው ፖሊስ ሲሔዱ ግን አቶ ገርማሜ በወንድሙ ላይ ተኩሶ ዓይናቸው አካባቢ ስለመታቸው ወደቁ። ከእርሳቸው በኋላም የሻምበል ባዬ ጥላሁንን ተኩሶ ገደለውና በኋላ ራሱን በራሱ አጠፋ ተብሎ ይነገራል።



የመቶ አለቃ (በኋላ ኮሎኔል) ማሞ አየለ

ከዚህ በኋላ የደብረ ዘይት ፖሊሶች የቆሰሉትን ጄኔራል መንግሥቱንና የሞቱትን የአቶ ገርማሜንና የሻምበል ባዬ ጥላሁንን አስክሬን አንስተው ወደ ገነተ ልዑል ቤተመንግሥት አምጥተው የሟቾቹን አስክሬን በቤተ መንግሥቱ ዐደባባይ ተጥሎ ንጉሡ እንዲያዩት ተደረገ። ከዚያም ወደፊት እንደምናየው እንደ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ አስክሬን የነዚህም የሁለት መፈንቅለ መንግሥት ተዋንያኖች አስክሬን ሕዝብ በሚያይበት ዐፄ ምኒልክ ሐውልት አጠገብ ተሰቀሉ። ጄኔራል መንግሥቱ ደግሞ ሕክምና ወደሚያገኙበት ፍል ውሀ ሆስፒታል ተልከው ሕክምና ጀመሩ።

ይህ በዚህ እንዳለ የሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ጉዳይ ገና አልተጠናቀቀም ነበር። አንድ የመቶ አለቃ የማሞ አየለ ጓደኛ፣ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ቅዳሜ ወደ ማታ ወደ ቀጨኔ መድኃኔዓለም አካባቢ ሔደ ይባላል ብሎ ይነግረዋል። የጦር ሠራዊት የመሐንዲስ መምሪያ መኮንኖች የኔን (የዚህ ታሪክ ጸሐፊ) ሚዜዬ ከነበረው ከመቶ አለቃ (በኋላ ኮሎኔል) ማሞ አየለ ጋር የነበረኝን ቀረቤታ ስለሚያውቁ ሆን ብሎ ነው ያንን መረጃ ያደረሰው። የመቶ አለቃ ማሞ አየለም ይህን እንደሰማ ወዲያው ወደ



የመቶ አለቃ (በኋላ ኮሎኔል) ማሞ አየለ

ቤቴ መጥቶ ይነግረኛል። ይህን ተመርኩዤ በማግሥቱ፣ ታኅሣሥ ዘጠኝ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ጠዋት ሦስት ሰዓት ገደማ፣ ቤታቸው ቀጨኔ መድኃኔዓለም አካባቢ ወደ ሆነው፣ ወደ ሊቀመጣኔ[3] ወረደ ቃል ወንድም ቤት ሔድኩ። ሊቀመጣኔ (መጣኒ) በልዩ ካቤኔ የሕግ ክፍል ሹም ነበሩ። ከሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ጋር በሥራ ቀረቤታቸው ብቻ ሳይሆን የአገር ልጅም ስለሆኑ፤ ተቀራራቢነት ነበራቸው። ስለዚህ በዚያ በኩል ማለፉን ያውቁ እንደሆነ በማግኘቱ እንዲረዱኝ ለመጠየቅ (ወደ ቤት ለመግባት በር ላይ ቁሜ) ለዘበኛው ማንነቴን ነገርኩት። ዘበኛው «ሦስት አራት ከሚሆኑ ሰዎች ጋር ናቸው፤ ይቆዩኝ ነግሬ ልምጣ» ብሎ ሔደ። ከዚያም «ግባ በለው» ተብሎ ስገባ፤ ቡና እየተጠጣ ነበር። «ቁጭ በል» ተብዬ እንደተቀመጥኩ፣ «ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ በዚህ አካባቢ አልፏል ይባላል፣ የሚያውቁት ነገር እንዳለ ቢረዱኝ» ብዬ ጠየኩ። «መምጣቱን አልሰማንም። ሊመጣ አስቦ እንደሆንም ባይመጣ ይሻላል። እኛ ልናደርግለት የምንችለው ነገር የለም» የሚል መልስ ተሰጠኝ።

ከዚያ በአጋጣሚ ባገኘው ወይም ወሬ ብሰማ በማለት በጊዜው ‹እቴጌ› በኋላ ‹የካቲት ፲፪ ትምህርት ቤት› ከሚባለው በር ጀምሮ እስከ ቀጨኔ መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን አደባባይ በሚወስደው መንገድ መኪናዬን ቀስ ብዬ እየነዳሁ እስከ ስድስት ሰዓት፤ ሦስት አራት ጊዜ ተመላልሼ ያሰብኩት ሳይሳካ ተስፋ ቆርጬ ወደ ቤቴ ተመለስኩ። አካሔዴ ትክክል ኑሯል። ይኸውም እኔ በዚያ አካባቢ የተመላለስኩት በወሬ በሰማሁት ብቻ ተመርቼ ሳይሆን መንፈሴም ገፋፍቶኝ ነበር።

ከመፈንቅለ መንግሥቱ ክሽፈት በኂላ አንደኛ ክፍለ ጦር በነበርንበት ጊዜ የሻለቃ ተሰማ ዋቅጅራ እንደነገረኝ በእርግጥም ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ እና የሻለቃ ተሰማ ታኅሣሥ ዘጠኝ ቀን ባደሩበት ቤት አካባቢ የማያስቀይ ተኩስና አሰሳ እየከበደ በመምጣቱ ከዚያ ወጥተው ወደ ቀጨኔ መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን በሚወስደው መንገድ ካለው ወንዝ ፊፋ ውስጥ ለመግባት ተማክረው ካደሩበት ቤት ሲወጡ፤ የሻለቃ ተሰማ ወደኋላ ቀረት ይላል። ኮሎኔል ወርቅነህ ክዳት ነው ብሎ ይጠረጥርና እጁን የሰጠ እንደሆነ ይጠቁምብኛል ብሎ በመስጋት እኔና አቶ ኤፍሬም ፀሐይ የኔ ምክትል የነበረ (በኋላ የገንዘብ ሚኒስቴር የአስተዳደር መመሪያ ኃላፊ) ታኅሣሥ አምስት ቀን ኮሎኔል ወርቅነህ ቤት አብረን ሔደን ከቤቱ ኃላፊ ተቀብለን ወስደን በሰጠነው ኡዚ ሻለቃ ተሰማን ተኩሶ ለመግደል ይሞክራል። ሻለቃ ተሰማ ከተሞከረበት ግድያ ወደ ገደል ተንከባሎ ያመልጣል። የሻለቃ ተሰማ ከተኩሱ አምልጦ ወደ ወንዙ ተንከባሎ ገብቶ ከተኩሱ ከተረፈ በኋላ በቅርብ ላገኘው የጦር ሠራዊት ያሳሽ ጦር አዛዥ አንድ የመቶ አለቃ፣ አንድ የአሥር አለቃና አንድ ወታደር ከቆሙበት ሔዶ እጁን ሰጠ። «ማነህ!» ብለው ሲጠይቁት «የሻለቃ ተሰማ ዋቅጅራ ነኝ» ብሎ ስሙንና መሥሪያ ቤቱን ሲነግራቸው፤ የአሥር አለቃው ኤም ዋኑን ወደ ግንባሩ ደግኖ ቢተኩስ ጥይቱ ግንባሩን ስቶ በራሱና በጆሮው መሐል ቆዳውንና

---

[3] ሊቀመጣኔ የቤተክህነቱ የመንፈሣዊ ክፍል ሹመት ነው

ጠጉሩን ለብልቦ በማለፍ ያስደነግጠዋል:: በዚያ ሳቢያ ከፍተኛ የደም ግፊትና የመንፈስ አለመረጋጋት አሳድሮበት ነበር:: ከዚያም ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር ተወስዶ ሲጠየቅ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ያለበትን አካባቢ ጠቆመ::

‹የፈሩት ይደርሳል፣ የጠሉት ይወርሳል› እንዲሉ የሻለቃ ተሰማ ዋቅጅራ እጁን ከመስጠቱ በፊት፣ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ወደ ቀጨኔ መድኃኔዓለም አካባቢ ሔዷል የሚል ጥቆማ ለሜጀር ጄኔራል መርዕድ ደርሷቸው ስለነበር፤ ጥቆማውን የሚያጣሩ ቃኞዎችና ሰላዮች ወደ አካባቢው ልከው በማጣራት ላይ እንዳሉ፣ ሻለቃ ተሰማ ተይዞ ጥቆማው ትክክል መሆኑን በማረጋገጡ ኮሎኔል ወርቅነህን ለመያዝ አንድ የመቶ ጦር ኦፐሬሽኑን እንዲያካሒድ ተላከ:: በዚህ የመቶ ጦር ጐንም ሌሎች ረዳት ጦሮች እንዲሰለፉ ተደረገ:: እንደተባለውም ጥቆማው ትክክል ሆኖ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህን ለመያዝ የተሠማራው ኃይል ከወንዙ ውስጥ ዓይቶት ከከበበው በኋላ የከባቢው ጦር አዛዥ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህን «ጌታዬ! እጅዎን ይስጡ?» ብሎ ሲጠይቀው፤ «አዬ! እሱን ተወው!» ቴዎድሮስ እጅ መስጠትን አላስተማረንም:: ይልቅ የምልህን ስማ:: እኛ የተነሣነው፣ እኛ ተበድለን ሳይሆን የአገራችንን ችግር ለማስወገድ ነበር:: እኛ ጀምረነዋል እናንተ ጨርሱት» እንዳለ፤ ከአዛዡ አጠገብ የነበረ አንድ ወታደር ተንደርድሮ ሔዶ ሊይዘው ሲል፣ በያዘው ኡዚ ተኩሶ ይገድለዋል:: አንድ የአሥር አለቃ ደግሞ ከሌላ ጐን ገሥግሦ መጥቶ ሊይዘው ሲል በሱም ላይ ተኩሶ ቆስሎ ከወደቀ በኋላ፤ በቀረችው አንድ ጥይት ራሱን «ሰዋ»::[4]

ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ራሱን ከገደለ ከአራት ሰዓት በኋላ፣ ሬሳው የሻለቃ አላምረው ጥሩነህ በተባለ የጦር ሠራዊት መኮንን በአንቡላንስ ወደ ቤተ መንግሥት ተወሰደ:: በዚያን ጊዜ የሻለቃ አንጋጋው ኃይሌ ቤተ መንግሥት ግቢ ውስጥ ስለነበሩ፤[5] የሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ አስከሬን ከመኪና ወርዶ ቤተ መንግሥት ግቢ አደባባይ ተጥሎ ንጉሡ እንዲያዩት መደረጉን ያስታውሳሉ:: ከዚህ በተጨማሪ «ወርቅነህ» እጅግ በጣም መልከ ቀና ወጣት የነበረ መሆኑንና አስከሬኑ መሬት ላይ ወድቆ ሲታይ ያ መልከ ቀና ወጣት መኮንን የተኛ እንጂ የሞተ አይመስል እንደነበር በስሜት ይገልጻሉ:: ንጉሡ አስከሬኑን በተመለከቱ ጊዜ ሲገልጹም «ኮሎኔሉ ከፈጠረው ዐመፅ ይልቅ ሬሳውን የተመለከቱትን ሁሉ ያራደ ነበር:: ጃንሆይም አስከሬኑን ትኩር ብለው አዩና ልባቸው በሐዘን ተሰበረ:: እያዩት ሞቷል ብለው ማመን ቸገራቸው:: ከዐመፀኞቹ አንዱ ብሎ መቀበልም አቃታቸው:: ለብዙ ደቂቃዎች ተክዘው

---

[4] ይህንን መረጃ ያገኘሁት የኔና የመቶ አለቃ ማሞን ጓደኝነት የሚያውቅና ያስከበበው ጦር አዛዥ የነበረው የመቶ አለቃ ወዲያው ለመቶ አለቃ ማሞ አየለ በመንገሩ፤ የመቶ አለቃ ማሞ አየለም ራስ ደስታ ሆስፒታል ጀርባ ከነበረው ቤቴ መጥቶ ይህንኑ በዚያው ምሽት ስለነገረኝ ነው:: የመቶ አለቃ ማሞ ከመቶ አለቃው ጋር ሊያገናኘኝ ተነጋግረን የነበረ ቢሆንም፤ እኔ ወዲያው ተይዤ ስለታሰርኩ የነበረውን ዝርዝር ሁኔታ ሳላገኝ ቀረሁ::

[5] ሻለቃ በኋላ ኮሎኔል አንጋጋው ስላዩትና ስለሰሙት አንድ ማስታወሻ እንዲሰጡኝ በ፲፱፻፹፮ ዓ.ም. ደጋግሜ ጠይቄአቸው፣ ከብዙ ውትወታ በኋላ አንድ ወር አስጠብቀው ፈቃደኛ በመሆን ለጋዜጣ (እንዳትሸጠው) ሳልከው መጽሐፍ ብቻ አውለው በማለት ከሰጡኝ ባለ ፴፮ ገጽ የጽሑፍ ማስታወሻ

ሲያጉመተምቱ ከቆዩ በኋላ፤ ሐሳባቸውን ሰብሰብ አድርገው፣ በማይሰማ ድምፅ ‹ወስዳችሁ ለሕዝብ በሚታይ አደባባይ ስቀሉት› እንዳሉ ይጠቅሳሉ።

የሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ሬሳ ከቤተ መንግሥቱ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ወጥቶ ወደ መናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ አደባባይ ተወስዶ ተሰቀለ። ልክ እንደሌሎቹ ጉዳዮች ይህንን ሁኔታም የመቶ አለቃ ማሞ አየለ ሰምቶ ነገረኝ። ጊዜው ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ገደማ ቢሆንም፤ ይህን እንደሰማሁ በቦታው ደርሼ የነገረኝን አረጋገጥኩ። የወርቅነህ አስክሬን መሰቀሉን አረጋገጥኩ አንድ ታንክ ከዐፄ ምኒልክ ሐውልት በስተደቡብና አንድ ታንክ ከሐውልቱ በስተሰሜን ከስቅላቱ ፊትና ኋላ ቆመው ይጠብቃሉ። አካባቢው ጭር ብሏል። ምን ላድርግ ብቻዬን ሦስት ጊዜ አካባቢውን ዞሬ በመጨረሻ መኪናዬን ከስቅላቱ አጠገብ አቁሜ

*ወዳጅ ያዝናል እንጂ መች አብሮ ይሞታል*

*እንደምንም ብሎ ይሰነባብታል*

እንዲሉ የማደርገውን አጥቼ አዝኜ፣ ተከፍቼ እና ተክዤ ከሬሳው አጠገብ ብቆምም ማንም የጠየቀኝ አልነበረም። ይህንን ዓይቼ ወደ ቤቱ ተመለስኩ። ለሊቱን የማደርገውን እንዳጣሁ፤ ሳልተኛ አደርኩ። በማግሥቱም እንደገና ሔጄ ዓየሁት። የሻለቃ አንጋጋው እንዳሉት የሞተ አይመስልም ነበር። ከዚያ የት እንደተቀበረ ሳይታወቅ ቀረ።

# ክፍል ፫

# የታኅሣሡ ግርግር
# መዘዝ

## ምዕራፍ ፰

# የመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ የተወው አሻራ

## ከመፈንቅለ መንግሥቱ ክሽፈት በኋላ በአንደኛ ክፍለ ጦር

የመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ ክሽፈት እንደተረጋገጠ፤ ግርግሩ ሲቆም ማንኛውም ሠራተኛ ወደ ሥራው እንዲመለስ፣ የዐመፅ ተካፋይ የነበረ ደግሞ እጁን ከነመሣሪያው ለፖሊስ፣ ለምስለኔ ወይም ለወረዳ ገዥ እንዲሰጥ፤ መንግሥት የክተት ጥሪ በሬዲዮ አሰራጨ። የዐዋጁን ጥሪ በመቀበል ብዙ የክብር ዘበኛ ወታደሮችና መኮንኖች እጃቸውንና መሣሪያቸውን ከላይ ለተጠቀሱት ክፍሎች አስረክበው ጊዜያዊ እሥር ቤት ወደ ሆነው አንደኛ ክፍለ ጦር እየገቡ ታሠሩ። በትእዛዙ መሠረት ሰዎች ወደሥራ መሔድ ሲጀምሩ፤ የዐመፁ ተካፋይ ከነበሩትም ውስጥ ወደሥራ ለመሔድ የሞከሩ ነበሩ። ከነዚህ ውስጥ አቶ ነጋሽ ድንበሩ አንዱ ነበረ። አቶ ነጋሽ ድንበሩ ከመፈንቅለ መንግሥቱ ክሽፈት በኋላ እንደማንኛውም ሠራተኛ ወደ ሥራው ለመመለስ ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ፊት ለፊት ካለው ሰፊ መስክ ጧት ጧት እየመጣ፤ ከሌሎች ሠራተኞች ጋር ተኮልኩሎ እየዋለ፤ ወደ ቤቱ ይመለስ ነበር። አንድ ቀን ነጋሽ አያኖ ተብሎ ሲጠራ "አቤት" ብሎ ካንድ የጦር ሠራዊት ሻምበል ፊት ይቀርባል። አንተ ነህ ነጋሽ አያኖ" ብሎ ጠየቀው። «አዎ» ብሎ ሲመልስለት «አንደኛ ክፍለ ጦር ስለምትፈለግ በመኪና ልላክህ ወይስ ራስህ ትሔዳለህ?» ይለዋል። ይህን ጊዜ ነጋሽ ይነቃና «ራሴ እሔዳለሁ» ይለዋል። መኮንኑም ማስታወሻ ጽፎ ለማን ሪፖርት እንደሚያደርግ ነግሮ ይልከዋል። ነጋሽ ይነቃና ወደታዘዘበት መሔዱን ትቶ ወደ ቤቱ ሔዶ ልብሱን ለውጦ ወደ ደብረ ብርሃን ይሔዳል። ከዚያ የካህን ልብስ አሰፍቶ ለብሶ እንደቄስ ጠምጥሞ ወደ «መንዝ አልዩ አምባ» ይሔዳል። እዚያ ከዘመዶቹ ጋር የሚካፈለው መሬት ስለነበረው የተጠራቀመ ሦስት ሺህ ብር ይሰጡታል። በጥርጣሬም ያዩታል፤ ቶሎም እንዲሔድላቸው ይነግሩታል። ወደ ደብረ ብርሃን ሲመለስ ግን መንገድ ላይ አድፍጠው ገድለው ገንዘቡን ለመውሰድ ይተኩሱበታል። ከዚያም ከተኩሱ ያመልጥና ወደ ደብረሲና ይሔዳል።

ነጋሽ ደብረ ሲና ቀን ቀን ገጠር እየዋለ ማታ ማታ ለዐይን ሲይዝ ከተማ እየገባ ወሬ ያጠያይቃል። ነጋሽ የማንንም መልክ፣ ቅርጽ፣ ድምፅ፣ ጠባይና ባሕርይ ማስመሰል ወይም ሆኖ የመታየትና የመምሰል ተሰጥኦ አለው። ስለዚህ ጥሩ ካህን መስሎ ነበር የሚንቀሳቀሰው። የፀጥታው ክፍልም ብርቱ አሰሳ ያደረገው በዚሁ አካባቢ ነበር። የሰው ደም አይለቅም ይባላልና፣ አንድ ቀን ነጋሽ መጠጥ ቤት ገብቶ ሲጠጣ የፀጥታ ሠራተኞች ከመጠጡ ቤት ይገባሉ። ሰላምታ ይሰጡትና ይተዋወቃሉ። «ልጆቼ ምን ልጋብዛችሁ» ብሎ ጠይቆ «ደብረሲና ብርድ ስለሆነ አረቄ» ብለው ይጋበዛሉ። በዚያ ጊዜ ከመካከላቸው አንዱ የሔራልድ ጋዜጣ አውጥቶ ማንበብ

ይጀምራል። ነጋሽም ዐይኑን ጣል አድርጐ ርዕሶቹን ይመለከታል። ሌላው የፀጥታ ሠራተኛ የነጋሽን ሁኔታ ይከታተል ስለነበር ታዳኙ መገኘቱን ያረጋግጣል።

ነጋሽም ጋብዟቸው «እንግዲህ ልጆቼ ደህና አምሹ" ብሎ ሊሔድ ሲል፣ "እንዴ እኛስ ብንጋብዝዎት? የርስዎን ተጋብዘን" ይሉታል። "በቃኝ" ይላቸዋል። በዚህ ጊዜ ማንገራገር ይጀመርና ወደ ጠብ ሲደረስ ተረባርበው ይይዙትና በካራቴ መትተው ይጥሉታል። ሲፈተሽ «ፎርቲ ፋይፍ» ሽጉጥ ይገኝበታል፤ እሱነቱን አረጋግጠው ለሊቱን አንድ ማክ መኪና ሙሉ ፈጥኖ ደራሽ (ፖሊስ) መጥቶ ወደ አዲስ አበባ ይዘውት ሔዱ። በመኳንንቱ ግድያ ተጠርጥሮ ተይዞ በወንጀል ምርምራና ፍርድ ቤት እስከ መጨረሻው ቢክደም፤ የሞት ቅጣት ፍርድ ተፈረደበት። በመጨረሻም በሞት ተቀጣ። በሞት በተቀጣበት ዕለት ላናዘዙት ካህን መኳንንቱን መግደሉን አምኗል። አናዛዡ ቄስም «አሁን ወደእውነተኛዉ ቦታ ስለምትሔድ ሂሳብ ክፍል በነበርክ ግዜ ብዙ ገንዘብ ጠፍቷል። ስለዚህ ጉዳይ የምታውቀው እንዳለ ንገረኝ» አሉት። በመጀመሪያ ደረጃ ወደእውነተኛው ቦታ መሔዴን አላውቅም፤ የገንዘቡን ጉዳይ ግን በአድራሻዬ በፍታብሔር ይጠይቁኝ" አላቸው ተብሎ፤ አናዛዡ ቄስ የነገሯቸው ሰዎች ሲያወሩ ተሰምቷል። እንግዲህ አቶ ነጋሽ ድንበሩ በተጠቀሰው ምክንያት ቂሙን ለመበቀል ጊዜና ሁኔታ ስላጋጠመው ከላይ የጠቀሳቸውን ባለሥልጣናት የገደላቸው እሱ መሆኑን በድፍረት ይገልፃል። ነጋሽ ድንበሩ ከጠዋት እስከማታ ከእሥረኛ ባለሥልጣናቱ አካባቢ ሳይርቅ ውሎ ርሽናው ሲጀመር አብሮ ከማካሔዱ በተጨማሪ፤ እራሱ እንዳመነው ቆስለው ሊተርፉ የሚችሉትን ሁሉ የምርመራ ተኩስ እናድርግ ብሎ ጥይት አርከፍክፎ የፈጀ ነው። አቶ ነጋሽ ከሚፀፀትባቸው ሟቾች ግን ደጃዝማች ለጥይበሉ ገብሬ ዋና ናቸው። ስለሁኔታውም ሲገልጽ ደጃዝማቹ አረር ውስጥ ገብተው ነው እንጂ እርሱ ሊገላቸው ፈልጎ እንዳልነበረ በቁጭት ያስታውሳል።

እኔም በበኩሌ፣ አርብ ከወርቅነህ ጋር ተለያይቼ ቅዳሜ ዕለትና እሑድ እርሱን ፍለጋ ብባክንም ሳይሳካልኝ ቀርቶ እቤት ቁጭ ብዬ ሳለሁ፤ እነጀኔራል መንግሥቱ ወደ ደብረዘይት ሔደዋል የሚባል ወሬን የሰማቺው ወሮ ዘረፈ ወርቅ ከእነጀኔራል መንግሥቱ ጋር ባለቤቷ ሻለቃ ያሬድ ቢተውም አብሮ ሔዷል በመባሉ እሑድ ታኅሣስ ፱ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. መጥታ ና ወደደብረዘይት እንሒድና እንፈልገው አለችኝ። በዚያ ሰፊ መስክ እንዴት ብለን ነው የምናገኘው ብዬአት በሃሣብ ስንብከነከን ውለን መፍትሔ አጥተን የምሳ ሰዓት ሲደርስ ተለያየን።

በማግሥቱ የሥራ ባልደረባዬና ጓደኛዬ የሻምበል ሺፈራው ከበደ ባለቤት፣ ወይዘሮ ገነት ዘለቀ ባለቤቷ እጁን ለፖሊስ ጣቢያ ሰጥቶ ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር ገብቷል ይባላልና እባክህ ሔደን እናረጋግጥ ብላ ተጨንቃ ጠየቀችኝ። እኔም እሷን ለማበረታታትና እግረ መንገዴንም ሁኔታውን ልይ ብዬ እሺ አልኩና ተያይዘን ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር ሔድን። እዚያ ስንደርስ የክፍለ ጦሩ አካባቢ፣ ከላይ ባቡር ከታች መኪና ከሚሔድበት ድልድይ ጀምሮ (በተለምዶ መሿለኪያ የሚባለው) ኋላ ባቡር

መምጣቱን የሚያሳይ መብራትና ኬላ በተሠራበት አድርጐ[1]፣ ወደ ደብረዘይት በሚወስደው መንገድ የተወሰነ ርቀት ይዞ እስከ ክፍለ ጦሩ መግቢያ በር ድረስ፣ ቦታው ከሚችለው በላይ እጅግ በጣም በተጨናነቀ የሰው ብዛት ተከቦ ነበር። እየቆየ ለዘብ ጠባቂዎች ከቁጥጥር በላይ በሆነ ሁኔታ ሕዝቡ በሩን ጥሶ እስከመግባት ድረስ አየለ። ወታደሮቹም የባሕር ዛፍ ዝንጣፊ ዱላ በመያዝ ለመምታት እየቃጡ በማስፈራራት ብቻ ግፊቱን ለመግታት ቢሞክሩም፤ ልጇን የምትፈልግ እናት፣ ባሏን ምትፈልግ ሚስትና ወንድሟን የምትፈልግ እህት ራሷን እንዳትመታ እንደ ተዋጊ በሬ አንገቷን ወደታች አቀርቅራ ማን ሙቷል፣ ማን ቆስሏል፣ ማን አምልጧል እያለች ትባዝን ነበር። ስለመጣችበት ሰው ዕጣ ፈንታ ጭንቀት ስለነበረባት፣ የምታደርሰውንም ሆነ የሚደርስባትን ችግር ሳታውቀው ትንኳተት ነበር። ተሰብስቦ ከነበረው ሕዝብ ሦስት እጅ ያህሉ ሴቶች ስለነበሩ፤ ከጭንቀታቸው የተነሣ እጅግ በጣም ከባድ የነበረውን መጨናነቅና ግፊት ከምንም ሳይቆጥሩ በዕሩብ ሰዓት አንድ ሜትር ያህል ርቀት መሔድ መቻል ከተሰፋ ጋር በጣም ጥሩ ተብሎ የሚገመት ነበር።

ወ/ሮ ገነት ዘለቀና እኔ እንዳንጠፋፋ እጅ ለእጅ ተያይዘን የጀመርነውን ጉዞ በነበረው ግፊት ፅናት ሳንወድ ተላቀቅንና ተለያይተን በትንሽ እርቀት ላይ እንተያይ ጀመርን። በተለይ እኔ ከውጥረት የተነሣ በግራና በቀኝ አጎንብሰው በሚሔዱ ሁለት ሴቶች ዳሌ በሞርሳ እንደተያዘ ተጣብቄ እግሬ መሬት ለቆ ከባቡር ሀዲዱ እስከ አንደኛ ክፍለ ጦር መግቢያ በር ድረስ ተጉዣለሁ። በኋላ እንደነገረችኝ፣ ወ/ሮ ገነትም ከዚያ ያልተለየ ሁኔታ አጋጥሟት ነበር። በዚህ ሁኔታ ከሦስት እስከ ሰባት ሰዓት ተንኳተን ክፍለ ጦሩ መግቢያ በር ስንደርስ አሁን የምሳ ጊዜ ስለሆነ ሰው መግባት አይችልም፣ በዘጠኝ ሰዓት ተመለሱ ተባለ። ያ ሁሉ ድካማችን ከንቱ ሆኖ፤ በመጣንበት ዓይነት ጊዜ ፈጅተንና አሳራችንን በልተን ወጣን። ችግሩ ይህን ያህል ይሁን እንጂ፣ ችለው የገቡት ደግሞ ቁርጣቸውን ዐውቀው ከፊሉ እያለቀሰ፣ ከፊሉ ደስ ብሎት እየሣቀ ይመለስ ስለነበር፤ እኛም ነገ ቀደም ብለን መጥተን ዕድላችንን ለመሞከር ወስነን ተለያየን። ሰኞ በዚህ ሁኔታ ከተመለስን በኋላ፣ ማክሰኞ ታኅሣስ አሥራ አንድ ቀን በተመሳሳይ ሁኔታ ከሰዓት በፊት እንደተለመደው ለመግባት ሞክረን ሳይሳካልን ቀረ። ሰኞ ሥራ ባልገባም ሰው ሁሉ ማክሰኞ ወደ ሥራ መመለስ ስለጀመረ እኔም ከሰዓት በኋላ ሥራ መግባት አለብኝ ብዬ ወደ ሥራዬ ሔድኩ። ወ/ሮ ገነት ዘለቀ ግን እዚያው ቆይታ ሞክራ መግባት ስለቻለች፤ ባለቤቷ እዚያ መኖሩን ዓይታ አረጋገጠች።

ይህ በዚህ እንዳለ፣ ታኅሣሥ ፲፫ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም.፣ እኔ፣ አቶ ማሞ አዩና አቶ ኤፍሬም ፀሐይ ቢሮአችን ገብተን ሥራ እንደ ጀመርን፣ በፀጥታ መምሪያው ም/ኃላፊ በኮሎኔል ይርጉ እንዳይላሉ የቃል ትእዛዝ ከሥራ መታገዳችንን አንድ

[1] ይህ ቦታ አሁን ለመንገድ ሥራ ማስፋፊያ ፈርሶ ከላይና ከታች መኪና እንዲያልፍበት ተደርጎ የተሠራው መንገድ ሲሆን፤ ፊትለፊቱ ያለው በወቅቱ አንደኛ ክፍለጦር ከመፈንቅለ መንግሥቱ በኋላ ደግሞ አራተኛ ክፍለ ጦር የተባለውና የጦር ሠራዊቱ ማረፊያና ማገገሚያ የነበረ ግቢ ነው።

ወታደር ተልኮ መጥቶ ለሁላችንም በየቢሮአችን ነገረን:: ወዲያውም መሥሪያ ቤቱን በመጠበቅ ላይ ላለው ጦር ኃላፊ ትእዛዝ ተሰጥቶ ኖሮ ከቢሮአችን እንድንወጣና እንድንሔድ ነገረን:: ጉዳዩም በዐመፁ ተካፋዮች ነበራችሁ ተብሎ ነው:: የሚገርመው በነዚያ ቀኖች አብሮ ላይ ታች ያለው ጉንደሬ ያልሆነውም ጭምር መሆኑ እየታወቀ፣ ከሥራ የታገድነው ግን ጉንደሬዎች ብቻ ተለይተን ነበር:: በዚህ የተነሣ እኔ እቤቴ ተቀምጬ ነገሮችን እያሰላሰልኩ እንዳለሁ፤ አቶ ኤፍሬም ፀሐይና አቶ ማሞ አዩ ወደ ቤቴ መጥተው፣ ‹አቶ ብርሃኑ ዝም ብለን ከቤታችን ከተቀመጥን እገዳውን በተገቢነት የተቀበልን እንዳይመስልብን በወቅቱ ሁኔታዎችን ለማረጋጋት ያስተዳደሩን ሥራ ኃላፊነት ለያዙት ለልዑል ደጃዝማች አሥራተ ካሣ ኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት ሔደን እናሳውቅ› አሉ:: ይሄ የማይሆንበትን ምክንያት ‹በእሳቸውና በእኔ መካከል የማያቀራርቡ እናንተ የማታውቋቸው ጉዳዮች አሉ:: የኔ ከእናንተ ጋር መሆን እናንተን ችግር ላይ ሊጥላችሁ ይችላል› በማለት በመፈንቅለ መንግሥት ውጣኔ ውስጥ ከሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ጋር ከየካቲት ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ጀምሮ እንደነበርኩበትና የደጃዝማች አሥራተ ካሣ ባለቤትንና ልእልት ጊሩትን ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ሳይጋብዛቸው እንደመጡ እንግዳ ቆጥሮ ሊያናግራቸው ባለመፈለጉ እኔ መልሼ ወደቤታቸው እንዳደረስኳቸው ባጭሩ አለፍ አለፍ ብዬ ገለጽኩላቸው:: ስለሁኔታው ሲሰሙ፤ ራሳቸውን ይዘው ጉድ ብለው ከቆዩ በኋላ ያ አልፏል፤ ግድየለህም እንሒድ ብለው አጥብቀው ስለያዙኝ ሳልወደውና ሳላምንበት እነሱን ቅር ላለማሰኘት፣ ‹‹እሺ ይሞከር›› በማለት፣ ቅዳሜ ታኅሣሥ ፲፭ ቀን ጠዋት ወደቤተ መንግሥቱ ሔድን::

ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት አካባቢ ከአፍሪካ ጎዳና ወደ ኢዮቤልዩ ዛሬ ብሔራዊ ቤተ መንግሥት ፊት ለፊት ካለው መስቀለኛ መንገድ ከቤተ መንግሥቱ ደርሰን የሰሜን በር ፊት ቆመን ሳለ፤ አንድ ወጣት የጦር ሠራዊት መኮንን አግኝተን የመጣንበትን መሥሪያ ቤት ነገርነውና ‹‹ልዑል ደጃዝማች አሥራተ ካሣን ስለምንፈልግ እዚህ መሆናችንን እባክህ ንገርልን›› ብለን ጠየቅነው:: ወጣት መኮንኑ መልእክቱን አድርሶ፣ ‹‹እነማን ናችሁ?›› የሚል ጥያቄ ይዞ መጣ:: አቶ ማሞ አዩ የስማችንን ዝርዝር ጽፎ ላከ:: ‹‹ጠብቁ አስጠራችኋለሁ›› ተብለን በመጠበቅ ላይ እንዳለን፣ አምስት ሰዓት ገደማ የፈራሁት አልቀረም በጦር ሠራዊት ወታደሮች ተከብበን ተያዝን:: ከዚያ በስሪ ኳርተር መኪና ወደ መሥሪያ ቤታችን ሊወስዱን ሲሉ፣ ‹‹የመጣነው በራሳችን መኪና ስለሆነ በራሳችን መኪና እንሔዳለን›› ብለን ስለተከራከርን ስምምነት ላይ ተደረሰና፣ በስሪ ኳርተር መኪና የተለያየ መሣሪያ በታጠቁ በርካታ ወታደሮችና ከባድ መትረየስ በጠመዱ በሁለት ጂፖች ታጅበን ወደ መሥሪያ ቤታችን ሔድን:: ከቀኑ ስድስት ሰዓት ላይ መሥሪያ ቤታችን ግቢ ውስጥ እንደገባን በኃላፊነት አሳጅቦ ያመጣን መኮንን ግቢውን ለሚያስጠብቀው መኮንን አስረክቦን ከኮሎኔል ይርጉ እንዳይላሉ የሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ ምክትል ኃላፊ ጋር ተነጋግሮ አጅበው ያመጡንን ወታደሮች

ይዞ ተመለሰ። እኛም ለተወሰኑ ደቂቃዎች መሥሪያ ቤቱ ግቢ ውስጥ ካለው መስክ ቁመን ብንቆይም፤ ነገሩ ቶሎ ስላልተፈታ አረፍ አረፍ አልን።

በዚህ መልኩ እስከ ስምንት ሰዓት ቆይተን፤ ስምንት ሰዓት ሲሆን ኮሎኔል ይርጉ እንዳይላሉ ከልዑል ደጃዝማች አሥራተ ካሣ ጋር ተነጋግረው ይመስለኛል ግቢውን ይጠብቁ በነበሩ የጦር ሠራዊት ወታደሮች ታጅበን ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር ተወሰድን። እዚያ ስንደርስ ለጥበቃ ኃላፊው እንዲያስረክቡ የታዘዙ ቢሆንም፤ የእሥር ቤቱ ኃላፊ ይህ፣ የሚሊቴሪ እንጂ የሲቪል እሥር ቤት ስላይደለ አልቀበልም ብሎ መለሰን። በዚያው በመጣንበት አኳኋን ተመልሰን ወደ መሥሪያ ቤታችን ተወሰድንና ኮሎኔል ይርጉ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር ተነጋግረው ስለተስማሙላቸው አሥራ አንድ ሰዓት ሲሆን በሸኘ ደብዳቤ ተመልሰን ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር ተልከን በር ላይ ተረከቡንና በአሥራ ሁለት ሰዓት እሥረኛ ያለበት ቁጥር ፬ ቤት የተዘጋ በር አስከፍተው አገቡን።

በዚያን ጊዜ የነበሩት የሥር ቤት ቁጥሮች ቁጥር ፩፣፫፣፬፣፭፣፯ የሚባሉ መደዳውን የተሠሩ የጦር ሠራዊት የማረፊያና ማገገሚያ ሰቀላ ቤቶች (ባራኮች) ናቸው። እኛ እሥር ቤቱ የደረስነው አሥራ ሁለት ሰዓት ገደማ ስለነበር፤ ቤተሰቦቻችን የት እንዳለን ሳያውቁ ጧት እንደወጣን ነው የቀረነው። ለመኝታና ለራት የሚሆነን ነገር አልያዝንም። ከበሩ መዝጊያ አጠገብ አገኘነው ቦታ ተቀምጠን እእምሯችን በተለያዩ ሐሳቦች ተወጥሮና ዓለምም ተዘበራርቃ ታየችን። ሦስታችንም የሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ መሥሪያ ቤት አባሎች ስለሆንና፣ በዚያን ጊዜ ሕዝቡ ስለ ፀጥታ መሥሪያ ቤት የነበረው ግንዛቤ ከመሠረተ ፍልስፍናው (ከጽንሰ ሐሳቡ) ውጭ በድፍኑ በምስጢር ሰውን መከታተል፣ ስለላ ማካሔድ እና ሰውን ለችግር ማጋለጥ አድርጎ ስለሚገነዘብ (በጠላት ግዜ በአርበኛና ደጋፊ ላይ ይደረግ እንደነበረው)፤ ቁጥር አራት ቤት ስንገባ፣ በዚያ ውስጥ የነበረው አብዛኛው መኮንን ሰላዮች ተለቀቁብን ብሎ በፍርሃት ተሸብሮ ያለጊዜው ተሸፋፍኖ የተኛም አሞኛል ያለም ነበር። ጥቂቶች ቢሆኑም ሁኔታዎችን መገመት የቻሉት ደግሞ ለስለላ ቢሆንማ በየክፍሉ አከፋፍለው ያስገቡዋቸው ነበር እንጂ፣ እንዴት በአንድ ክፍል ሰብስበው ያስገቡዋቸዋል? በማለት ሳይጠራጥሩ ተቀብለው ስለመጣንበት አነጋገሩን።

በመጨረሻ ማታ የመኝታ ሰዓት ሲደርስ፣ ቀደም ብለው የገቡት የክብር ዘበኛ መኮንኖች በዚያ የነበረውን ደህና ደህናውን አልጋና ፍራሽ ስለያዙት ለጊዜው እኛ አላገኘንም ነበርና፣ የመኝታ ልብስና እራትም ስላልያዝን ሁለት ጉንደሬዎች ኮሎኔል ወርቁ መኮንን (በኋላ ጀኔራል) እና የሻምበል ማሩ ጋረድ (በኋላ ኮሎኔል) ለመኝታ የሚሆን ልብስ ሲያዋጡልን፤ ሌሎችም መኮንኖች የጐደለንን ሁሉ አዋጥተው ከመስጠታቸውም በላይ፣ ተሸጋሽገው ተኝተው አልጋም ለቀቁልን። በዚህ ዓይነት ረድተውን ዓለም እንደተዘበራረቀችብን የመከራ እንቅልፍ (ደመመን) ይዞን አደርን። መንግሥቱ የኛ ቤተሰቦች ያለንበትን ቦታ አውቀው የሚያስፈልገውን ሁሉ

አመጡልን:: አልጋም ከዛው ጠጋግነን እምንወድቅበት አበጀን:: እንግዲህ በዚህ ላይ እንዳለን ጉንደሬዎች ብቻ ተለይተው ታሠሩ የሚለው ሃሜት ስለጠነከረ ከጥቂት ቀናት በኋላ ሌሎች የመሥሪያ ቤታችን ባልደረቦችም ተይዘው መጥተው ገቡ:: እኛም ኑሮ እንዳደረጉት ነውና በአንደኛ ክፍለ ጦር በነበረው ሁኔታ አዲስ ኑሮ ጀመርን::

በአዲሱ ኑሮ የዚህ ታሪክ ጸሐፊ ለምርመራ ከመሔዶ በፊት፣ ልዑል ደጃዝማች አሥራተ ካሣ አሁን ለምነው ሳይሆን ተለምነው ሊያገኙኝ እንደሚችሉ ሲያረጋግጡ የመቀራረቢያና መደለያ ፍራፍሬ በያይነቱ፣ ማርማላታና የገበታ ቅቤ፣ ብስኩት፣ አይብ፣ ዳቦ፣ ሠርዲን አድርገው በሁለት በጣም ትልልቅ ካርቶኖች ሙሉ ተጭኖ እሥር ቤት ድረስ መጥቶ[2] ለእሥር ቤቱ ኃላፊ ለኮሎኔል ግርማ አስረስ ከልዑል ደጃዝማች አሥራተ ካሣ «ለአቶ ብርሃኑ አስረስ የተላከ ነው» ተብሎ ቀረበ:: ኮሎኔል ግርማም «ሻለቃ ብርሃኑ ነው እንጂ አቶ ብርሃኑ የሚባሉ የሉም» ይሏቸውና የመጡት ሰዎች ተመልሰው ይሔዳሉ:: እነዚህ ሰዎች ሁኔታውን ለልዑል ደጃዝማች አሥራተ ሲገልጹ እሳቸው እንዳሳሰሩኝ ስለሚያውቁ «አለ ሒዱና አግኙት» ብለው መልሰው ሰደዷቸው::

ተመልሰው መጥተው «አቶ ብርሃኑ አስረስ የሚባሉ ሰው አሉና ከውስጥ ያስጠይቁ ያገኟቸዋል» ብለው ለእሥር ቤቱ ኃላፊ ለኮሎኔል ግርማ አስረስ ይነግሯቸዋል:: ኮሎኔል ግርማም ቁጥር አራት ቤት መጥተው በሩ ላይ «አቶ ብርሃኑ የሚባሉ ሰው አሉ?» ብለው ጠየቁ:: በሩ አጠገብ ስለነበርኩ «አለሁ» አልኩና ወጣሁ:: ስወጣ በቁመናዬና ሰውነቴ በጣም ድቅቅ ያልኩ ሰው ስለሆንኩ፣ ልዑል ደጃዝማች አሥራተ ካሣ አስበው ስንቅ የሚልኩለት ሰው ትልቅ፣ ለዓይን ጐላ ያለ! ጠብቀው ነበርና፣ እኔን ሲያዩ ደንገጥ ብለው ወደኋላ ፈግ ፈግ አሉ:: «አንተ» ሲሉኝ የነበሩት ኰሎኔል ግርማ አስረስ፣ «ብርሃኑ አሥረስ እርስዎ ነዎት?» አሉኝ:: ፈገግ ብዬ «አዎ» አልኳቸው ነገሩ ገርሞኝ:: «መልካም ነው! ጌታዬ ልዑል ደጃዝማች አሥራተ ካሣ ስንቅ ልከውልዎታል» አሉኝ:: ለኔ ለየትኛው ቀረቤታዬና ውለታዬ ነው የሚልኩልኝ» አልኩ:: በመልሴ ተገርመው «እንዴ» ሲሉ «አዎ! እንዴት ዐውቀው ለኔ ስንቅ ይልኩልኛል? ካሰቡልኝ መጀመሪያውኑ ለምን ያስሩኛል» አልኩ:: አሁን ደግመው «እንዴ? ሲሉ «አዎ! እንዴት እሳቸው አሥረው ራሳቸው ስንቅ ይልኩልኛል?» አልኩ:: የጠየቅነው ፍትህ እንጂ ለኔ እሥራትና ስንቅ አልነበረም:: «ቢሆንም ዝም ብለው መቀበል አለብዎ» አሉኝ:: «አልቀበልም» አልኩ:: አሁንም ደግመው ያመጡት ሰዎችም ክው! አሉና ደነገጡ:: «እንዴት ነው ይሔ ነገር» ብለው ኃላፊ ሆነው የመጡት ሰው «ጌታዬ» ብለው አክብረው እንድቀበል ተማፀኑኝ:: እሳቸው አሥረው እሳቸው ስንቅ ላኪ ሆኑ ማለት ነው:: እኔም «የለም አልቀበልም! ለየትኛው

---

[2] ከዚህ በፊት የተፈጠሩ ሦስት ከዚህ ጉዳይ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ቀደም ብሎ እርሳቸውና እኔ ያልተስማማንባቸው ጉዳዮች ነበሩ::

ውስታዬ ለየትኛው ቅርበቴ ነው የሚልኩልኝ» ብዬ እምቢ ስላልኩ ቅር እያላቸው ተመልሰው ሔዱ።

በዚያን ጊዜ በልዑል ደጃዝማች አሥራተ ካሣ ላይ እንዲህ ያለ አቋም መያዝ ሊያስከትል የሚችለውን ችግር ማሰብ ተገቢ ነበር። የልጅነት፣ ያለመብሰል ነገር ሆነና ተደረገ። በማግሥቱ ያው ዕቃ ተመልሶ መጣና ለአቶ ኤፍሬምና ለአቶ ማሞ አዩ ተብሎ ቀረበና ተቀበሉ። ይህን ባደረጉ በማግሥቱ አቶ ኤፍሬምና አቶ ማሞ አዩ ወደ ልዑል ደጃዝማች አሥራተ ካሣ ቢሮ ተጠርተው ሔደው ስለጠቅላላው ሁኔታና ስለኔ ተጠይቀው የመሰላቸውን ሁሉ ሳያስረዱ አልቀሩም። እዚያ ውስጥ የኔ ስም ተነሥቶ በበጐ እንደማይታይ ይሰማኝ ስለነበር፤ ባይነግሩኝም እገምት ነበርና አልጠየኩም፤ እነሱም አልተናገሩም። የሻምበል አሥራት ደፈረሱ (የክብር ዘበኛ የማስታወቂያ ክፍል ኃላፊ) ግን ሁሉን ማወቅ ይፈልግ ስለነበር አንዳንድ ሁኔታዎችን ጠየቀ። የተመለሰለትም ልዑል ደጃዝማች አሥራተ ካሣ ባጠቃላይ መፈንቅለ መንግሥቱ ስለተነሣበት ሁኔታ የምታውቁት እንዳለ ግለጹልኝ ሲሉ መጠየቃቸውንና እነርሱም ምንም የምናውቀው ነገር አልነበረም ብለው እንደመለሱላቸው ነው። ከጊዜ በኋላ ልዑል ደጃዝማች አሥራተ ካሣ ሁለቱ ሰዎች የነገሯቸውን ለሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ (በኋላ አቡነ መልከ ጸዴቅ) በካቢኔው የመንፈሳዊ ጉዳይ ኃላፊና የቅድስት ሥላሴ ገዳም አስተዳዳሪ፣ ሸጠውት ሔዱ (ስለሱ በጐ አልተናገሩም) ብለው እንደነገሯቸው አጫውተውኛል።

ይህ በዚህ እንዳለ፣ እሥር ቤት ውስጥ እያለን አንዳንድ የማስታውሳቸው ክስተቶች ነበሩን። የክብር ዘበኛ ሠራዊት የንስሀ አባት የነበሩት ቄስ የመቶ አለቃ አማረ ቸኮል ማታ ማታ ምህላ እየመሩ እንጸልይ ነበር። በእንዲህ ዓይነት በጸሎት ላይ በነበርንበት በአንድ ወቅት በአጠገባችን ባለው ወደ ደብረዘይት በሚወስደው ጎዳና የምታልፍ አንድ ሞተር ብስክሌት ከበሩ አጠገብ ስትደርስ በጢስ ማውጫዋ ሁለት ጊዜ ድው! ድው! የሚል የተኩስ ድምፅ የሚመስል አሰማች። በዚህ ጊዜ ግቢው ውስጥ የነበረው ከጅማ የመጣ ጦር ተኩስ ተከፈተብን በሚል ድንጋጤ በሙሉ ሻለቃው አንድ ጊዜ ተኩስ ሲከፍት ሰማይና ምድሩ የተገናኘ መሰለን። እኒያ ምህላ ሲመሩ የነበሩት ቄስ በተኩሱ ድንጋጤ ምህላ መምራቱን አቋርጠው «አቡነ ዘበሰማያት» ብለው ዘለው እመኝታቸው ላይ አረፉ። ከዚያ በኋላ ምሥጢርም ስናወራ ሆነ ያላሰብነው ሰው ብቅ ሲል «አቡነ ዘበሰማያት» ማለት ጨዋታችንን ማቆሚያ ዘዴያችን ሆኖ ቀጠለ።

ይኸ በእንዲህ እንዳለ ከሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ መምሪያ አቶ መስፍን ወልደ ሚካኤል፣ እኔ ራሴ ብርሃኑ አስረስ፣ አቶ ማሞ አዩ፣ አቶ ኤፍሬም ፀሐይ፣ የሻለቃ ተፈራ ወልደ ትንሣኤና የሻምበል አሥራት ደፈረሱ ከክብር ዘበኛ ባንድ ላይ መሰብሰባችንና አብረን መብላታችንን ያዩ «ወንጀለኞች በገዛ እጃቸው ተለይተው ባንድ ላይ ሆኑ» የሚል ሐሜትና አስተያየት ያሰሙ ጀመር። አሽሟጣጭም ቢያሽሟጥጥ

ሐሜተኛም ቢያማ እኛ ኑሮአችንን በዚህ ዓይነት መሥርተን እንዳለን፣ አንዳንድ የውጭ ወሬ ስንጠይቅ፣ «የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ተማሪዎች በዐመፁ ተከፋይነትም ሆነ በምስክርነት እንዳይጠየቁ፣ ከተጠየቁ ነገሩን ያከፋዋልና ግርማዊነትዎ በጠቅላላው ነገሩን ቢዘጋው ይሻላል» ብለው የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ማት፣ ንጉሡን ስለመከሩ ሃሳባቸው ተቀባይነት አግኝቶ ነገሩ ሲዘጋ፤ የመሐንዲስ ኮሌጁ ዲን ግን እንዲህ ስላላስደረጉ፣ አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ እኔ ተጠርቼ ወጣሁ:: ቀጥሎ የኔ ተመሳሳይ የሆኑ ስድስት ወጣት መኮንኖችም ተጠሩና ወጥተው እኔ ከመሐል ሆኜ በሰልፍ እንድንቆም ተደረገ:: ከዚያ አራት የመሐንዲስ ኮሌጅ ተማሪዎች ከመርማሪ ፖሊሶች ጋር መጡና፣ «ታኅሣሥ ስድስት ቀን ወደ ኮሌጁ መጥቶ ንግግር ያደረገላችሁን ሰው ከዚህ መሐል ለይታችሁ አውጡ (ጠቁሙ)» ሲባሉ፤ አራቱም ያለአንዳች ማወላወል እኔን ጠቆሙ:: ከዚህ በኋላ፣ ወደ ነበርንበት ተመለስን:: ትንሽ ግዜ ቆይቶም መርማሪዎች አንዳንድ መኮንን ለምርመራ እየጠሩ መውሰድ ጀመሩ:: ተመርማሪው ሔዶ ሲመለስ የቀረቡለትን ጥያቄዎች እየሰማን የየራሳችንን መልስ እናዘጋጅ ጀመር::

እኔም የካቲት ወር ውስጥ ተራው አንድ ቀን ደረሰኝና ተጠርቼ ብሔድም ለምርመራ ሳልቀርብ ሦስት ቀንና ለሊት ጨለማ ቤት ተዘግቶብኝ ቆየሁ:: በአራተኛው ቀን ዘጠኝ ሰዓት ላይ ለምርመራ ሲወስዱኝ፤ በነበርኩበት የታፈነ አየርና ጨለማ ታፍኖ የሰነበተው ሰውነቴ ለአዲስ አየርና ከባድ ብርሃን በድንገት በመጋለጡ እግሬ መሬት መቆንጠጥ አቅቶት ሥራመድ እግሬ ነቀል ነቀል አለና ሰውነቴን መሸከም ተስኖት፤ ወደቅሁ:: ከዚያ አንስተው ሲያስቀምጡኝ ቀስ በቀስ ሰውነቴ ከአየሩም ከብርሃኑም ጋር ተለማምዶ ማንሠራራት ጀመረ:: በእንዲህ ያለ ሁኔታ ትንሽ ከተቀመጥኩ በኋላ ዓይኔ ብርሃን አልደፍር ብሎ አስቸገረኝ:: ስለዚህ በእጄ ሸፍኜ ቆይቼ ቀስ በቀስ በመልቀቅ ሳለማምደው እጅግ በጣም ብሩህ ሆኖ እየታየኝ ወደ ምርመራ ክፍሉ መሔድ ቻልኩ::

በምርመራ ክፍሉ፣ መጀመሪያ የፖሊስና የጦር ሠራዊት ባልደረቦች የሆኑ የበታች ሹማምንትነ ለምርመራ መግቢያ የሚሆን ስሜን፣ ዕድሜዬን፣ መሥሪያ ቤቴንና ሥራዬን ከጠየቁና ከመዘገቡ በኋላ ወደ ሌፍትናት ኮሎኔል ተከሥተ አስተላልፈውኝ ጥያቄና መልስ ጀመርን:: ከታኅሣሥ አምስት ጀምሮ እጄ እስከተያዘበት ቀን ድረስ ምን ምን ሥራዎችን እንዳካሔድኩ ጠይቀውኝ መመለስ ስጀምር፤ ከሳቸው ጋር በታዛቢነት አብሮ ተቀምጦ የነበረ የጦር ሠራዊት ወጣት መኮንን ተጠርቶ ወጣ:: ብቻችንን ስንቀር፤ ድምፅ የሚቀዳ ነገር ስለመኖሩ ገልመጥ ገልመጥ ብለው የቤቱን ጣራ ማዕዘን ዓይተው «የሚያስወነጅልህ ነገር እንዳትናገር፣ ራስህን ጠብቀህ ነው መናገር:: ምስክር ከሌለብህ ጨርሶ የምታምነው ነገር መኖር የለበትም» የሚል አጭር ምክር ሰጡኝ:: መኮንኑም ወዲያው ተመልሶ መጣና ገባ:: ወዲያው ሌ/ኮሎኔሉ፣ ጠንከር ባለ አነጋገር፣ «እስቲ ከታኅሣሥ አምስት ጀምሮ እጅህ

እስከተያዘበት ድረስ የሠራሃቸውን ነገሮች፣ ምንም ነገር ሳትደብቅና ሳታስቀር በዝርዝር ንገረን፤ ብዙ መረጃዎች ተገኝተው ተያይዘዋልና አምነህ እራስህን ብታቀርብ ይሻላል» የሚል ምክርና ጥያቄ አቀላቅለው አቀረቡልኝ:: እኔም እንኳን የቀደመውን ምክር አግኝቼ ባይነገረኝም እራሴን ለችግር አጋልጬ የምሰጥ አልነበርኩምና ተደፋፈርኩ:: አስቤ የነበረውንም በእርግጥ እንድገፋበት ስላደፋፈሩኝ ያዋጣኛል ያልኩትን ቃል ሰጠሁ:: ኮሎኔሉ ትልቅ ውለታ ሠርተውልኛል:: የጦር ሠራዊቱ ወጣት መኰንንም ባይናገርም በሁኔታው ራስህን ጠብቅ የሚል ምክር በፊቱና በሰውነቱ እንቅስቃሴ መክሯል:: ለቀረበው ጥያቄ መልስ ከሰጠሁ በኋላ የምሳ ሰዓት ስለደረሰ ወደ ቁጥር አራት ቤት ተመልሼ ከሰው ጋር ተቀላቀልኩ:: በማግሥቱም እንዲሁ ተጠርቼ ሔጄ ምርመራው ቀጠለ::

እዚህ ላይ አንድ ሳነሣው የምፈልገው ነገር አለ:: ይኸውም፣ ለምርመራ የሚሔዱት መኰንኖች ካሉበት ክፍል እየተጠሩ የሚወጡት፣ ቀደም ብዬ ከዘረዘርኳቸው የማረፊያ ቤቶች (ባራኮች) ነበር:: ከጅማ ከመጣው ጦር ውስጥ የተገኙ የሻለቃ ሙሉጌታ የሚባሉ፣ ቁመናቸውም ሆነ ሥነ ሥርዓታቸው የሠለጠነ የእንግሊዝ የጦር መኰንን የሚመስሉ ምግባረ መልካም ሰው፣ ለእሥረኛው በነበራቸው አክብሮት «ነገር ከልኩ ሳያልፍ ትርፍ ነገር ማድረግ አያስፈልግም» በማለት ለምርመራ ተጠርቶ የሚወጣውን መኰንን በእርጋታ አሜውተው፣ አረጋግተውና አበረታተው ይወስዱና ለመርማሪዎች ያስረክቡ ነበር:: በአንጻሩ ደግሞ፣ ሌፍተናንት ኮሎኔል በቀለ ወርቁ የሚባሉት ከኮሎኔል ግርማ በኋላ የተተኩት የእሥር ቤቱ ኃላፊ ሲመጡ፤ ለምርመራ የተጠራውን ሰው ከማረፊያ ቤት እንዳወጡት ሳይሆን ከጦር ሜዳ ማርከው እንደያዙት ሰው ነበር የሚያደርጉት:: ሁልጊዜ ሰውነታቸውን አስቆጥተው አነጋገራቸውም እንዲያው መሬት ለቆ ጫን ጫን እየተነፈሱ፣ የሚፈለገውን መኰንን ጠርተው በሁለት ወታደር አሳጅበው ወስደው ለመርማሪው ያስረክቡ ነበር:: በጊዜው በእሥረኞች አመለካከት በጠባቂው ጦር አዛዥ በሻለቃ ሙሉጌታና በእሥር ቤቱ ኃላፊ መኰንን በኮሎኔል በቀለ ወርቁ መካከል የነበረው የሥነ ሥርዓትና የጠባይ ሁኔታ ይህን ይመስል ነበር:: የሚደንቀው እኒህ በአንደኛ ክፍለ ጦር የእሥር ቤቱ ኃላፊ የነበሩት ሌፍትናንት ኮሎኔል በቀለ ወርቁ በዚያው ዓመት መጨረሻ አካባቢ፣ አንድ መጠጥ ቤት ውስጥ ከሰው ጋር ተጣልተው አንድ ሰው ገድለው ሌላውን አቁስለው ተይዘው፣ አዲስ አበባ ወህኒ ቤት ገብተው፣ ሰው በሰው እጅ ሲወድቅ እንዴት እንደሚሆን ዓዩ:: ባለፈው አድራጐታቸው ተጸጽተው ራሳቸውን ከሰው አግልለው ሲቀመጡ፤ ብዙዎቹ የክብር ዘበኛ መኰንኖችና እኔም ያለፈውን ረስተን ስለወደፊቱ ብቻ እንዲያስቡ እየመከርናቸውና እያበረታታናቸው ሁላችንም የመከራ ጊዜ ጓደኞች ሆንን::

እንግዲህ የመጀመሪያ ምርመራዬ ካለቀ በኋላ፣ ለሌላ አጣሪ መርማሪ ለኮሎኔል ዳዊት ገብሩ ተመራና ያን ቀደም ብዬ የሰጠሁትን ቃል በማስተባበል «የለም ሌላ ብዙ የሠራኸው አለ:: ማስረጃም ተይዟልና እውነቱን ብታወጣ ይሻላል» የሚል

ጥያቄ አነሡ:: በአጋጣሚ ከመጀመሪያ መርማሪዬ ይልቅ ከኮሎኔል ዳዊት ገብሩ ጋር ዕውቂያ ያለንና ያንድ አካባቢ ሰዎችም ስለሆን፤ ባይረዱኝ እንኳን፣ አላስፈላጊ ጫና ፈጥረው ያስጨንቁኛል የሚል እምነትና ግምት አልነበረኝም:: ነገር ግን፣ ያገኘሁት እርዳታ ሳይሆን ጠንከር ያለ ጥያቄ ነበር:: እኔ ግን መጀመሪያ ከሰጠሁት ቃል የለወጥኩት አልነበረም:: ለዚህም የረዳኝ አራት የመሐንዲስ ኮሌጅ ተማሪዎች ለምስክርነት ለፖሊስ የሰጡትን ቃል ይዘቱን ሰምቼ ስለነበርና፣ ማስተባበያ ለሌለው አምኖ መከራከሩ ይሻላል ብዬ ስለወሰንኩ ከዚያች ዝንፍ አላልኩም::

ኮሎኔል ዳዊት ገብሩ ይህን አጣርተው ከጨረሱ በኋላ፣ በሌ/ኮሎኔል ታምራት ይገዙ ሰብሳቢነት፤ ፊታውራሪ ትርፌ ሹምዬ፣ ኮሎኔል አበበ ገመዳና ሌሎች ሁለት ስማቸውን የማላውቀው አባሎች ላሉበት የምርመራ አጣሪ ኮሚቴ ተመራና ቀረብኩ:: እነሱ ዘንድ ስቀርብ በዘር ተለይተን ስለታሠርን ንዴትና ሲቃ ይዞኝ ስለነበር ንግግሬን የጀመርኩት፣ ስለምርመራው ሳይሆን፣ ስለአድሏዊ አሠራሩ ነበር:: "እኛ የተያዝነው ከሌሎቹ የሥራ ጓደኞቻችን የተለየ ወንጀል ሠርተን ሳይሆን ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ጉንደሬ ስለሆነ እነዚህም ጉንደሬዎች ናቸው፤ በቀል ማውጫ ይሁኑ ተብሎ መሆኑ የሚያሳዝን ነው" ስል፤ ሌ/ኮሎኔል ታምራት እዝንና ስቅቅ ብለው፣ "እሺ ይኸን እናጣራለን" አሉ:: ፊታውራሪ ትርፌና ኮሎኔል አበበ ገመዳ ግን፣ "የተማሪዎች የምስክርነት ቃል ብቻ ሳይሆን፤ ኮሎኔል ወርቅነህን ትረዳ ስለነበርክ አብራችሁ የሠራችሁት ብዙ ነገር እንዳለ ይታወቃል" በማለት ጠበቅ ጠበቅ ያሉ ጥያቄዎች አቅርበው በማፋጠጥ ማጥ ውስጥ ሊያገቡኝ ሞከሩ:: እኔ ግን በዚያው በመጀመሪያው ቃል ፀንቼ "ሌላ የሠራሁትና የማውቀው ነገር የለም" ብዬ ፀናሁ:: ፊታውራሪ ትርፌ ሹምዬና ኮሎኔል አበባ ገመዳ ግን ደጋግመው ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህን ትረዳ ነበር ይባላል ሲሉኝ አዎ አልኩ:: ታዲያ ምን ምን ነበር የምትረዳው ቢሉኝ፤ የቢሮ ሥራ ነው የምረዳው ስላልኳቸው፤ የሚያገኙብኝ ምንም ነገር አጡ:: በዚህ ጊዜ ሌ/ኮሎኔል ታምራት ይገዙ "ቅድም ስላሳሰብከው ነገር እናጣራና እንነግርሃለን:: አትዘን እስከዚያ ወደ መጣህበት ተመቀስ" አሉኝና ተመለስኩ::

በጊዜያዊ እሥር ቤቱ የነበረው እሥረኛ ሁሉ ምርመራ ሊጨርስ ሲቃረብ፤ የካቲት ሦስት ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ጄኔራል መንግሥቱ ከሁለት አባሪ ናቸው ከተባሉ የክብር ዘበኛ መኮንኖች ጋር ወደ ፍርድ ቤት መወሰዳቸውን ሰማን:: ይህን ያልኩበት ምክንያት ጄኔራል መንግሥቱ ታሥረው ይኖሩ የነበረው ከጠቅላላው የክቡር ዘበኛ እሥረኛ ሠራዊት ጋር ሳይሆን ለብቻቸው እራቅ ባለው መድፈኛ ግቢ ስለነበር ነው::

ይህ በዚህ እንዳለ አንድ ጭምጭምታ ተሰማ:: ጭምጭምታውም ከጦሩ የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄ ጋር የተያያዙ ነገሮች ነበሩ:: መፈንቅለ መንግሥቱ ከሽፎ አንድ ወር ተኩል እስኪያልፍ ድረስ በለውጥ ንቅናቄው አራማጆችም ሆነ በዘውድ ጠባቂው ክፍል ለጦሩ ቃል ተገብቶለት የነበረው የደመወዝ ጭማሪ በዝምታ ተያዘ:: በዚህም የተነሣ ጦሩ ጉርምርምታ ማሰማት ጀመረ:: ጉርምርምታው እያየለና እየከረረ

ሲመጣ ይህን ለማርገብ መንግሥት አንድ ስልት ቀየሰ። ይኸውም፣ በመጀመሪያ የተራ ወታደር ደመወዝ ብር ፲፯ የነበረው ብር ፳፬ ሊሆን ነው ብሎ አስወርቶ ከሠራዊቱ የሚመጣውን መልስ ጠበቀ። ወሬውን ተከትሎ በመንግሥት የተሠራጭው ወሬ ጦሩን እንዳበሳጨውና እንደማይቀበለው ተሰማ። በዚህ ጊዜ ደግሞ፣ መንግሥት ይህን የጦሩን አቋም ለማስለወጥ ሌላ ስልት ቀየሰ። ስልቱም በአዲስ አበባ ከተማ ካሉትና ንቅናቄውን ለማክሸፍ ከየጠቅላይ ግዛት ከመጡት ልዩ ልዩ የጦር ክፍሎች ጭምር የተውጣጡ የሠራዊቱ አባሎች ካምቦሎጆ (ስታዲየም) ውስጥ ተገኝተው የምድር ጦር አዛዥ ጄኔራል ከበደ ገብሬ የደመወዝ ጭማሪውን አስመልክቶ በሚሰጡት መግለጫ ላይ ውይይት ለማድረግ በቦታው እንዲገኙ ለየጦር ክፍሉ መልእክት ተላለፈ። በመልእክቱ መሠረት ተወካዮች በቀኑና በሰዓቱ በቦታው ተገኙ። ጄኔራል ከበደ መግለጫቸውን ሲጀምሩ፤ ከአገሪቱ የምጣኔ ሀብት ዐቅም አንጻር ታይቶ የተራ ወታደር ደመወዝ ከብር ፲፯ ወደ ፳፯ ከፍ እንዲል ተደርጓል። የነባርና የእጅ ብልጫ አበል እንደነበረው ይቀጥላል በማለት ንግግር አደረጉ። የተሰበሰበው የየክፍሉ ተወካይ ግን በውሣኔው አለመስማማቱን ገለጸ። በእናንተ ቃል የተገባልን ወይም የለውጥ ንቅናቄው ክፍል ታኅሣሥ ስድስት ቀን ባወጣው መግለጫ ለወታደር የቆረጠው ደመወዝ ይሰጠን የሚል ድምፅ አሰማ።

ጄኔራል ከበደ ገብሬ መጀመሪያ የለውጡን ንቅናቄ የመደገፍ አዝማሚያ ይታይባቸው ነበር። የኛን ድካም አልደገፉትም የሚል ሐሜት በጦሩ ውስጥ ስለነበር፤ የጦር ተወካዮች ነገሩን ከዚያ ጋር በማያያዝ በመግለጫው ይዘት ተከፍተው እንዳሉ ከተሰብሳቢዎቹ መካከል አንድ የዐሥር አለቃ "ጃሎ" እያለ ወደ ጄኔራል ከበደ ገብሬ ቀርቦ እንዲህ ብሎ አቅራራ።

"እኔው ተበድዬ እኔው ካሣ ክሼ
ዕርቁ ጅላጅል ነው ላፍርሰው፣ መልሼ"

ብሎ ስብሰባውን ሊያፈርስ ሲል፣ ተው! ተው! ተብሎ ሰውዬው ተይዞ ዞር እንዲል ተደረገና ስብሰባው መቋጫ ሳያገኝ ተቋረጠ።

ይህ በሆነ ወር ባልሞላ ጊዜ ጦሩ በየክፍሉ ውስጥ ለውስጥ በምስጢር ተወያይቶ የሚወክሉት የበታች ሹማምንትን መረጠ። የነዚህ ተወካዮች ተልዕኮ በጦር ኃይሎች ኤታማዦር ሹም የተገባልን የደመወዝ ጭማሪ ወይም የታኅሣሥ የለውጥ መሪዎች ወስነውት የነበረው ጭማሪ የወታደር መነሻ ደመወዝ ብር አርባ ከምክትል መቶ አለቃ እስከ ሻለቃ ተጨማሪ ብር ሃምሣ ይሰጠን ብለው ጃንሆይ ዘንድ ቀርበው ማመልከት ነበር። እነዚህ ተወካዮች የተላኩበት አቤቱታ ፍፃሜ ባያገኝ ወይም ነገሩን ለማዳፈን ሲባል እንደዚያ ጃሎ ባይ በተወካዮች ላይ አንዳች እርምጃ ቢወሰድ ጠቅላላ ጦሩ በእሥር ላይ ያሉትን የክብር ዘበኛ መኮንንኖችን ፈትቶ የጦሩን ዐመፅ እንዲመሩ ለማድረግ ወሰነ ተብሎ ተሰማ። ከየጦሩ የተውጣጣ ተወካይ ከላይ የተነሱትን ነጥቦች ዐላማው አድርጐ ከያዘ በኋላ በየጠቅላይ ግዛቱ የሚገኘው ጦር የተያዘውን አቋም

እንዲያውቅ ሲደረግ፤ በእሥር ላይ ያለው የክብር ዘበኛ መኰንንም ጉዳዩን እንዲያውቅ ተደረገ። የተጀመረው የደመወዝ ይጨመርልን ጠንካራ ጥያቄ በየቦታው ለነበረው ጦር በምስጢር ተዳርሶ በሐሳቡ መስማማቱ ከተረጋገጠ በኋላ ተወካዮች ሐሳቡን ለአዛዦቻቸው ሳይገልጹ እንዲሁም ከግርማዊ ጃንሆይ ዘንድ ለመቅረብ ከልዩ ጽሕፈት ቤት ወይም ከእልፍኝ አስከልካዩ ጽሕፈት ቀጠሮ ሳያገኙ ራሳቸው በመረጡት የበታች ሹም ተመርተው በሠልፍ ኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት በር ደረሱ። የቤተ መንግሥቱ ጠባቂ ዘቦች ያለምንም ተቃውሞ የቤተ መንግሥቱን በር ወለል አድርገው ከፍተው ሰልፈኛው ሰተት ብሎ ገብቶ ዐደባባይ ላይ ቆመ። ይህ ድርጊት ከመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ ቀጥሎ የዐፄ ኃይለሥላሴን መንግሥት ያራደ አስደንጋጭና አስፈሪ ድርጊት ነበር።

መፈንቅለ መንግሥቱን ያከሸፉት የጦር አዛዦች ስለዚህ እንቅስቃሴ አንድ መረጃ ሳያገኙና መፍትሔ ይሆናል ያሉትን መንገድ ሳይቀይሱ ዱብዳ መድረሱ እነሱንና ንጉሠ ነገሥቱን አስተከዘ። የመጨረሻው መጀመሪያ መሆኑንም አመለከተ። ከዚህም በላይ ሰልፈኛው ወደ ቤተመንግሥት የመጣው ቀጠሮ ሳይሰጠው ቢሆንም፤ ወደ ጃንሆይ ለመቅረብ መጠየቁ ተነግሮ ጃንሆይ ምንም ሳያቅማሙ ሰልፈኛውን ለማነጋገር መጡ። ተወካዩ ጃንሆይ ፊት ቀርቦ ሊናገር ሲል አንዳች የመከላከል ወይም እንደድሮው ሥርዓት አልተጠበቀም! አንቀበላችሁም! አትናገርም! የሚል መከላከል አልተደረገም። ይህን ለማገድ የሚያስችል ዐቅም አልነበረምና። በመሆኑም ሳይወዱ የጦሩን ጥያቄ ተቀብለናል። በአምስት ቀናት ውስጥ መልሱን እንገልጽላችኋለን ተብለው ተወካዮች እጅ ነስተው ተመለሱ። በመጨረሻ ለተራ ወታደር መነሻ ደመወዝ ብር አርባ ስምንት ለመክንን ብር ሃምሣ ጭማሪ ሆኖ የለውጡ አራማጆች ባሉት መሠረት እንዳይገባ ለአገልግሎትና ለእጅ ብልጫ ይሰጥ የነበረው እንደነበረው ይቀጥል ተብሎ ተወሰነና በሬዲዮ ተነገረ። ሠራዊቱ በጉልበት ደመወዙን አስጨምሮ ወደ ሠፈሩ ተመለሰ። አንባቢ ይህ ድርጊት ቁና ነውና በሠፈሩት ቁና ስለ መሠፈር ታሪኩን ልብ ይበሉ።

በዚህ ሁኔታና ድርጊት የዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዙፋን መዝመም ጀመረ። ለደርግ አነሳስ እርሾ ሆነ። የልጅ ኢያሱም ዙፋን እንዲህ እያለ ነበር የተቦረቦረው። ይህ በአንድ በኩል የታየው ሲሆን፤ በሌላ ጐኑ ደግሞ ጦሩ አንድ ልብ ሆኖና አንድ አቋም ይዞ በመነሣቱ የታኀሣሡን መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ፈለግ በመከተል ለሕዝብ የሚጠቅም ለውጥ ያመጣል ተብሎ በሕዝብ ተይዞ የነበረው ተስፋ ቀርቶ ጦሩ በተደረገለት የደሞወዝ ጭማሪ ረክቶ ወደ ሠፈሩ በመመለሱ ሕዝቡ ወታደሩን ሆዳም ብሎ ነቀፈው። ሠራዊቱም ሰምቶ አንገቱን ደፍቶ ዝም አለ።

ያ ሁሉ ነውጥ አልፎ አገር መረጋጋት ሲጀምር፤ የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ጥሩ ስምና አቋም የነበራቸው ጥቂቶቹ ሳይቀር የታኀሣሡ መፈንቅለ

መንግሥት ቢከሽፍም ትቶት የሔደውን መንፈስ ባለማጤን የመንግሥት ሥራና ኃላፊነታቸውን ትተው ሀብት በማግበስበስ ላይ ተሰለፉ። ይባስ ብለው ባለሥልጣኑ ሁሉ እንደያቅሙ የመንግሥትን መኪና፣ አውሮፕላንና ሔሊኮፕተር ሳይቀር ለግል ሥራ በመጠቀም እርሻ መጉብኚያና የደን ቦታ መመሪያ እስከማድረግ ድረስ እየከፋ ሔደ። ሕዝብ ጉድ አለ። እግዜር የቁጣ ፊቱን ወደ አገሪቱ መለሰና የሕዝብ መከፋትና አለመረጋጋት መጣ። በመቀጠልም የጉዱ ጦር የመኖሪያ ሠፈራችን ወግ ይኑረው። የሰው መኖሪያ ይምሰል፤ ይታይልን ብሎ። መጀመሪያ ጉርምርምታ አሰማ። ቀጥሎ መንግሥትን ጠየቀ። የጉዱን ወታደራዊ ሠፈር በዚያን ጊዜ የዚህ ታሪክ ጸሐፊ አይቶታል። አንዳንድ ቤቶች ቢኖሩም በአብዛኛው የስደተኞች ጊዜያዊ መጠለያ የመሰለ አገሩ በረሃ ስለሆነ የጭራሮ ዳስ ነበር። በንጉሠ ነገሥቱ ተጉብኝቶ ቤት እንዲሠራላቸው ታዟል ተባለ። በተግባር ግን ምንም አልተደረገም። ቀደም ብሎ በነበረው ልምድ ጃንሆይማ አዘው ነበር፤ ሹሞቻቸው አድበስብሰው አስቀሩት እንጂ ይባል ነበር። አሁን ግን እየተለወጠ ሔደና ወቀሳው በቀጥታ በጃንሆይ ላይ መሆን ጀመረ። ወታደሩ ለንጉሠ ነገሥቱ የነበረው ከበሬታና ፍቅር ተሟጦ ጥላቻና ዛቻ ይነገር ጀመር።

አጋዶን የሥራ ሥፍራዬ ስለነበር። በየጊዜው በቦታው ተገኝቼ እንደሰማሁት፤ አገራችንን በባእድ እንዴት እናስይዛለን ብለን ነው እንጂ ጥሎ መሔድ አልጠፋንም። አገር ምን ይላል? ወገን ምን ይላል? ታሪክ ምን ይላል? ብለን ነው እንጂ እንደባለሥልጣኖቹ ቢሆንማ አንድ ሰው እንኳ እዚህ ቦታ አይገኝም ነበር። በማለት ሠራዊቱ ቅሬታውን ያሰማ እንደነበር አውቃለሁ። በዚህ ሁኔታ የጦሩ ልብ ሻከረ፣ ቆሰለ፤ ጊዜና ምክንያትም ጠባቂ ሆነ። እንግዲህ ወደ መሠረተ ጉዳዩ ስንመለስ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ አድራጊዎቹን ለፍርድ ማቅረብ ተጀመረ።

# የአንደኛ ደረጃ ተከሳሾች ፍርድ ቤት መቅረብ

አንደኛ ደረጃ ተከሣሾች ይገኙበት የነበረው የአንደኛ ክፍለ ጦር መድፈኛ ግቢ መፈንቅለ መንግሥቱን የሚደግፍ ኃይል ተነስቶ ችግር ቢፈጠር ለመመከት ታስቦ ይመስላል ግቢው በሁለት ጥምጥም ልዩ ልዩ መሣሪያ በታጠቁ ምርጥ ወታደሮች ከባድ መሣሪያ በተጠመደባቸው ሦስት ስሪ ኳርተር መኪናዎች ተጠናክሮ ይጠበቅ ነበር። ጠዋት የካቲት ፫ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ሁለት ሰዓት ተኩል፣ አንደኛ ተከሣሽ ጀኔራል መንግሥቱ ንዋይ ከመያዛቸው በፊት ሁሉም መኮንኖች በእኩልነትና በወንድማማችነት እንዲተያዩ ሐሳብ አቅርቦ በዚያ የነበረውን ቡድን ለመምራት ኃላፊነት የወሰደው የሻምበል ባዬ ጥላሁን በሰጠው ትእዛዝ መሠረት በትከሻቸውና በክሳዳቸው (በአንገትጌያቸው) ላይ የነበረው የማእረግ ምልክት የተነሣ ቢሆንም፤ ግሩም በሆነው ወታደራዊ ቁመናው[3] ላይ የለበሰው ቡላ ገበርዲን የመለዮ ልብስ ካደገው ጺሙ ጋር ግርማ ሞገሥና ውበት እንዳላበሰው ለመጀመሪያ ጊዜ ከነበረበት እሥር ቤት ብቅ ብሎ ለሕዝብ ታዬ። ጀኔራሉ በድል አድራጊነት ከጦር ሜዳ የመጣ የጀንጊስካንን[4] የጦር ጀኔራል መስሎ በመታየት አካባቢውን በወኔ ናጠው። በመቀጠልም የሻምበል ክፍሌ ወልደ ማርያምና የመቶ አለቃ ድጋፌ ተድላ በንቁ ወታደራዊ ስሜትና ግርማ ተከትለው በመውጣት፤ ሦስቱም ለየብቻ በስሪ ኳርተር መኪና ተሳፍረው ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመሩ[5]።

ጀኔራል መንግሥቱ ፍርድ ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረበው፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር የሚፈታ ሕዝባዊ መንግሥት አቋቁማለሁ ብሎ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ካካሔደበት ጠቅላይ መምሪያ ከነበረው የክብር ዘበኛ ጽሕፈት ቤት ከ፫፻ ሜትር በላይ በማይሆን ርቀት ከሚገኘው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ነው። አካባቢው በአንድ ሻምበል ጦር ጥብቅ ጥበቃ ሥር ነበር። የተከሳሾቹ ጉዳይ በዝግ ችሎት እንዲታይ ተወስኖ ስለነበር በፍርድ ቤቱ ውስጥ ከሚችና ከተከሳሾች ቤተሰብ ሌላ ወደ ችሎቱ እንዲገባ አልተፈቀደም። የፍርድ ቤቱ ግቢም ጣታቸውን በጠመንጃቸው ምላጭ ላይ ባሳረፉና በሥጋት ይናጡ በነበሩ ወታደሮች እየተጠበቀ ነበር። ሦስት ሰዓት ሲሆን ተከሳሾቹ ፍርድ ቤት ደርሰው ሲገቡ፤ በአካባቢው የነበረው ተመልካች ከፊሉ ሲያለቅስ፣ ከፊሉ ደግሞ የአንደኛውን ተከሳሽ ቁመናና ግርማ በማድነቅ ይመለከት ነበር። አንደኛው ተከሳሽ በደረሰበት አደጋ ምክንያት ዐይኑ አጥርቶ ስለማያይ በሰው እየተረዳ ወደ ተከሳሽ መቆሚያ ሥፍራ ተወስዶ ቆመ።

---

[3] ጀግና አንተ አይባልምና

[4] እአአ በ፲፫ኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ ሞንጎሊያን የመራና አብዛኛውን አውሮፓና እስያን የገዛ ሰው ነበር።

[5] ሦስተኛው ተከሳሽ የመቶ አለቃ ድጋፌ ተድላ አንደኛ ክፍለ ጦር በእሥር ላይ ሳለን ከነገረን እንደተረዳሁት

ዳኞቹ አንደኛ ብላታ ኃይሌ ወልደ ኪዳን፣ ሁለተኛ ኰሎኔል አበበ ተፈሪ፣ ሦስተኛ አቶ ውቤ ወልደ የስ ነበሩ። ኰሎኔል አበበ ተፈሪ በዳኝነት እንዲገቡ የተደረገው ዳኝነቱ በሲቪልና በወታደራዊ ጦር ፍርድ ቤት ኮርት ማርሻል ጥምር ፍርድ ቤት እንዲታይ ከፍተኛ ባለስልጣኖች በመወሰናቸው ነበር። ዳኞች ወደ ችሎት ከተሰየሙ በኋላ፤ ዐቃቤ ሕጉ ኰሎኔል ተፈራ ገብረ ማርያም በተከሳሾች ላይ ያቀረቡት ክስ የሚከተለው ነበር። አንደኛ፣ ተከሳሽ የክብር ዘበኛ ዋና አዛዥ የነበረው ብርጋዴር ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ በኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ቁጥር ፪፻፶ የተደነገገውን ሕግ ተላልፎ ታኅሣሥ ፬ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. መንግሥታዊ አስተዳደሩን ለመገልበጥ አልጋ ወራሹን በማስገደድ አዲስ መንግሥት መቋቋሙን የሚገልጽ ዐዋጅ በኢትዮጵያ ሬዲዮ እንዲሰማ አድርጓል። ሁለተኛ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ቁጥር ፪፻፶፪ በመተላለፍ ታኅሣሥ ፮ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ሚኒስትሮችን ጠቅላይ ገዥዎችንና ሌሎችንም ባለሥልጣኖች አሥሯል። እንዲሁም አንደኛ ክፍለ ጦር ለሕጋዊው መንግሥት ማገዝ እንዳይችል ግብረ አበሩ በሆነው የክብር ዘበኛ ጦር አደጋ ጥሏል። በታጠቀ የጦር ኃይልም በሰላማዊ ሕዝብ ላይ ሽብር አስነስቷል። ሦስተኛ፣ ሦስቱም ተከሳሾች በኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፭፻፳፪ የተደነገገውን ተላልፈው ከሞቱትና ከሌሎችም ስማቸው ካልታወቀ ግብረ አበሮቻቸው ጋር ሆነው በጭካኔ የመግደል መንፈስ ተነሣስተው ታኅሣሥ ፰ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. አዲስ አበባ ከተማ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ውስጥ ከቀትር በኋላ በ፲ ሰዓት ፲፭ ከፍተኛ የመንግሥት ሚኒስትሮችን፣ ጠቅላይ ገዥዎችን እና ምክትልና ረዳት ሚኒስትሮችን ከባድ በሆነ የግፍ አገዳደል ገድለዋል የሚል ነበር።

የፍርድቤቱ ዐቃቤ ሕግ ያቀረበውን ክስና በተለይ በአንደኛ ተከሳሽ የጤንነት ሁኔታ ከሐኪም የቀረበውን የጤንነት ማረጋገጫ ከመረመረ በኋላ ተከሳሾች የእምነት ክህደት ቃል እንዲሰጡ አዘዘ። አንደኛ ተከሳሽ የእምነት ክህደት ቃል እንዲሰጥ ሲጠየቅ፤ በቀጠሮው ዕለት (የካቲት ፲ ቀን) መልሱን እንደሚሰጥ ገለጸ። ስለዚህ በቀጠሮው ዕለት አንደኛው ተከሳሽ ጄኔራል መንግሥቱ ጠበቃውን ይዞ እንዲቀርብ የማስጠንቀቂያ ትእዛዝ በመስጠት፤ ምናልባት ጠበቃ ባያገኝ በሚል በሕገ መንግሥቱ መሠረት ፍርድ ቤቱ ጠበቃ ሊያቆምለት ስለሚችል አቶ ሕይወት ኀዳሩ እንዲቆሙለት አዟል። እንዲሁ ለተቀሩት ሁለቱ ተከሳሾችም አቶ ኃይለ ማርያም ገመዳ እንዲቆሙላቸው ተወሰነ። ቀደም ሲል አንደኛ ተከሣሽ አሁን ካለሁበት እሥር ቤት ወደ ወህኒ ቤት እንድዛወር ይደረግልኝ በማለት አቅርቦት ለነበረው አቤቱታ ዐቃቤ ሕግ ተከሳሾቹ ከፍ ባለ ወንጀል የተከሰሱ በመሆኑ ጥብቅ ጥበቃ ባለው እሥር ቤት እንዲቆዩ በማለት ባቀረበው ተቃውሞ መሠረት ፍርድ ቤቱም ፩ኛ ተከሣሽ ከነበረበት እሥር ቤት እንዲቆይ ፪ኛና ፫ኛ ተከሳሾች ግን ወደ ወህኒ ቤት እንዲዛወሩ ወሰነ።

አቶ ሕይወት ኀዳሩና አቶ ኃይለ ማርያም ገመዳ “የፍርድ ቤቱን ትእዛዝ በማክበር ለተከሳሾቹ ጥብቅና ብንቆም ለሚቆች ዘመድ በመሆናችን በሙሉ ሕሊናችን

ልንረዳቸው አንችልም" ብለው በማመልከታቸው ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ካጠና በኋላ እነሱ ቀርተው ለአንደኛ ተከሳሽ አቶ ጌታሁን ሁነኛው፤ ለሁለተኛና ሦስተኛ ተከሳሾች አቶ ተሾመ ገላግሌ የተባሉት ጠበቆች ተከሳሾቹ ከሚገኙበት እሥር ቤት ሔደው ነገሩን አጥንተው በቀጠሮው ቀን ቀርበው እንዲከራከሩ በማለት ለሁለቱም ጠበቆች ማዘዣ እንዲጻፍ አዘዘ።

የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ተከሳሾቹና ጠበቆቻቸው ቀርበው አንደኛው ተከሳሽ የዕምነት ክህደት ቃሉን ቢጠየቅ የተናቀ መንደር፣ በአህያ ይወረራል ብሎ በመተረት መልስ ባለመስጠቱ፤ ተደጋግሞ ቢጠየቅም ፍርድ ቤቱ ለሰጠኝ ጠበቃ አላስጠናሁትም። እሱንም አልፈልገውም። የውጭ አገር ጠበቃ እፈልጋለሁ[6] በማለት ቃሉን መስጠት እንዳልፈለገ አሳወቀ። በዚህም ምክንያት ፍርድ ቤቱ ተከሳሽ መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ቀርበው እንዲመሰክሩ ሲያዝ፤ አቶ ጌታሁን ሁነኛው ደንበኛዬ ካልፈለጉኝ እንድሰናበት በማለት ያቀረቡትን ጥያቄ ፍርድ ቤቱ አልተቀበለውም። የሁለተኛው ተከሳሽ ጠበቃ ተከሳሹ በሰው መግደል እንጂ በመንግሥት ግልበጣ ያልተከሰሰ ስለሆነ፤ ጉዳዩ ከአንደኛው ተከሳሽ ጋር አብሮ መታየት የለበትም ሲል አመለከተ። ፍርድ ቤቱ ግን ሁኔታው በፍርድ ጊዜ ተለይቶ ይታያል በማለት የጠበቃውን ጥያቄ ስለጣለው፤ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል መስማት ጀመረ። በሒደቱም ፳፪ ምስክሮች፣ አንደኛ ተከሳሽ ሌሎች ተባባሪዎቹን ይዞ መንግሥት ለመገልበጥ ሆን ብሎ ባነሳሳው ዐመፅ፣ በጦር ሠራዊቱ በኩል በገጠመው ተቃውሞና በደረሰበት ጠንካራ የማጥቃት እርምጃ አግቶ በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ይዟቸው በነበሩ የአገሪቱ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ላይ ጭካኔ በተሞላ መንገድ በጥይት ተደብድበው እንዲገደሉ ስለማዘዙና በግድያው እንደተካፈለ፤ እንዲሁም በዚሁ መነሻ በተከሰተው የርስ በርስ የከተማ ውስጥ ጦርነት ከመንግሥት በኩል በርካታ ሲቪሎችና ከ፴፬ ያላነሱ መኮንኖችና ባለሌላ ማእረግተኞች መሞታቸውን፣ እንዲሁም ፲፭ መኮንኖችና ባለሌላ ማዕረግተኞች መቊሰላቸውን መሰከሩ። ይህ ሁሉ የምስክርነት ቃል በተሰማበት ወቅት የተከሳሾቹ ጠበቆች በምስክሮች ላይ ያቀረቡት መስቀለኛ ጥያቄ አልነበረም።

ስለዚህ መጋቢት ፳፱ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. በነበረው ችሎት ዐቃቤ ሕግ ምስክሮችን ባሰማበት ጊዜ አንደኛው ተከሳሽ ጠበቃ ያልያዘ በመሆኑ የመስቀለኛ ጥያቄ አላቀርብም በማለቱ ታልፎ ነበር። ጠበቃ ከተመደበለት በኋላም የተከሳሽ ጠበቃ ከ፫ኛ እስከ ፰ኛ ላሉት የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች መስቀለኛ ጥያቄ ቢያቀርቡም የተሰጠው መልስ ግን በጉዳዩ ላይ መሠረታዊ ለውጥ ሊያመጣ አልቻለም። እንዲሁም አንደኛው ተከሳሽ ዘጠኝ የመከላከያ ምስክሮች ቢያቀርብም ከወንጀሉ ነፃ የሚያደርግ ምስክርነት ባለመስጠታቸው የሁለተኛና የሦስተኛ ተከሳሾች ምስክርነትም ከወንጀል ነፃ

---

[6] ያገር ውስጥ ጠበቆች ለራሳቸው በመፍራት እንደልብ ሊከራከሩ ስለማይችሉ እንደልብ የሚከራከር ጠበቃ መፈለጋቸውን ለመግለጽ ነው።

ስላላደረጋቸው ጉዳዩ መሰማት ቀጠለ። የቀረቡት ምስክሮች ሁሉ ሁለተኛና ሦስተኛ ተከሳሽ በሥራ በነበሩበት ወቅት ስለነበራቸው መልካም ጠባይ በመግለጽ ቢመሰክሩም፤ መንግሥት ለመገልበጥ ካሴረ ግለሰብ በተሰጠ ትእዛዝ ወንጀል ስለመፈፀማቸው ተመስክሮባቸው ዐቃቤ ሕግ የመፋረጃ ሐሳብ እንዲያቀርብ ለመጋቢት ፲፰ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ተቀጠረ።

በቀጠሮው እለት ዐቃቤ ሕግ አንደኛ፣ ሁለተኛና ሦስተኛ ተከሳሾች የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፪፻፶፪ና ፭፻፳፪/፩ በመተላለፍ መንግሥት በኃይል የመገልበጥ ተግባር ለመፈፀም የመንግሥት ባለሥልጣናትን ሲገድሉ ባስነሱት ሽብር በርካታ መኮንኖችና ባለ ሌላ ማዕረግ የሠራዊቱ አባላትና ሰላማዊ ሰዎች እንዲያልቁ ምክንያት ሆነው ለመገኘታቸው በዐቃቤ ሕግ ምስክሮች የተረጋገጠ በመሆኑ፤ አንደኛው ተከሳሽ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ ፭፻፳፪ ንዑስ አንቀጽ ፩ በሚያዘው መሠረት ማዕረጉ ተገፎ የስቅላት ቅጣት እንዲፈፀምበት፤ በተጨማሪም በወንጀለኛ መቅጫ ደንብ አንቀጽ ፹፩ ሀ/ለ እና ፺፯/፪፻፶፪ መሠረት ተከሳሹ ያለው ንብረት በሙሉ ለመንግሥት እንዲገባ ይፈረድልን በማለት አቀረበ። የአንደኛው ተከሳሽ ጠበቃ ባቀረቡት የመፋረጃ ሐሳብ የተከሳሽን ቅጣት ለማቃለል የሚያስችል ሕግ ነክ ሳይሆን ሃይማኖታዊ መጻሕፍትን በመጥቀስ የሰው ልጅ መገዳደል ያለ፣ የነበረና የሚኖር እንደሆነ ጠቅሰው አመለከቱ። የሁለተኛ ተከሳሽ ጠበቃ የምስክሮችን ቃል አካሔድ በዝርዝር በማስቀመጥ ካስረዱ በኋላ አንደኛው ተከሳሽ ሁኔታውን በማደናገር የሌለውን እንዳለ ያልተደረገውን እንደተደረገ አድርገው ለተለያዩ የመንግሥት ባለሥልጣናት በማቅረብ የራሳቸውን ድብቅ ዐላማ ለማስፈፀም መሞከራቸው፤ ሁለተኛው ተከሳሽም የበታች ሹም ስለበሩ አዛዣቸውን በማመን እንጂ ወንጀሉን አስበውና ተረድተው አለመፈፀማቸውን ስለሚያረጋግጥ እንዲሁም በኢትዮጵያ ሕግ ቁጥር ፷፲ ስለወታደራዊ አስፈላጊ /አስቸኳይ/ ሁኔታ በተሰጠው ሕግ መሠረት በወታደራዊ አደጋ ጊዜ በተለይም በዐድማ፣ ግርግር ወይም በጦር ግንባር፣ አንድ የወታደር አዛዥ ወይም የበላይ ሹም፣ ሥነ-ሥርዓትን ለማስከበር ወይም ተገቢውን የታዛዥነት ተግባር ለማፅናት በነዚህ በተዘረዘሩት ጊዜያት የፈፀመው አያስቀጣም ስለሚል፤ ፍርድ ቤቱ ሁኔታውን በሚገባ መርምሮ በአንቀጹ መሠረት ነፃ እንዲያደርገው በማለት አቀረቡ። የሦስተኛ ተከሳሽ ጠበቃ የምስክሮችን ቃል በዝርዝር ካቀረቡ በኋላ በአመዛኙ እርስ በርስ እንደሚቃረንና በተለይም የመከላከያ ምስክሮች ሦስተኛው ተከሳሽ ዘብ ያለመጠበቁን፣ የሲቪል ልብስ መልበሱንና የብረት ቆብ አለማድረጉን ስለመሰከሩለት፤ ፍርድ ቤቱ በአዲሱ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፭፲/፭፱/፲/፲፭ እንደተመለከተው ከትምህርት ቤት በማስገደድ ትዕዛዝ አምጥተው ከሰልፍ ውስጥ እንዲገኝ ያደረጉት መሆኑን ፍርድ ቤቱ ተረድቶ ፍርድ እንዲሰጥ ጠየቁ።

በዚህ መልኩ ዳኞች የዐቃቤ ሕጉንና የሦስቱን ተከሳሾች ጠበቆች የመፋረጃ ሐሳብ ከሰሙ በኋላ የሚከተለውን ፍርድ ሰጡ።

## ፍርድ

አንደኛ ተከሳሽ የክብር ዘበኛ ዋና አዛዥ የነበረው ጄኔራል መንግሥቱ በኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር በ፪፻፹፩፣ ፪፻፹፪፣ ፭፻፳፪ የተደነገገውን ሕግ ተላልፎ ታኅሣሥ ፬ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ሚኒስትሮችን ጠቅላይ ገዥዎችንና ሌሎችንም ባለሥልጣናት አሥሯል። በአንደኛ ክፍል ጦር ላይ አደጋ እንዲጣል አድርጓል። በጦር ኃይል ሽብር አስነስቷል። የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፭፻፳፪ን በመተላለፍ በጭካኔ የመግደል መንፈስ በመነሣሳት ሚኒስትሮችንና ሌሎች ባለሥልጣናትን ከባድ በሆነ የግፍ አገዳደል አስገድሏል። ይህም በስምንት ምስክሮች ቃል ተረጋግጧል። ባስነሣውም የጦር ሽብር ፳፬ መኮንኖችና ወታደሮች መሞታቸው፣ ፲፩ መቁሰላቸው በጽሑፍ ማስረጃ ጭምር ተረጋግጦ የቀረበ በመሆኑ ተከሳሹ የፈፀማቸው ወንጀሎች ከባድና አሰቃቂዎች፣ አፈፃፀማቸውም ከዳተኛነት፣ ማታለልንና ግፈኝነትን የያዙ ስለሆነ፤ በድካሙ ያፈራው ንብረት በሕግ መሠረት እንዲወረስና በአደባባይ በስቅላት እንዲቀጣ።

ሁለተኛ ተከሳሽ ክፍሌ ወልደማርያም የተከሰሰበትን ፭፻፳፪ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በመተላለፍ ጥፋተኛ ነው። ሆኖም ወንጀል ለመሥራት አስቦ ያልተነሣሳ፣ ከአደጋውም በኋላ እጁን በፈቃዱ ለፖሊስ መስጠቱንና የምስክሮቹን ቃል መዝነን በቁጥር ፭ ንዑስ ቁጥር ፪/፴፫/፷፱/ሀ/ሐ/ሠ፡- ፩፻፹፬ ለ ፩፻፹፯ የተጻፈውን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ተመልክተን፣ ያገኘው ሽልማትና ማዕረግ ተገፎ እጁ ከተያዘበት ታኅሣሥ ፴[7] ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም ጀምሮ ፲፭ (በአሥራ አምስት ዓመት) ፅኑ እሥራት እንዲቀጣ።

ሦስተኛ ተከሳሽ ድጋፍ ተድላ እንደ ሁለተኛ ተከሳሽ በተመሳሳይ ሁኔታ የሚታይ በመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ቁጥር ፭፡፩፡፳፫፡/ሀ/ሐ/ሠ - ፩፻፹፬ ለ ፪፻፹፯ የተጻፈውን ተመልክተን በ፲ ዓመት ፅኑ እሥራት እንዲቀጣ በድምፅ ብልጫ ወስነናል።

ስለሆነም ሦስተኛው ዳኛ ኮሎኔል አበበ ተፈሪ ፫ኛው ተከሳሽ በተከሰሰበት ወንጀል በአንቀጽ ፭፻፳፪ ስለሰዎች መግደል ያልተመሰከረበት ስለሆነና፣ ግዙፍነት ባለው ማስረጃ ያልተደገፈ በአንድ በተጠረጠረ ምስክርነት ያውም በመከላከያ የፈረሰውን ምስክርነት ይዞ ተከሳሹን ጥፋተኛ አድርጐ መቅጣት ተገቢ ስለማይሆን በነፃ ይለቀቅ በማለት የሐሳብ ልዩነታቸውን አሳውቀው የፍርዱ ውሳኔ በዚህ ተደምድሞ በፍርዱ ቅር የተሰኘ ይግባኝ ማለት ይችላል ብለው ሲጨርሱ፤ አንደኛው ተከሳሽ ጄኔራል መንግሥቱ ትንቢትና ወዮታ ያዘለ ማስጠንቀቂያቸውን[8] እንዲህ ሲሉ ገለጹ።

7 *እዚህ ጋር ከላይ እንደጠቀስኩት የተያዙት ታኅሣሥ ፲፪ መሆኑ ይታወቃል። በፍርድ ቤቱ ውሳኔ ላይ ስህተት እንዳለ ያመለክታል።*

8 *ከዚህ በኋላ ወደሞት እየሔዱ ያሉትን ጄኔራል በነበረው የተለመደ ስምና ክብራቸው አንቱ እያልኩ እቀጥላለሁ።*

.... እናንተ ዳኞች የበየናችሁብኝን የሞት ፍርድ ያለይግባኝ ተቀብየዋለሁ:: ይግባኝ ብዬ ጉዳዬን የሚመለከትልኝ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቢሆን ኖሮ ይግባኝ ማለት በፈለግሁ ነበር:: ነገር ግን እንደማይሆን ዐውቃለሁ:: የዐፄ ኃይለ ሥላሴን ፊት ለማየት አልፈቅድም::

.... ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት፣ ነፃነትና እርምጃ የተነሣሁ ወንጀለኛ ነኝ እንጂ ላፋጀው የተነሣሁ ወንበዴ አይደለሁም:: ይህንን ለማድረግ ፈልጌ ቢሆን ኖሮ ማንም የማይወዳደረው ሠራዊትና መሣሪያ ሳላጣ ዛሬ በእናንተ ፊት ለመቆም ባልበቃሁ ነበር::

.... ከእናንተ ከዳኞችና የሞት ፍርድ እንድትበይኑብኝ ካዘዛችሁ ሰው ይልቅ ፍርድ ተቀባዩ የዛሬው ወንጀለኛ የነገው ባለታሪክ ነኝ:: የእኔ ከጓደኞቼ መካከል ለጊዜው በሕይወት መቆየትና ለእናንተ ፍርድ መብቃት የዘመኑን ፍርድ ለመጨረው ትውልድ የሚያሳይ ይሆናል::

.....ዋ! ዋ !ዋ! ለእናንተና ለገዥአችሁ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሐሳቡ በዝርዝር ገብቶት በአንድነት በሚነሣበት ጊዜ የሚደርስባችሁ መዓት የሚያሰቅቅ ይሆናል::

ያም ሆነ ይህ ፍርዱ ከተወሰነ በኋላ በጀኔራሉ የሞት ቅጣት የተፈጸመው በአፋጣኝ ሲሆን፤ አፈፃፀሙንም በወቅቱ የፍርድ ሚኒስትር የነበሩት ዶ/ር ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴ እንደሚከተለው ይተርኩታል::[9]

የእልፍኝ አስከልካዩ ኮሎኔል አሰፋ ደምሴ (በኋላ ጄኔራል) መጋቢት ፰ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ከሌሊቱ ፬ ሰዓት ስልክ ደውሎ ‹‹የጄኔራል መንግሥቱን የሞት ቅጣት ፍርድ ጃንሆይ አጽድቀውታል:: ቅጣቱን በጧቱ እንድታስፈፅም አዘዋል:: አንደኛ ክፍለ ጦር መድፈኛ ግቢ በቶሎ እንገናኝ" አለኝ:: እንዳለኝ ቶሎ ተዘጋጅቼ ከተባለው ቦታ ስደርስ፤ ሺብር የተነሳ ይመስል በአካባቢው የነበረው ግርግር ሌላ ነበር:: ከዚያ ጄኔራል መንግሥቱን ሰላምታ ከሰጠሁት በኋላ የሞት ቅጣቱ የሚፈፀመው በዕለቱ ጧት መሆኑን ነገርኩት:: ምንም ዓይነት የመደንገጥ ወይም የመናደድ ነገር አላሳየም፤ ምንም አልመሰለውም:: ዝም ብሎ ተቀበለው:: ኮሎኔል አሰፋ ቀለም ከመነከሩ በቀር በጣም ተራ የሆነ ስስ መርዶፍ እጅጌው አጭር ሸሚዝና ቁምጣ ሱሪ የወህኒ ቤት ልብስ አምጥቶ ኑሮ "ያን ይልበስ" አለ:: አይሆንም ብዬ ብዙ በመጨቃጨቅ ጊዜ ካሳለፍን በኋላ "እኔ ለጃንሆይ ይነገር እንጂ ይህን ልብስ አልብሸ ቅጣቱን አላስፈጽምም" ስላልኩ፤ ሌሊት ጃንሆይ እንዲሰሙት ተደርጐ እሺ የራሱን ልብስ ይልበስ ብለው ስለፈቀዱ፤ የራሱን ልብስ ከለበሰ በኋላ በስሪ ኳርተር መኪና ላይ ተሳፈር ስንለው እሱን እሺ ነገር ግን አንድ ጥያቄ አለኝ ብትቀበሉኝ አለ:: "እሺ ቿይቅ" አልነው:: "እዚህ ያሉት ወታደሮች ባይኔ አጥርቶ አለማየት ምክንያት ወደ ሽንት ቤት ስሔድ እቸገር ስለነበር ደግፈው ወስደው በማድረስ፣ በመመለስና የሚያስፈልገኝን ሁሉ በማድረግ ውለታ ውለውልኛልና እንዳመሰግን ብትሰበስቡልኝ ፈቃዳችሁን እጠይቃለሁ"


9 ዶ/ር ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴን በ፲፱፻፺፮ ዓ.ም. ቃለ መጠይቅ አድርጌላቸው

አለ። ፈቀድንለትና የተሰበሰቡትን አመሰገናቸው። ወታደሮቹ ወጣቶች ስለነበሩ በሁኔታው መቆጨትና ማዘናቸው በፊታቸው ላይ ይታይ ነበር።

ከዚያ በስሪ ኳርተሩ ላይ ተሳፍሮ በብዙ ወታደሮች ታጅቦ ተክለ ሃይማኖት አደባባይ ከመስቀያው ቦታ እንደደረስን፤ ወደ ተክለሃ ይማኖት ቤተክርስቲያን ዞሮ እጅ እንዲነሳ አደረግን። ከዚያ ገመዱን ከአንገቱ ላይ ሊያገቡ ሲሉ ኮሎኔል አሰፋ ደምሴ አላይም ብሎ መሔድ እንደጀመረ፤ "ጥሩት" ብሎ አስጠራውና «እባክህ እነዚህ ሰዎች አያውቁትምና የገመዱን ቋጠሮ በተገቢው ቦታ እንዲያደርጉት ንገርልኝ አለው። ይህን ያለበት ምክንያት በላይ ዘለቀ ሲሰቀል ገመዱ በትክክለኛው ቦታ ባለመሆኑ የደረሰውን ስቃይ ዓይቶ ስለነበር ነው። እሱም "እሺ" ብሎ ለሰዎቹ ነገራቸው። ከዚያ በኋላ ገመዱን በተገቢው መንገድ አደረጉለትና መኪናው ወደፊት ሄደ። ብዙም አልቆዬ ነፍሱ ወዲያው አለፈ።

## የሻምበል ክፍሌ ወ/ማርያምና የመቶ አለቃ ድጋፍ ይግባኝ

የሻምበል ክፍሌ ወልደ ማርያምና የመቶ አለቃ ድጋፍ ተድላ ለተሰጣቸው ፍርድ ይግባኝ ሲሉ፤ ዐቃቤ ሕጉም ይግባኝ አቅርቦ ስለነበር፤ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኛቸውን ከመረመረ በኋላ የሻምበል ክፍሌ ወ/ማርያም የ፲፰ ዓመቱ የፅኑ እሥራት ፍርድ በሞት ተለወጠ። የመቶ አለቃ ድጋፍ ተድላ የ፲ ዓመት ፅኑ እሥራት ፍርድም ፀንቷል በማለት ፍርደኞችን አሰናበታቸው። በዚህ ፍርድ መሠረት፣ ፍርዱ በተሰጠ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ አንድ ሌሊት ፬ ሰዓት የሻምበል ክፍሌ ወልደማርያም የሞት ቅጣቱ ወደሚፈፀምበት ቦታ ሲወስዷቸው ዓለም በቃኝ ለነበርነው እሥረኞች "እኔ ምንም ወንጀል አልፈጸምኩም ንጹህ ደም ነው የሚያፈሱት" ሲሉ ተደምጠዋል። የመቶ አለቃ ድጋፍ ተድላ ግን ቅጣቱን እንዲፈፅም ወደ ወህኒ ቤቱ ተመለሰ።



የመቶ አለቃ ድጋፍ ተድላ

የመቶ አለቃ ድጋፍ የቅጣቱን ጊዜ የሚያቀልል መልካም አጋጣሚ በማግኘቱ ግን የእሥር ጊዜውን ሳይጨርስ የነፃነት አየር ለመተንፈስ በቀቷል። ነገሩ የሆነው እንዲህ ነው። ከዚህ ታሪክ ጸሐፊ ጋር የወህኒ ቤቱ የእንዱስትሪ ክፍል ባዲስ መልክ ተዋቅሮ እሥረኛው ሲፈታ ራሱን የሚያስተዳድርበት ሙያ ቀስሞ እንዲሔድ እንድናደርግ ታዘዝን። እኛም መዋቅር ቀርፀን በየሥራ ዘርፉ የሚገቡትን እሥረኞች እንደመለመልን፣ ንግሥት ኤልሳቤጥ ኢትዮጵያን ለመጐብኘት ሲመጡ ለክብራቸው በቤተ መንግሥት



የመቶ አለቃ ድጋፍ ተድላ

ውስጥ ለሚደረገው ታላቅ የእራት ግብዣ ፪ሺህ፭፻ ሰዎች መያዝ የሚችል አዳራሽና የመስተንግዶ ግብር ገበታው በተመቸ ሁኔታ እንዲዘረጋ ፕላን ሠርቶ እንዲሰጣቸው የወህኒ ቤቶች አስተዳደር ረዳት ሚኒስትር አቶ ጫንያለው ተሾመ የመቶ አለቃ ድጋፍን አዘዙት። የመቶ አለቃ ድጋፍም ጥሩ የሆነ ፕላን በአጭር ጊዜ ሠርቶ ፕላኑን ለአቶ ጫንያለው ሰጣቸው። አቶ ጫንያለው ይህንኑ ፕላን ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ለቤተ መንግሥት ኃላፊዎችና ለጃንሆይም አሳይተው ስለተስማሙ ለሁለት ወር ለሚሆን ጊዜ ኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት ግቢ ውስጥ ሲሠራ ቆየ። ንግሥቲቱ መጥተው የግብሩ ገበታውና አዳራሹ ሁሉን አርኪ በሆነ መልክ በመዘጋጀቱ ለዚህ መልካም ውጤት ያበቁት ሁሉ ሲመሰገኑ የመቶ አለቃ ድጋፍ ተድላም ይህን ሁሉን ያስደሰተ ሥራ በመሥራቱ እንደሌሎቹ ተመስግኖ በዚያውም አምላክ ምክንያት አድርጐለት የእሥራት ጊዜውን አጋማሽ እንኳን ሳይታሠር በምሕረት ለመፈታት አበቃው።